ነው የሚለው ቡድን አይሉ በመምጣቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ተመሠረተ። በእንግሊዝኛ ምኅጻረ ቃሉ ይበልጥ የሚታወቀው «ኡዙዋ»ና መጽሔቱ *Struggle* («ታገል») በኢትዮጵያ ተማሪዎች ፖለቲካ ውስጥ የግራ ክንፉን ድርጅታዊና ርእዮተ ዓለማዊ የበላይነት አረጋገጡ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ባገር ውስጥ ብቻ ሳይወሰን በውጭ ሀገርም ጠንካራ ዘርፍ ነበረው። በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር («ኤዙና») እና በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር («ኤዙዌ») የዚህ ዘርፍ አስተባባሪዎች ነበሩ። በውጭ ያሉት ተማሪዎች ካገር ከመራቃቸውም ሌላ አብዮታዊ ሥነ ጽሑፍ ያሳንዳች ገደብና ሳንሱር ማግኘት በመቻላቸው ከዕለት ዕለት የፖለቲካ ትግሉ ይልቅ በቲዎሪና ርእዮተ ዓለሙ የመራቀቅ ዝንባሌ ይታይባቸው ነበር። በተለይም የሁለቱ ዐበይት ማኅበራት ልሳኖች፣ ማለትም የ«ኤዙና» «ቻሌንጅ» እና የ«ኤዙዌ» «ታጠቅ» የጠቅላላ የተማሪው ንቅናቄ የቲዎሪ መጽሔት ለመሆን በቁ። ይሁን እንጂ በውጭው የቲዎሪ ርቀትና ባገር ቤቱ የፖለቲካ ትግል መካከል የነበረው ቅንብር አነስተኛ ነበር። አብዮቱ መዳረሻ ላይም ውጭ ያለው ተማሪ ሁለት ቦታ ተከፍሎ የከረረና የመረረ የቃላት ጦርነት ያካሄድ ነበር። ከአብዮቱ በኋላ ይኸው ክፍፍል ወዳገር ቤት ተዛምቶ ከፍተኛ እልቂት አስከተለ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ለለውጥ ባለው ጽናትና በመሥዋዕትነት ስሜቱ ብዙም ወደር የሚገኝለት አይደለም። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ግልጽ የፖለቲካ ተቃውሞ በታገተበት ሥርዓት ውስጥ የተቃውሞን ሰንደቅ በኩራትና በጀግንነት አነሡ። ዳሩ ግን ያገራቸው የፖለቲካ ባህል ለዚህ ከባድ ተግባር በቅጡ ያዘጋጃቸው አልነበረም። ዲሞክራሲያዊና የነፃ አመለካከት ባህል ሳገራቱ እንግዳ በመሆኑ ይኸው ችግር የተማሪዎቹን ንቅናቄ ተጠናወተው። ንቅናቄው ለተቃዋሚ ሐሳብ ስፍራ የለውም ነበር። የርእዮተ ዓለም ክርክሮች እንደ ዘመነ መሳፍንቱ የሃይማኖት ክርክሮች ከፀጉር የሰለሉና ደም የሚያቃቡ ሆኑ። ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርእዮት የአስተሳሰብ ዘይቤ መሆኑ ቀረና እንደ እምነት ተወሰደ። መፈክሮች የቲዎሪን ስፍራ ያዙ። የከረረ የተቃውሞ አቋም መያዝ በአግባብ ነው ወይስ አለአግባብ ብሎ ከመመዘን ይልቅ በራሱ የሚፈለግ ሁኔታ ሆነ። የሁሉም ፉክክር ከግራም በላይ ግራ ለመሆን ነበር።

ለዚህ ዓይነት አክራሪ የፖለቲካ ባህል አንድ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገው መንግሥት ራሱ የወሰደው ያፈና አቋም ነው። መንግሥት በተማሪዎች ላይ የሚወስደው እርምጃ መሪዎችን ላጭር ጊዜ በፖሊስ ጣቢያ በማሰር ይጀምርና ወደ ኋላ በገፍ ተማሪዎችን ወደ በረሃ ማጋዝ ይደርሳል። ተማሪዎችም ባንፃሩ በሰልፍና መፈክር በማነብነብ የጀመሩትን ተቃውሞ ወደ አውሮኘላን ጠለፋ አሸጋገሩት። በተለይም አብዮቱ መዳረሻ ላይ የመንግሥት አፈና እየከፋ ሲሄድ እያሌ ተማሪዎች ስደትን መረጡ። ይህም ሁኔታ በተለይ በሰሜን አሜሪካ የነበረውን የተማሪዎች ንቅናቄ በማጠናከር ጉልህ ለውጥ አመጣ። የሆነው ሆኖ የተማሪና የመንግሥት ፍጥጫ እየከረረ ይምጣ እንጂ፣ የ1966ቱ አብዮት ሁለቱም ባልጠበቁት ሰዓትና ሁኔታ ነበር የፈነዳው። ሥርዓቱም የፍጻሜውን መቃረብ አልተረዳም ነበር። ለዓመታት የታገሉት ተማሪዎችም ያን የጠሉትን ሥርዓት በምን እንደሚተኩት ገና እውጠንጥነው አልጨረሱም ነበር።

# ምዕራፍ ስድስት

# አብዮትና መዘዙ

## መግቢያ

የ1966 አብዮት ለሁሉም ዱብ ዕዳ ነበር። ለአሥር ዓመታት ያህል የታገሉለትን ተማሪዎችም ሳይቀር አብዮቱ እንደ ማዕበል ነው የመታቸው። የገኘው መደብማ ምን እንደመታው ሳያውቅ ማዕበሉ ጠርጎ ወሰደው። «አብዮት» የሚለውን ቃል ራሱ ብዙዎች ምን እንደሆነ ያጤኑት ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ ነው። የሂደቱን ድንገተኛነት ለመግለፅም «አብዮት ፈነዳ» ከሚለው የተሻለ አገላለፅ ማሰብ ያዳግታል። እንደማንኛውም ፍንዳታ ሁሉ፣ አብዮቱ በመንግሥትም ሆነ በጠላቶቹ ጎራ መደናበርና መደናገርን አስከተለ። ስለሆነም አብዮቱን መምራት ይቅርና ሰልፍን ከሂደቱ ጋር ማስተካከሉ ብርቱ ፈተና ሆኖ፣ የማታ ማታ አገሪቱን ለፍፁማዊ ወታደራዊ አገዛዝ አሳልፎ ሰጠ።

ይሁንና የኢትዮጵያ አብዮት ድንገተኛነት እንግዳ ነገር አይደለም። የዓለምን ታላላቅ አብዮቶች ያጠናው አሜሪካዊው ታሪክ ተመራማሪ ክሬን ብሪንቲን እንዳለው፣ «አብዮት ምንጊዜም ቢሆን ድንገተኛ ነው።» ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮት ከሌሎች ታሪካዊ አብዮቶች ጋር የሚጋራው ድንገተኝነትን ብቻ አይደለም። እንደነሱ ሁሉ ፈጣን፣ ግዙፍና አመፅ የተሞላበት፣ ማኅበራዊ ለውጥ የታየበት፣ ላይ የነበረው ወደ ታችና ታች የነበረው ወደ ላይ የተሸጋገረበት ክስተት ነው። ዝነኛውን የሌኒንን የአብዮታዊ ወቅት አገላለፅ ተከትሎ፣ ገዥዎች እንደ ጥንቱ መግዛት የተሳናቸው ተገዥዎችም እንደ ቀድሞው አልገዛም፣ አሻፈረኝ ያሉበት ወቅት ነው። የኢትዮጵያ አብዮት ከቀደምት አብዮቶች ጋር የሚጋራው ሌላ ነጥብ ደግሞ፣ ብሩህ ሕልምን ያለመ አብዮታዊ ትውልድ መኖሩ፣ የዚያኑ ያህል ደግሞ አብዮቱን ያቀጣጠለው ወገን አብዮቱን ለመቆጣጠር አለመቻሉ ነው።

የገጠሩን ሕይወት በማያሻማ መንገድ የለወጠ ምጡቅ የመሬት ድልድልን በማወጁ ደግሞ የኢትዮጵያ አብዮት ከቻይናው አብዮት ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል። ይሁን እንጂ፣ የኢትዮጵያ አብዮት ይበልጥ የሚቀራረበው ከፈረንሣይና ከሩሲያ አብዮቶች ጋር ነው ቢባል እምብዛም ውል የሳተ አይሆንም። እንደነሱ ሁሉ የኢትዮጵያ አብዮትም ለዘመናት የቆየ ሥርወ መንግሥትን ገርስሷል (ምንም እንኳ የፈረንሣዩ ሥርወ መንግሥት በ19ኛው መቶ ዓመት ለጥቂት አሠርት ዓመታት እንደገና ለማንሰራራት ቢችልም)። በሦስቱም አገሮች፣ በብሩህ ተስፋ የጀመረው አብዮት ብዙም ሳይቆይ ወደ ሽብርና ፅልመት ተሸጋገረ። ሕዝባዊ ሥልጣንና ዳኝነትም በአምባገነናዊ አገዛዝ ተተካ። የፈረንሣይ አብዮት ናፖሊዮንን፣ የሩሲያ አብዮት ስታሊንን፣ የኢትዮጵያ አብዮት ደግሞ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ወለደ። እንግሊዛዊው ደራሲ ጆርጅ ኦርዌል «አኒማል ፋርም» በተሰኘው ምጸታዊ ልብ ወለዱ እንዳስቀመጠው፣ አብዮት

መጀመርያ ሁሉንም እኩል አደረገች፤ ብዙም ሳይቆይ ግን አንዳንዶቹ «ይበልጥ እኩል» መሆናቸውን አወጁ።

በብዙ ሰዎች ኅሊና፣ የኢትዮጵያ አብዮትና የመንግሥቱ ስብዕና የማይነጣጠሉ ሆነው ቆይተዋል። በተለይም ለምዕራቡ ዓለም ከ1966 እስከ 1983 ያሉት የአብዮት ዓመታት አንዳችም ማርከሻ የሌለው ዘመነ ጥፋት ነው። አያሌ ኢትዮጵያውያንም ቢሆኑ፣ ሽብርና የርስ በርስ ጦርነት ካስከተሉት ደምና ዕንባ ባሻገር፣ የአብዮቱን በጎ ገፅታዎች ለማየት ይቸገራሉ። በስክነ መንፈስ ሁኔታዎችን ለማጤን ለሚሞክር ተመራማሪም ቢሆን፣ ከሁለት አሠርት ዓመታት ያህል ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ለውጦች በኋላ ሀገሪቷ ይህን በጎ ነገር አገኘች ብሎ አፍ ሞልቶ ለመናገር ያዳግታል። ምናልባት የዘመናትን ብዝበዛ ያስወገደው የመሬት ዐዋጅ እንደ አንድ ዘላቂና በጎያዊ ክንዋኔ ሊታይ ይችል ይሆናል። ያም ሆኖ ወረድ ብለን እንደምናየው የአርሶ አደሩን ሕይወት አልጋ በአልጋ አደረገለት ለማለት የሚቃጣው ሰው ጥቂት ነው። ይህ ሁሉ ግን የኢትዮጵያ አብዮት በፈነዳበት ወቅት የነበረውን ሕዝባዊ ድጋፍ መካድ አለብን ማለት አይደለም። ስለሆነም፣ ይህን ሕዝባዊ ገፅታውን ዘርዝር አርጎ ማየቱ ሚዛናዊ ፍርድ ለማስተላለፍ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

## ሕዝባዊ አመፅ

በየካቲት 1966 ገንፍሎ የወጣው ሕዝባዊ አመፅ በመሠረቱ የከተሜ ንቅናቄ ነበር። አልፎ አልፎ አንዳንድ ጉምጉምታ ቢሰማም ገጠሬው ባብዛኛው ድምፁን አጥፍቶ ቁጭ ብሎ ነበር። በከተሞች ግን፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች (ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ወታደሮች እና ሥራ-አጥ ወጣቶች) ሥርዓቱን አሻፈረኝ ብለው ተነሱ። ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ ይህ ሕዝባዊ አመፅ መጀመርያ የተለኰሰው በነገሌ ቦረና የሠፈሩት የ4ኛ ክፍለ ጦር ወታደሮች በጥር ወር መጀመርያ ላይ ባነሱት አድማ ነው።

የነገሌ ወታደሮች ጥያቄ በመሠረቱ ፖለቲካዊ ሳይሆን የኑሮ ሁኔታቸውን የተመለከተ ነበር። ዋና ብሶታቸውን ብለው ያመለከቱት የምግብና የውሃ እጥረትን ነው። በተጨማሪም ደመወዛቸውን በወቅቱ አለማግኘታቸው ሌላ ያስመረራቸው ጉዳይ ነበር። ከነዚህ በግልፅ የተቀመጡ ጥያቄዎች ጀርባ ግን በመኰንኖችና ወታደሮች መካከል የነበረው የጌታና ሎሌ መሰል ግንኙነትም ሁኔታውን ሳያባብሰው አልቀረም። እያደርም አማፅያኑ ወታደሮች እየተደፋፈሩ ሲሄዱ ጥያቄዎቻቸውን ሰፋ ማድረግ ጀመሩ። የበረሃና የጡረታ አበል እንዲቆረጥላቸው፣ የተሻለ ዩኒፎርም እንዲሰጣቸውና ለልጆቻቸውም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲከፈትላቸው ጠየቁ። በሚያስተላልፉት የሬዲዮ መልእክቶች አማካይነትም ሌሎች የጦር ሠራዊት ክፍሎች ከጎናቸው እንዲሰለፉ ጠየቁ።

የባታልዮንና የክፍለ ጦር አዛዦች ነገሩን ለማብረድ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። ነገሩ እየከበደ ሲሄድ፣ የምድር ጦር ጠቅላይ አዛዥ ጀኔራል ድረሴ ዱባለ በቦታው በመገኘት አማፅያኑን ለማግባባት ሞከሩ። ወታደሮቹ ይባስ



ብለው ጀኔራሉን ከብርጌድ አዛዡና ከሌሎች መኰንኖች ጋር አገቱት። እንዲያ ያስመረራቸው ኑሮ ምን እንደሚመስል በቅጡ እንዲረዱትም የተበላሸውን የራሽን ምግብና ድፍርስ ውሃ እንዲጠጡ አስገደዱት። በመጨረሻ ወታደሮቹን አግባብቶ ጠቅላይ አዛዡን ከእስር ለማስፈታት የቻለው ሌላው ልዑክ ጀኔራል አበራ ወልደ ማርያም ነበር።

በነገሌው አመፅና እሱን ተከትሎ በጦሩ በተዛመተው ንቅናቄ መካከል የነበረው ግንኙነት ምን ያህል ቀጥተኛ እንደሆነ አስረግጦ መናገር ባይቻልም የአማፅያኑ የሬዲዮ መልእክቶች በመጠኑም ቢሆን ግፊት እንዳደረጉ መገመት አያዳግትም። ደሞዝ እንዲጨመርላቸውና የኑሯቸው ሁኔታ እንዲሻሻልላቸው የአዲስ አበባው አራተኛ ክፍለ ጦርና የደብረ ዘይቱ አየር ኃይል ክፍል ባልደረቦች ያቀረቧቸው ጥያቄዎች የነገሌው አመፅ ነፀብራቅ ይመስላሉ። ከዚህም የበለጠ ተመሳሳይነት ያለው በኤርትራ የሚገኘው የሁለተኛ ክፍለ ጦር ሁኔታ ነው። የጠረፍ ክፍለ ጦሮች በወታደራዊው አመፅ ግንባር ቀደም ሚና መጫወታቸው ያለምክንያት አይደለም። የጦርነትን ገፈት የሚቀምሱትና በዚያው ልክ ደግሞ የኑሯቸው ሁኔታ ይበልጥ እንግልት የበዛበት እነሱው ነበሩ። የአሥመራው ጦር በነበረበት ፍትጊያ ይበልጥ ነቅቶና በነበረውም ወታደራዊ ጡንቻ ተደፋፍሮ ይመስላል የከተማውን ራዲዮ በቁጥጥሩ ሥር በማድረግ ከኤኮኖሚያዊ ጥያቄዎችም አልፎ የመንግሥት ለውጥን በመጠየቅ አመፁን አንድ እርምጃ ወደፊት ገፋው። በዚህም እርምጃው ለአክሊሉ ሀብተወልድ ካቢኔ ሥልጣን መልቀቅ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ አደረገ።

የወታደሮቹ እንቅስቃሴ አብዛኛውን ጊዜ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ፣ የሚዲያውን ቀልብ ይበልጥ የሳበው የሲቪሉ ወገን አመፅ ነበር። በመጀመርያ በየካቲት 11፣ 1966 የሀገሪቱ መምህራን ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ መቱ። «የደሃውን ልጅ በደሃነቱ ለማስቀረት የታለመ ነው» በሚል ፍራቻ የአያሌ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችንና የወላጆችን ድጋፍ ያገኘው ዋና ጥያቄያቸው መንግሥት ተግባራዊ ለማድረግ በዝግጅት ላይ የነበረው «ኤዱኬሽናል ሴክተር ሪቪው» የተሰኘውና ትምህርት ማሻሻያ ይሆናል ተብሎ የተነደፈው ፕሮግራም እንዲታገድ ነበር። በዚያኑ ዕለት ታክሲ ነጂዎች የመካከለኛውን ምሥራቅ ጦርነት ተከትሎ በነዳጅ ዋጋ ላይ ከተደረገው የ50 በመቶ ጭማሪ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የታሪፍ ጭማሪ በመጠየቅ ሥራ አቆሙ። የነሱ አድማ የተማሪዎችና የሥራ አጥ ወጣቶችን ድጋፍ በማግኘቱ ወዲያውኑ ወደ አመፅና ሁከት ተሸጋገረ። የታክሲዎቹ የሥራ ማቆም ስኬታማ እንዲሆን ይመስላል በማናቸውም ተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪዎች ላይ የድንጋይ ናዳ አወረዱበት። በተለይም ናዳው ያነጣጠረው የመንግሥት ንብረትና የታክሲዎች ጣውንት በሆኑት አውቶቡሶችና የምቾትና የድሎት ተምሳሌት በነበሩት እንደ መርቼዴስ ባሉ መኪናዎች ላይ ነበር።

እንዲህ ገንፍሎ የወጣው ሕዝባዊ ቁጣ መለያ ባሕሪው ያልተቀናጀ መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ግዙፍና ሁለንተናዊ በመሆኑ ሥርዓቱን አርበደበደው። በየካቲት 21 በጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ የሚመራው ካቢኔ ከሥራ መሰናበቱም የዚህ የሥርዓቱ መራድ ውጤት ነው። ንጉሠ ነገሥቱም ወዲያውኑ ሥራውን በለቀቀው ካቢኔ ውስጥ የመገናኛ ሚኒስትር የነበረውን ልጅ እንዳልካቸው መኰንንን ጠቅላይ ሚኒስትር አርጎ በመሾም አዲስ

ካቢኔ እንዲመሠርት አዘዘ። እንዳልካቸውም ከቀድሞው ሚኒስትሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ዶክተር ምናሴ ኃይሌን ብቻ ሲያስቀር ካቢኔውን ባዲስ መልክ አቋቋመ። አዲሱ ካቢኔ የመሣፍንቱን ወገን ጊዜያዊ የበላይነት ከማንፀባረቁ ባሻገር እንዳልካቸውን ጨምሮ ሦስት የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ምሩቃን ስለነበሩበት (ሌሎች ሁለቱ የአገር ግዛት ሚኒስትሩ ዶ/ር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴና የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ ልጅ ሚካኤል እምሩ ናቸው) የሕዝቡን ሕሊና የሚስብ ይመስል ነበር። ይሁን እንጂ ሕዝባዊው አመፅ በዚህ የማስታገሻ እርምጃ ከመብረድ ይልቅ ይበልጥ እየሰፋና እየከረረ ሄደ።

ቀደም ብሎ በመግቢያው እንደተገለፀው የሕዝባዊው ንቅናቄ ዓይነተኛ ባሕሪ ሕዳጣን በኃያላን፣ የበታቾች በበላዮች ላይ ብትራቸውን ያነሱበት መሆኑ ነው። ወታደሮችና የበታች መኰንኖች በበላይ መኰንኖች፣ ደሀ በባለጸጋ፣ ሠራተኛ በአሠሪ ላይ ሆ! ብሎ ተነሣ። ወትሮ ማናቸውንም ተቃውሞ ለጥ ፀጥ ያደርጉ የነበሩት የመንግሥቱ የጭቆና አውታሮች መደበኛ ተግባራቸውን ለማከናወን ፍላጎቱም ችሎታውም አልነበራቸውም። ፖሊሶች ሰላማዊ ሰልፍ መበተናቸው ቀረና አብረው መሰለፍ፣ አልያም አጅበው ከግቡ ማድረስ ያዙ። በየካቲት መጨረሻ ላይ ለልማዱ ሥርዓቱን በመፈታተን እምብዛም ያልታወቀው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን አራት ቀን የቆየ ውጤታማ አጠቃላይ የሥራ ማቆም አድማ አደረገ። በዚህን ወቅት ሠራተኞቹ ያነሷቸው ጥያቄዎች ደሞዝ እንዲጨመርላቸው፣ አዲስ የሠራተኛና አሠሪ ሕግ እንዲደነገግና በነፃነት የመደራጀት መብት እንዲከበር ነበር።

ለአያሌ ሳምንታት በቆየው ሕዝባዊ አመፅ ውስጥ ሌላው ጉልህ ሥፍራ የያዘው በሚያዝያ 10 የተካሄደው ከመቶ ሺ በላይ የሚገመት ሕዝብ የተካፈለበት ግዙፍ ሠላማዊ ሰልፍ ነው። ሙስሊሞችና ክርስቲያን ደጋፊዎቻቸው የተሳተፉበት ይህ ሰልፍ የሃይማኖት እኩልነት እንዲሰፍን፣ የመንግሥትና ቤተ ክህነት ቁርኝት እንዲቀርና የሙስሊም በዓላት ብሔራዊ በዓላት ሆነው እንዲከበሩ አበክሮ ጠየቀ። በየሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ከፍተኛ ሹማምንት ከሥራ እንዲባረሩ መጠየቅ የተለመደ ነገር ሆነ፤ አንዳንድ ባለሥልጣናት እስከናካቴው በየቢሮዎቻቸው ለተወሰነ ጊዜ እስከመታሰር ደርሰው ነበር። በዋና ከተማዪቱ የተጀመረው እንቅስቃሴ ወደ ጠቅላይ ግዛቶችም ተዛመተ። በጅማ በሕዝቡ የተመረጠ ኮሚቴ ሙሉ ሥልጣን ጨብጦ በሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻ አትርፎ የነበረውን የንጉሠ ነገሥቱን እንደራሴ ደጃዝማች ፀሐዩ እንቈ ሥላሴን አባረረ። ይህን ተግባሩን በሩሲያ አብዮት ከታየው ሕዝባዊ ልዕልና ጋር በማነፃፀር ግራ ኃይሎች «የጂማ ሶቪየት» ሲሉ አሞካሹት።

የእንዳልካቸው ካቢኔ ይህን ሕዝባዊ ማዕበል ለመግታት ከቶም አልቻለም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ «ፋታ ስጡኝ» እያለ ቢማጠንም ሰሚ አላገኘም። ከግራ ኃይሎች ለዚህ ምልጃ ያገኘው ምላሽ «ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም» የሚል ሆነ። በሌላ አነጋገር፣ በቀድሞውና በአዲሱ ካቢኔ መካከል የቅርፅ እንጂ የይዘት ልዩነት የለም እንደማለት ነው። አዲሱ ካቢኔ የወሰዳቸው አንዳንድ የማሻሻያ እርምጃዎችም የሕዝቡን ቀልብ ከቶም ሊስቡ አልቻሉም። ለምሳሌ፣ ካቢኔው በተሰየመ ጥቂት ቀናት ውስጥ በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ ሕገ መንግሥቱን ለማሻሻል ዕቅድ ነደፈ። በመጋቢት ወር ውስጥ ደግሞ የቀድሞ መንግሥት ሹማምንትን አለአግባብ መበልፀግ አጣርቶ ለፍርድ የሚያቀርብ የምርመራ ኮሚሽን ተቋቋመ። ከዚያም በማስከተል አዲሱ ካቢኔ የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲውን በዝርዝር የሚያብራራ የእንግሊዝ መንግሥትን የአሠራር ዘይቤ ተከትሎ «ነጭ ሰነድ» (White Paper) የተሰኘ መመሪያ ይፋ አደረገ።

ይህ ሁሉ ግን ለእንዳልካቸው የፈለገውን ፋታ ሊያስገኝለት አልቻለም። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ዐቢይ ችግር፣ ምንም እንኳን ራሱንና ካቢኔውን ባዲስ መልክ ለማቅረብ ቢሞክርም፤ የቀድሞ ታሪኩ እስረኛ መሆኑ ነው። ባንድ ወገን ከመሣፍንት ዘር መወለዱና በሌላ ወገን ደግሞ የሥርዓቱ ተዋናይ ስለነበር ከተጠያቂነት ሊያመልጥ አለመቻሉ ለአብዮቱ ጎራ ተቀባይነት የሌለው ሰብዕና ሰጠው። ገና ከመሾሙ በየካቲት 22 ተማሪዎች ተቃውመውት ሰልፍ ወጡ። ከሦስት ቀን በኋላ ደግሞ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ማኅበር የማያወላዳ ሂስ ሰነዘሩበት። ከዚያ ቀጥሎ በሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን የተጠራው ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ በመሠረቱ የሠራተኛውን መብት ለማስከበር የተደረገ ነበር ቢባልም አዲሱን ካቢኔ የመቃወም የፖለቲካ ገፅታም ነበረው። በሠራዊቱም ዘንድ ቢሆን በተለይ በአየር ኃይሉ ክፍል የእንዳልካቸው መንግሥት ብዙም ተቀባይነት አላገኘም።

የተቃውሞው ማዕበል የጎን ውጋት የሆነበት አዲሱ ካቢኔ ይህን ለመቋቋም ኃይልና ዘዴን ያጣመረ ስልትን መረጠ። በሚያዝያ 22 በሱ ግምት የማያባራ ሕገ ወጥ የሆነውን ሕዝባዊ ንቅናቄ ለመግታት «ብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽን» የሚባል አካል አቋቋመ። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ በተለይ ሠራዊቱን በጥቅልም ሆነ በከፊል አባብሎ ከሱ ጎን ለማሰለፍ ልዩ ጥረት አደረገ። ሠራዊቱ በየካቲት ወር ንቅናቄውን ሲጀምር ትግሉን የሚያቀናጅለት ኮሚቴ አቋቁሞ ነበር። ከጊዜ በኋላ፣ የአየር ወለድ ብሪጌድ አዛዥና የእንዳልካቸው ዘመድ የሆነው ኮሎኔል ዓለም ዘውድ ተሰማ በዚህ ኮሚቴ ውስጥ የመሪነት ሥፍራ ለማግኘት ችሎ ነበር። የሠራዊቱን ንቅናቄ ለመቆጣጠር ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህ ምቹ አጋጣሚ ሆነለት። ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲሉ፣ ባንድ በኩል የሠራዊቱን ቁጣ ለማስታገስ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ተቀናቃኞቹን ከአደባባይ ለማራቅ በሚያዝያ ወር ሁለተኛ አጋማሽ ውስጥ በዓለም ዘውድ አማካይነት አያሌ የቀድሞው ካቢኔ ሚኒስትሮችንና ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት ሹማምንትን በቁጥጥር ስር አዋላቸው። እንዳልካቸው ይህን እርምጃ እንዲወስድ ዓለም ዘውድን ሲጠይቅና ንጉሠ ነገሥቱም ሲፈቅድ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀድሞ ባልደረቦቹን፣ ንጉሠ ነገሥቱም የቀድሞ አገልጋዮቹን በመሰዋት ራሳቸውን ለማዳን ያሰቡ ይመስላል። ከጥቂት ወራት በኋላ እንዲህ እንደዋዛ አሳልፈው የሰጧቸውን ሹማምንት እንደሚቀላቀሉ ከቶም አልታሰባቸው።

## አዝጋሚው መፈንቅለ መንግሥት

እንዲህ ከሥሩ የተናጋው ሥርዓት፣ በመስከረም 1967 የሥርዓቱ ቁንጮ የነበረው ንጉሠ ነገሥት ከሥልጣን ሲወርድ ግብዓተ መሬቱ ተፈጸመ። ያ እስከሆነ ድረስ ግን በተለይም በመጨረሻው ሁለት ወራት ሥርዓቱ ስልታዊ ቡርቦራና ሸርሸራ ተካሄደበት። የዚህ ሸርሸራ ግንባር ቀደም ተዋናይም በታሪክ «ደርግ» እየተባለ ሲታወቅ የኖረው ከሠራዊቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች የተውጣጣው



6.1 ደርግ ልደቱን ያገኘበት አራተኛ ክፍለ ጦር ውስጥ የሚገኘው ሕንፃ

ኮሚቴ ነው:: የዚህ ኮሚቴ ቅድመ ታሪክ እምብዛም ጠርቶ የወጣ ባይሆንም፣ አጠቃላይ ገፅታው ግን የሚከተለውን ይመስላል:: ከየካቲት 66 እስከ ሰኔ መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ ይህ ወታደራዊ ኮሚቴ በሦስት መልክ እንደተከሰተ ይነገራል:: የመጀመርያው በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ ከደሞዝ ጭማሪ አንስቶ እስከ አጠቃላይ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ለውጥ ድረስ ይጠይቁ የነበሩትን የሠራዊቱ የተለያዩ ክፍሎች ትግል ለማስተባበር የተቋቋመው ኮሚቴ ነው:: ሁለተኛው የዚህ ኮሚቴ የታሪክ ምዕራፍ ደግሞ፣ በኮሎኔል ዓለም ዘውድ መዳፍ ስር ወድቆ ሕዝባዊ ዓላማ የነበረው ንቅናቄ የእንዳልካቸውን ካቢኔ ዕድሜ ለማራዘምና ሥልጣኑንም ለማደላደል እንዲያገለግል የተደረገውን ሙከራ ያመለክታል::

ከነዚህ ሁሉ ዘላቂ ውጤት ለማምጣትና የማታ ማታም ሥልጣን ላይ ለመደላደል የቻለው ግን በሰኔ 21 ቀን 1966 የተመሠረተውና «የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና የሕዝባዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ» በሚል ስያሜ ይፋ የወጣው ሦስተኛው ኮሚቴ ነው:: ይህ ቡድን ይበልጥ በታሪክ የታወቀው ግን «ደርግ» በሚለው መጠርያ ነው:: ቢያንስ የዚህ የሦስተኛው ኮሚቴ ሐሳብ በሚብላላበት ወቅት ሻለቃ ተፈራ ተክለአብ የሚባል የጦር ሠራዊት መሐንዲስ መምሪያ መኰንን ግንባር ቀደም ሚና እንደተጫወተ ይነገርለታል:: የኋላ ኋላ ግን አስተሳሰቡ ከሌሎች ጓዶቹ አመለካከት እየተለፈነጠረ ስላስቸገራቸው ያገለሉት ይመስላል:: ከመጀመርያው ኮሚቴ አንስቶ እስከ ሦስተኛው ኮሚቴ ልደት ድረስ ተዋናይ የነበረው ሌላ መኰንን ደግሞ አራተኛ ክፍለ ጦርን ወክሎ የቀረበው ሻለቃ አጥናፉ አባተ ነበር:: ምናልባትም መጀመርያ ላይ አጥናፉ የደርግ ሊቀ መንበር ሆኖ ሲመራ ቆይቶ፣ ሰኔ 21 ደርጉ ተሟልቶ በተቋቋመበት ወቅት የሊቀ



መንበርነቱን ሥፍራ የሐረሩን ሦስተኛ ክፍለ ጦር ወክሎ ለመጣው ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በመልቀቅ እሱ የምክትል ሊቀ መንበርነቱን ሥፍራ የያዘ ይመስላል:: ኋላ ግን፣ ደርግ አደባባይ የሚወጣበት ግርማ ሞገስ ያለው የከፍተኛ መኰንን ስም አስፈልጎት ሌተና ጄኔራል አማን አንዶምን ሊቀ መንበር አድርጎ፣ መንግሥቱንና አጥናፉን በማሽጋሸግ ተቀዳሚና ሁለተኛ ሊቀ መንበር ለማድረግ ተገዷል::

በተለምዶ ሁሉም ይጠቀምበት ለነበረው፣ ነገር ግን ባዕድ ለሆነው «ኮሚቴ» ሊሚለው ቃል ሀገራዊ ምትክ እንዲሆን ታስቦ ጥቅም ላይ የዋለው «ደርግ» ልክ እንደ «አብዮት» ዘመኑ የወለደው ቃል ነው:: ሁለቱም የጥንታዊውን የግዕዝ ቋንቋ በማጣቀስ የተቀመሙ ናቸው:: «ደርግ» የሚለው ቃል አዲስ ይሁን እንጂ ወታደሮች በፖለቲካ ጣልቃ በመግባት ሁኔታዎችን ለመለወጥ መሞከራቸው እንዳንዴም መቻላቸው ግን አዲስ አልነበረም:: በተለይም ቤተ መንግሥት አካባቢ የሚገኙ ወታደራዊ ኃይሎች ነገሥታትን በማንገሥና ከዙፋን በማውረድ ወሳኝ ሚና ከመጫወትም አልፈው፣ በየጁ መሳፍንት እንዳየነው የራሳቸውን ሥርወ መንግሥት እስከ መመስረት ደርሰዋል:: በሃያኛው መቶ ዓመት መጀመርያ አሥርት ዓመታትም መሐል ሰፋሪ በመባል የሚታወቀው ከቤተ መንግሥቱ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ጦር ካንዴም ሦስቴ (በ1902፣ በ1909 እና በ1910) የፖለቲካ ሹም ሽር በማምጣት ግንባር ቀደም ሚና እንደተጫወተ ቀደም ሲል ተመልክተናል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ የቅርብ ጊዜ ትዝታ የነበረው፣ በክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ በብርጋዲየር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የተመራውና የከሸፈው የ1953 መፈንቅለ መንግሥት ነበር::

ምናልባትም ከሁሉም በላይ በደርግ አባላቱ ሕሊና ውስጥ ጉልህ ሥፍራ የነበረው ይኸው የ1953ቱ የመንግሥት ለውጥ ሙከራ ሳይሆን አይቀርም:: መሠረታዊ ለውጥ ላይ ባነጣጠረው ሕዝባዊ ንቅናቄና «ሕግና ሥርዓትን» ለማስፈን በሚጣጣሩት ኃይሎች መካከል ተወጥሮ የነበረው ደርግ ዐቢይ ፕረትና ስጋት የ1953ቱ ለውጥ ፈላጊዎች ዕጣ እንዳይደርስበት ነበር:: ስለሆነም የማይገሰስና የማይደፈር ይመስል የነበረውን ዐፄያዊ ሥልጣን ለመናድ በዘዴና በጥንቃቄ መራመድ ነበረበት:: በበትረ መንግሥቱ ላይ ቁጥጥራቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጠበቁ በሄዱ መጠን፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ያላቸውን ፅኑ ታማኝነት በሚያማልል ቋንቋ ይገልፁ ነበር:: ለዚህም ነው ንጉሠ ነገሥቱን ከሥልጣን ለማውረድ ለተጠቀሙበት ዝግ ያለ ግን ስልት የተሞላበት አካሄድ «አዝጋሚው መፈንቅለ መንግሥት» የሚል ስያሜ የተሰጠው::

የተለያዩ ምንጮች እንደሚጠቁሙት ደርግ በመጀመርያ በዋና ከተማዪቱና አካባቢዋ የሚገኙ መለዮ ለባሾችን የወከሉ መኰንኖች ያቋቋሙት ኮሚቴ ነበር:: ኋላ ግን አገር አቀፍ ይዘት እንዲኖረው በመፈለጉ በሀገሪቱ የሚገኙ አርባ የጦር ክፍሎች ሦስት ሦስት ተወካዮች እንዲልኩ ተደርጎ እንዲህ ተስፋፍቶ የተዋቀረው ኮሚቴ ሥራውን ሰኔ 21 ቀን ጀመረ:: ይህንኑ ስሌት ተከትሎ በተለምዶ መቶ ሃያ የደርግ አባላት እየተባለ ይነገር እንጂ እውነተኛ ቁጥራቸው ከመቶ አሥር በልጦ አያውቅም:: ይህም የሆነበት ምክንያት አንዳንድ የጦር ክፍሎች ተወካዮች አሟልተው ባለመላካቸው ይመስላል:: እንዲህ በምርጫ መሰል ሂደት የተዋቀረ በመሆኑም ደርግ የወታደራዊ ፓርላማ ባሕሪ ነበረው:: ከመደበኛ ፓርላማ የሚለየው ግን ወታደሮቹ እንዴ ወኪሎቻቸውን ከመረጡ



6.1 ደርግ ልደቱን ያገኘበት አራተኛ ክፍለ ጦር ውስጥ የሚገኘው ሕንፃ

ኮሚቴ ነው፡፡ የዚህ ኮሚቴ ቅድመ ታሪክ እምብዛም ጠርቶ የወጣ ባይሆንም፣ አጠቃላይ ገፅታው ግን የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ከየካቲት 66 እስከ ሰኔ መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ ይህ ወታደራዊ ኮሚቴ በሦስት መልክ እንደተከሰተ ይነገራል፡፡ የመጀመርያው በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ ከደሞዝ ጭማሪ አንስቶ እስከ አጠቃላይ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ለውጥ ድረስ ይጠይቁ የነበሩትን የሠራዊቱ የተለያዩ ክፍሎች ትግል ለማስተባበር የተቋቋመው ኮሚቴ ነው፡፡ ሁለተኛው የዚህ ኮሚቴ የታሪክ ምዕራፍ ደግሞ፣ በኮሎኔል ዓለም ዘውድ መዳፍ ስር ወድቆ ሕዝባዊ ዓላማ የነበረው ንቅናቄ የእንዳልካቸውን ካቢኔ ዕድሜ ለማራዘምና ሥልጣኑንም ለማደላደል እንዲያገለግል የተደረገውን ሙከራ ያመለክታል፡፡

ከነዚህ ሁሉ ዘላቂ ውጤት ለማምጣትና የማታ ማታም ሥልጣን ላይ ለመደላደል የቻለው ግን በሰኔ 21 ቀን 1966 የተመሠረተውና «የጦር ኃይሎች፣ የፖሊስና የሕዝባዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ» በሚል ስያሜ ይፋ የወጣው ሦስተኛው ኮሚቴ ነው፡፡ ይህ ቡድን ይበልጥ በታሪክ የታወቀው ግን «ደርግ» በሚለው መጠርያ ነው፡፡ ቢያንስ የዚህ የሦስተኛው ኮሚቴ ሐሳብ በሚብላላበት ወቅት ሻለቃ ተፈራ ተክለአብ የሚባል የጦር ሠራዊት መሐንዲስ መምሪያ መኰንን ግንባር ቀደም ሚና እንደተጫወተ ይነገርለታል፡፡ የኋላ ኋላ ግን አስተሳሰቡ ከሌሎች ጓዶቹ አመለካከት እየተስፈነጠረ ስላስቸገራቸው ያገለሉት ይመስላል፡፡ ከመጀመርያው ኮሚቴ አንስቶ እስከ ሦስተኛው ኮሚቴ ልደት ድረስ ተዋናይ የነበረው ሌላ መኰንን ደግሞ አራተኛ ክፍለ ጦርን ወክሎ የቀረበው ሻለቃ አጥናፉ አባተ ነበር፡፡ ምናልባትም መጀመርያ ላይ አጥናፉ የደርግ ሊቀ መንበር ሆኖ ሲመራ ቆይቶ፤ ሰኔ 21 ደርጉ ተሟልቶ በተቋቋመበት ወቅት የሊቀ



መንበርነቱን ሥፍራ የሐረሩን ሦስተኛ ክፍለ ጦር ወክሎ ለመጣው ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በመልቀቅ እሱ የምክትል ሊቀ መንበርነቱን ሥፍራ የያዘ ይመስላል፡፡ ኋላ ግን፣ ደርግ አደባባይ የሚወጣበት ግርማ ሞገስ ያለው የከፍተኛ መኰንን ስም አስፈልጎት ሌተና ጄኔራል አማን አንዶምን ሊቀ መንበር አድርጎ፣ መንግሥቱንና አጥናፉን በማሸጋሸግ ተቀዳሚና ሁለተኛ ሊቀ መንበር ለማድረግ ተገዷል፡፡

በተለምዶ ሁሉም ይጠቀምበት ለነበረው፣ ነገር ግን ባዕድ ለሆነው «ኮሚቴ» ሊሚለው ቃል ሀገራዊ ምትክ እንዲሆን ታስቦ ጥቅም ላይ የዋለው «ደርግ» ልክ እንደ «አብዮት» ዘመኑ የወለደው ቃል ነው፡፡ ሁለቱም የጥንታዊውን የግዕዝ ቋንቋ በማጣቀስ የተቀመሙ ናቸው፡፡ «ደርግ» የሚለው ቃል አዲስ ይሁን እንጂ ወታደሮች በፖለቲካ ጣልቃ በመግባት ሁኔታዎችን ለመለወጥ መሞከራቸው አንዳንዴም መቻላቸው ግን አዲስ አልነበረም፡፡ በተለይም ቤተ መንግሥት አካባቢ የሚገኙ ወታደራዊ ኃይሎች ነገሥታትን በማንገሥና ከዙፋን በማውረድ ወሳኝ ሚና ከመጫወትም አልፈው፣ በየጁ መሳፍንት እንዳየነው የራሳቸውን ሥርወ መንግሥት እስከ መመስረት ደርሰዋል፡፡ በሃያኛው መቶ ዓመት መጀመርያ አሠርት ዓመታትም መሐል ሰፋሪ በመባል የሚታወቀው ከቤተ መንግሥቱ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ጦር ካንዴም ሦስቴ (በ1902፣ በ1909 እና በ1910) የፖለቲካ ሹም ሽር በማምጣት ግንባር ቀደም ሚና እንደተጫወተ ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የቅርብ ጊዜ ትዝታ የነበረው፣ በክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ በብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የተመራውና የከሸፈው የ1953 መፈንቅለ መንግሥት ነበር፡፡

ምናልባትም ከሁሉም በላይ በደርግ አባላቱ ሕሊና ውስጥ ጉልህ ሥፍራ የነበረው ይኸው የ1953ቱ የመንግሥት ለውጥ ሙከራ ሳይሆን አይቀርም፡፡ መሠረታዊ ለውጥ ላይ ባነጣጠረው ሕዝባዊ ንቅናቄና «ሕግና ሥርዓትን» ለማስፈን በሚጣጣሩት ኃይሎች መካከል ተወጥሮ የነበረው ደርግ ዐቢይ ጥረትና ስጋት የ1953ቱ ለውጥ ፈላጊዎች ዕጣ እንዳይደርስበት ነበር፡፡ ስለሆነም የማይገሰስና የማይደፈር ይመስል የነበረውን ዐፄያዊ ሥልጣን ለመናድ በዘዴና በጥንቃቄ መራመድ ነበረበት፡፡ በበትረ መንግሥቱ ላይ ቁጥጥራቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጠበቁ በሄዱ መጠን፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ያላቸውን ፅኑ ታማኝነት በሚያማልል ቋንቋ ይገልፁ ነበር፡፡ ለዚህም ነው ንጉሠ ነገሥቱን ከሥልጣን ለማውረድ ለተጠቀሙበት ዝግ ያለ ግን ስልት የተሞላበት አካሄድ «አዝጋሚው መፈንቅለ መንግሥት» የሚል ስያሜ የተሰጠው፡፡

የተለያዩ ምንጮች እንደሚጠቁሙት ደርግ በመጀመርያ በዋና ከተማዪቱና አካባቢዋ የሚገኙ መለዮ ለባሾችን የወከሉ መኰንኖች ያቋቋሙት ኮሚቴ ነበር፡፡ ኋላ ግን አገር አቀፍ ይዘት እንዲኖረው በመፈለጉ በሀገሪቱ የሚገኙ አርባ የጦር ክፍሎች ሦስት ሦስት ተወካዮች እንዲልኩ ተደርጎ እንዲህ ተስፋፍቶ የተዋቀረው ኮሚቴ ሥራውን ሰኔ 21 ቀን ጀመረ፡፡ ይህንኑ ስሌት ተከትሎ በተለምዶ መቶ ሃያ የደርግ አባላት እየተባለ ይነገር እንጂ እውነተኛ ቁጥራቸው ከመቶ አሥር በልጦ አያውቅም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አንዳንድ የጦር ክፍሎች ተወካዮች አሟልተው ባለመላካቸው ይመስላል፡፡ እንዲህ በምርጫ መሰል ሂደት የተዋቀረ በመሆኑም ደርግ የወታደራዊ ፓርላማ ባሕሪ ነበረው፡፡ ከመደበኛ ፓርላማ የሚለየው ግን ወታደሮቹ እንደ ወኪሎቻቸውን ከመረጡ



6.2 አፄ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ከወረደ በኋላ፣ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር እስር ቤት ወደ ወሰደችው ታሪካዊ ቮልስ ቫገን መኪና ሲያመራ

የታሰበ ነበር:: በተለይም «የምንወደውና የሚወደን ሕዝባችን» የሚለውን ንጉሣዊ ዘይቤ ለመናድ የታለመ ነበር:: እንደታሰበውም የፕሮፓጋንዳው ቅንብር ግቡን ስለመታ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚያዝንለት ጠፍቶ «ይውረድ!» የሚለው በረከተ::

መስከረም 2 1967 ጠዋትም፣ የደርግ ተወካዮች ብሔራዊ ቤተ መንግሥት በመሄድ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ከዙፋን እንዲወርድ መወሰኑን አርድተው ወደተሰናዳለት ሥፍራ እንዲሄድ ጋበዙት:: የውርደቱን ልክ ለማሳየት ይሁን ወይ ከሕዝብ ቁጣ ለመሰወር እንደሆነ አይታወቅም፣ በቮልስዋገን መኪና አስገፈው የደርጉ መካነ ልደት ወደሆነው ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ወሰዱት:: ያቺ ቅፅበት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በርዝመቱም ሆነ ሀገሪቱ ባየችው ለውጥ ብዙም ወደር የማይገኝለትን የንጉሥ ዘመን ማክተም ብቻ የምታመላክት ሳይሆን ሥረ መሠረቱን ከንጉሥ ሰለሞንና ንግሥተ ሳባ ጋር የሚያጣቅሰውን «ሰለሞናዊ» ሥርወ መንግሥትን ፍጻሜም ጭምር ነው::

## ወታደራዊ አገዛዝና ባላንጣዎቹ

የአብዮቱ ተምሳሌት የሆነው መስከረም 2፣ 1967 ሁለት ተቃራኒ ገፅታዎች ነበሩት:: ባንድ ወገን ንጉሣዊ አገዛዝን አስወግዶ ሕዝቡን ነፃ ያወጣ ሲመስል በሌላ ወገን ደግሞ አዲስና ከፊተኛው ያልተናነሰ አምባገነን አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ተጫነበት:: በዕለቱ ሥልጣን የጨበጠውና ራሱን «የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ» ብሎ የሰየመው መንግሥት መጀመርያ የወሰደው እርምጃ አዲሱን ሕገ መንግሥት ማገድ፣ ፓርላማን መበተንና ማናቸውንም ዓይነት ሰላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም አድማን መከልከል ነበር:: ዓላማ ጠቋሚ የነበረው «ኢትዮጵያ ትቅደም» የሚለው መፈክርም ወደ እምነትነት ተሸጋገረ:: እሱን መቃወምም ታላቅ ወንጀል ሆኖ ተፈረጀ:: አብዮታዊው ንቅናቄ የወለደው ደርግ ሥልጣኑን ለማደላደል ሲል ወላጁን ካደ:: በዚህም፣ በየካቲት 66ቱ ሕዝባዊ አመፅ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና ከነበራቸው ተማሪዎችና መምህራን ጋር የከረረ ቅራኔ ውስጥ ገባ:: ደርግና ደጋፊዎቹ መስከረም ሁለትን የሕዝባዊው ንቅናቄ ማሳረጊያ ብለው በየዓመቱ ሲያከብሩት፣ ተቃዋሚዎቹ ግን አብዮቱ ሀዲዱን የሳተበት ቀን ብለው ዘከሩት::

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን መቋቋም ከሲቪሉ ወገን በብርቱ የተቃወሙት ተማሪዎች፣ «ፎረም» በመባል የሚታወቀው ግራ ዘመም የሆነው የዩኒቨርሲቲ መምህራን ቡድን፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን፣ «ዴሞክራሲያ»ና «የሰፊው ሕዝብ ድምፅ» በሚባሉት መጽሔቶች ዙሪያ የተሰባሰቡት ኅቡዕ የግራ ክንፍ ድርጅቶች ሲሆኑ፤ ከወታደሩ ክፍል ደግሞ የመሐንዲስ ክፍል፣ ክቡር ዘበኛና የወታደር የበረራ ክፍል («አርሚ አቪየሽን») ይገኙበታል:: እነዚህ ተቃዋሚዎች እንደ አማራጭ ያቀረቡትም የ«ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» መቋቋምን ነበር::

ይህ ሁለት ዓመት ያህል ገኖ የቆየ መፈክር መጀመርያ የተወረወረው የእንዳልካቸው ካቢኔ በተቋቋመበት ወቅት ነበር:: በዚያን ወቅት ግራ ክንፍ ኃይሎች ሕዝቡ የሚፈልገውና የሚጠብቀው የካቢኔ ሹም ሽር (ወይም «ጉልቻ መቀያየር») ሳይሆን መሠረታዊ ለውጥ ነው በማለት «ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም» የሚለውን መፈክር ባማራጭነት አቀረቡ:: ሆኖም እነዚሁ ኃይሎች እውነተኛ ሕዝባዊ መንግሥት ማቋቋም ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ስለተረዱ ይመስላል፣ በወቅቱ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» ነው በማለት መፈክራቸውን አስተካከሉ:: መፈክሩን በመሰንዝር ብቻ ሳይገታ ይዘቱንም በሐምሌ ወር ለደርግ በፃፈው ደብዳቤ አብራርቶ ያቀረበው የ«ፎረም» ቡድን ነበር:: ይሁን እንጂ የመፈክሩ ደጋፊዎች ስለይዘቱ ሙሉ ስምምነት ነበራቸው ብሎ ለመናገር ያዳግታል:: አንዳንዴ ከሠራተኞች፣ ተማሪዎች፣ መምህራንና ገበሬዎች የሚውጣጣ መንግሥት ሆኖ ሲቀርብ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የየካቲት 66 ሕዝባዊ ንቅናቄ በወለዳቸው ኮሚቴዎችና ድርጅቶች ላይ የሚመሠረት ሆኖ ይቀርብ ነበር::

ውሎ አድሮ ይህ የ«ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» መፈክር የሁለቱ ግንባር ቀደም የግራ ክንፍ ቡድኖች፣ ማለትም «ዴሞክራሲያ» እና «የሠፊው ሕዝብ ድምፅ» በተሰኙት ህቡዕ ጋዜጦች ዙርያ የተደራጁት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እና የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)፣ ዋነኛ የፍልሚያ ምክንያት እንደሆነ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ በመጀመርያዎቹ ወራቶች ሁለቱም ቡድኖች የመፈክሩ አራማጆች ነበሩ:: እንዲያውም ንጉሠ ነገሥቱ ከዙፋን ከመውረዱ ከሁለት ቀናት በፊት የወጣው «የሠፊው ሕዝብ ድምፅ» በወታደር የሚመራ መንግሥት፣ የፈለገውን ያህል ቅን ልቦና ቢኖረው፣ ዞሮ ዞሮ አገሪቷን ባንድ አምባገነን መሪ መዳፍ ሥር ይጥላታል ሲል ትንቢታዊ ትንተና አቅርቦ ነበር::



6.2 እቴ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ከወረደ በኋላ፣ ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር እስር ቤት ወደ ወሰደችው ታሪካዊ ቮልስ ቫገን መኪና ሲያመራ

የታሰበ ነበር። በተለይም «የምንወደውና የሚወደን ሕዝባችን» የሚለውን ንጉሣዊ ዘይቤ ለመናድ የታለመ ነበር። እንደታሰበውም የፕሮፓጋንዳው ቅንብር ግቡን ስለመታ፣ ለንጉሡ ነገሥቱ የሚያዝንለት ጠፍቶ «ይውረድ!» የሚለው በረከተ።

መስከረም 2 1967 ጠዋትም፣ የደርግ ተወካዮች ብሔራዊ ቤተ መንግሥት በመሄድ፣ ንጉሡ ነገሥቱን ከዙፋን እንዲወርድ መወሰኑን አርድተው ወደተሰናዳለት ሥፍራ እንዲሄድ ጋበዙት። የውርደቱን ልክ ለማሳየት ይሁን ወይ ከሕዝብ ቁጣ ለመሰወር እንደሆነ አይታወቅም፣ በቮልስዋገን መኪና አክንፈው የደርጉ መካነ ልደት ወደሆነው ወደ አራተኛ ክፍለ ጦር ወሰዱት። ያቺ ቅፅበት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በርዝመቱም ሆነ ሀገሪቱ ባየችው ለውጥ ብዙም ወደር የማይገኝለትን የንጉሥ ዘመን ማክተም ብቻ የምታመላክት ሳይሆን ሥረ መሠረቱን ከንጉሥ ሰለሞንና ንግሥተ ሳባ ጋር የሚያጣቅሰውን «ሰለሞናዊ» ሥርወ መንግሥትን ፍጻሜም ጭምር ነው።

## ወታደራዊ አገዛዝና ባላንጣዎቹ

የአብዮቱ ተምሳሌት የሆነው መስከረም 2፣ 1967 ሁለት ተቃራኒ ገፅታዎች ነበሩት። ባንድ ወገን ንጉሣዊ አገዛዝን አስወግዶ ሕዝቡን ነፃ ያወጣ ሲመስል በሌላ ወገን ደግሞ አዲስና ከፊተኛው ያልተናነሰ አምባገነን አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ተጫነበት። በዕለቱ ሥልጣን የጨበጠውና ራሱን «የጊዜያዊ ወታደራዊ




አስተዳደር ደርግ» ብሎ የሰየመው መንግሥት መጀመርያ የወሰደው እር[ምጃ] አዲሱን ሕገ መንግሥት ማገድ፣ ፓርላማን መበተንና ማናቸውንም ዓ[መ]ፅ [...]ነት ሰላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም አድማን መከልከል ነበር። ዓላማ [...]ነት የነበረው «ኢትዮጵያ ትቅደም» የሚለው መፈክርም ወደ እምነትነት ተሸጋ[ገረ]። እሱን መቃወምም ታላቅ ወንጀል ሆኖ ተፈረጀ። አብዮታዊው ንቅናቄ የወለ[ደው] ደርግ ሥልጣኑን ለማደላደል ሲል ወላጁን ካደ። በዚህም፣ በየካቲት [...]ው ሕዝባዊ አመፅ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና ከነበራቸው ተማሪዎችና መም[ህራን] ጋር የከረረ ቅራኔ ውስጥ ገባ። ደርግና ደጋፊዎቹ መስከረም ሁለትን የሕዝባ[ዊ] ንቅናቄ ማሳረጊያ ብለው በየዓመቱ ሲያከብሩት፣ ተቃዋሚዎቹ ግን አብ[ዮ]ቱ ሀዲዱን የሳተበት ቀን ብለው ዘከሩት።

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን መቋቋም ከሲቪሉ ወገን [...] የተቃወሙት ተማሪዎች፣ «ፎረም» በመባል የሚታወቀው ግራ ዘመም [...] የዩኒቨርሲቲ መምህራን ቡድን፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬ[ሽን]፣ «ዴሞክራሲያ»ና «የሰፊው ሕዝብ ድምፅ» በሚባሉት መጽሔቶች [...] የተሰባሰቡት ኅቡዕ የግራ ክንፍ ድርጅቶች ሲሆኑ፣ ከወታደሩ ክፍል [...] የመሐንዲስ ክፍል፣ ክቡር ዘበኛና የወታደር የበረራ ክፍል («አርሚ አቪየ[ሽን]») ይገኙበታል። እነዚህ ተቃዋሚዎች እንደ አማራጭ ያቀረቡትም የ«ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» መቋቋምን ነበር።

ይህ ሁለት ዓመት ያህል ገኖ የቆየ መፈክር መጀመርያ የተወረ[ወ]ረው የእንዳልካቸው ካቢኔ በተቋቋመበት ወቅት ነበር። በዚያን ወቅት ግራ [ክ]ንፍ ኃይሎች ሕዝቡ የሚፈልገውና የሚጠብቀው የካቢኔ ሹም ሽር (ወይም «[...]» መቀያየር») ሳይሆን መሠረታዊ ለውጥ ነው በማለት «ሕዝባዊ መንግ[ሥት] ይቋቋም» የሚለውን መፈክር ባማራጭነት አቀረቡ። ሆኖም እነዚሁ ኃይ[ሎ]ች እውነተኛ ሕዝባዊ መንግሥት ማቋቋም ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ስለ[ተረዱ] ይመስላል፣ በወቅቱ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችለው «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» ነው በማለት መፈክራቸውን አስተካከሉ። መፈክሩን በመሰንዘር [...] ሳይገታ ይዘቱንም በሐምሌ ወር ለደርግ በጻፈው ደብዳቤ አብራርቶ ያቀ[ረ]ብ[ው] የ«ፎረም» ቡድን ነበር። ይሁን እንጂ የመፈክሩ ደጋፊዎች ስለይዘቱ [...]ው ስምምነት ነበራቸው ብሎ ለመናገር ያዳግታል። አንዳንዶ ከሠራተኞ[ች] [...] ተማሪዎች፣ መምህራንና ገበሬዎች የሚውጣጣ መንግሥት ሆኖ ሲቀርብ፣ [...] ጊዜ ደግሞ የየካቲት 66 ሕዝባዊ ንቅናቄ በወለዳቸው ኮሚቴዎችና ድርጅቶች ላይ የሚመሠረት ሆኖ ይቀርብ ነበር።

ውሎ አድሮ ይህ የ«ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» መፈክር የ[...] ግንባር ቀደም የግራ ክንፍ ቡድኖች፣ ማለትም «ዴሞክራሲያ» እና «የሠ[ፊ]ው ሕዝብ ድምፅ» በተሰኙት ህቡዕ ጋዜጦች ዙርያ የተደራጁት የኢትዮጵያ [ሕ]ዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እና የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ዋነኛ የፍልሚያ ምክንያት እንደሆነ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በመጀመርያ [...] ወራቶች ሁለቱም ቡድኖች የመፈክሩ አራማጆች ነበሩ። እንዲያውም [...] ነገሥቱ ከዙፋን ከመውረዱ ከሁለት ቀናት በፊት የወጣው «የሠፊው ሕዝብ ድምፅ» በወታደር የሚመራ መንግሥት፣ የፈለገውን ያህል ቅን ልቦና ቢኖረው፣ ዞሮ ዞሮ አገሪቷን ባንድ አምባገነን መሪ መዳፍ ሥር ይጥላታል ሲል ትን[ቢ]ታዊ ትንተና አቅርቦ ነበር።

በኋላ በነሱ ላይ ሥልጣን አልባ መሆናቸው ነው። በሌላ አነጋገር፣ ወኪሎቻቸው የሚያደርጉት ነገር ካልጣማቸው ተመልሱ ለማለት ወይም እንደገና ለመምረጥ ምንም ኃይል ወይም ዕድል አልነበራቸውም። ይህም በቀንደኛው የደርግ አባል በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ታይቷል። በደርግ ውስጥ የነበረው ሥልጣን እየገነነና የሚወስዳቸውም እርምጃዎች እየከረሩ ሲሄዱ መጀመርያ የወከለው የሐረሩ ሦስተኛ ክፍለ ጦር ወደ ክፍለ ጦሩ እንዲመለስ ጥሪ ቢያደርግለትም፤ ደርግ ሊቀ መንበር አርጎ ከባድ ኃላፊነት ስለሰጠኝ ይህን አደራ ትቼ አልመለስም ብሎ አሻፈረኝ አለ። እንዲመለስ ለማስገደድ እስቦ ጦሩ ቤተ ሰቡን ቢያግትበትም ሽለቃው ከዓላማው ንቅንቅ አላለም።

ሌላው የደርግ መለያ ባሕሪ ከፍተኛ መኰንኖች ከአሮጌው ሥርዓት ጋር በቅርብ የተሳሰሩ ናቸው ተብሎ በመታሰባቸው፣ ከሻለቃ ያለፈ መኰንን አባል እንዳይሆን መደረጉ ነው። ስለሆነም ሃምሳ የሚሆኑት የደርግ አባላት ከመቶ ዓለቃ እስከ ሻለቃ የሚደርሱ መኰንኖች ሲሆኑ፣ የቀሩት ተራ ወታደሮችና ባለሌላ ማዕረጎች ነበሩ። ይሁን እንጂ፣ ብዙም ሳይቆዩ በሕዝብ ዘንድ ምንም ዓይነት እውቀትና ዝና የሌላቸው ዝቅተኛ መኰንኖች ለውጡን በግንባር መምራቱ እያስፈራቸው ስለመጣ፤ ሕዝብ ፊት የሚቀርቡበት የታዋቂ ከፍተኛ መኰንን ሽፋንና ጋሻ አስፈለጋቸው። ለዚህም ተግባር የመረጡት በሠራዊቱ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት የነበረውን ሌተናንት ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን ነበር። በደርጉ ጥያቄና ድጋፍም ጄኔራሉ መጀመርያ የጦር ኃይሎች ኤታ ማጆር ሹም፣ ቀጥሎ የመከላከያ ሚኒስትር፣ በመጨረሻም የደርግ ሊቀ መንበር (የሕዝብ ግንኙነት መኰንን ማለቱ ይበልጥ ወደ እውነቱ የተጠጋ ሳይሆን አይቀርም) ሆኖ ተሾመ።

የደርግ የመጨረሻ ግብ በትረ መንግሥቱን መጨበጥ ቢሆንም፣ ንጉሠ ነገሥቱን ከሥልጣን ለማግለል የተጠቀመበት ስልት የኃይልና የድፍረት ሳይሆን የትሕትናና የማዋዛት ነበር። ለንጉሠ ነገሥቱ መጀመርያ ያቀረባቸው ጥያቄዎችም፣ ለፖለቲካ እስረኞችና ስደተኞች አጠቃላይ ምህረት ማወጅ፣ የተረቀቀውን አዲስ ሕገ መንግሥት ባፋጣኝ በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ እና ለዚሁም ይረዳ ዘንድ ፓርላማ እንደ ወትሮው ለክረምት መዘጋቱ ቀርቶ በዚሁ ላይ እንዲመክር ነበር። ይህን ሁሉ ጥያቄ ሲያቀርቡ ለንጉሠ ነገሥቱ ያላቸውን ታማኝነትና ላሳየውም ከፍተኛ አመራር አድናቆታቸውን በሰፊው እየገለፁ ነበር። ስለዚህም ይሆናል ንጉሠ ነገሥቱ የደርጉን ጥያቄ ለመቀበል ብዙ ጊዜም ያልወሰደበት። ይሁን እንጂ ይህ አዎንታዊ መልስ ደርግን ማስታገሱ ቀርቶ ሌሎች ተከታታይ እርምጃዎች እንዲወስድ አደፋፈረው። ከነዚህም እርምጃዎች ዋነኛውና የደርጉን የወደፊት አቅጣጫ የጠቆመው በመካኼድ ላይ ላለው ለውጥ እንቅፋት ይሆናሉ ብሎ የገመታቸውን ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትንና የመሣፍንቱን አባላት ማሰር ነው። ሠራዊት ያዘምታሉ፣ ከፍተኛ ችግር ያደርሳሉ ተብለው ይፈሩ የነበሩት ኃያላን ባብዛኛው ምንም ሳያንገራግሩ እጃቸውን ሰጡ።

ይህ ሁሉ ሲሆን፣ የደርግ ዓላማና የወደፊት አቅጣጫ ምን እንደሆነ ሕዝቡ ግር ሳይለው አልቀረም። ይህን ጥያቄ ለመመለስም ይመስላል ደርግ የሚከተለው መርህ «ኢትዮጵያ ትቅደም!» የሚለው መሆኑን ከጥልቅ ይዘት ይልቅ በቃለ አጋኖ በታጀቡ ተከታታይ መግለጫዎች አወጀ። በሀገሪቱ የተነሳሳው የለውጥ ስሜትም ፈርጠም ያለ ጡንቻ ያለውን ወታደራዊ ንቅናቄ እንደ አጋዥ



ኃይል ስለቆጠረው፤ የለውጥ ጥቆማዎች ደርግ ለዚሁ ብሎ ያስቀመጣቸውን የሐሳብ መስጫ ሳጥኖች ሞሏቸው። ደርግም በነሐሴ መጨረሻ ላይ፣ አንድም ይህንኑ ጡንቻ ለማሳየት፣ አንድም የሕዝቡን ስሜት ለመፈተሽ፤ «ኢትዮጵያ ትቅደም» የሚለውን አርማውን እያመላከተ በአዲስ አበባ ዋና ዋና ጎዳናዎች ላይ በወታደር መኪና ሰልፍ አደረገ።

በዚህ ሁኔታ የመንግሥት ሥልጣን የእንዳልካቸው ካቢኔና ደርግ የሚጋሩት የመንትዮሽ ባህሪ ያላት ሆና አንድ ወር ግድም ቆየች። የጋርዮሽ አስተዳደሩን የተቀናጀ መልክ እንዲሰጠው ታስቦ ከሁለቱም ወገን የተውጣጣው አራት አባላት የነበሩት አገናኝ ኮሚቴ ግን ተግባሩን በሚገባ ሊወጣ አልቻለም። ሥልጣን ቀስ በቀስ ከእንዳልካቸው እጅ እያፈተለከች ደርግ መዳፍ ውስጥ ገባች። በዚሁም አባበቃ፤ ሐምሌ 15 ቀን እንዳልካቸው ከጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣኑ እንዲወርድ ተደርጎ፣ ከጥቂት ቀናት በኋላ እሱው ራሱ ያሳሰራቸውን ጓዶቹን ተቀላቀለ። በቦታውም ተራማጅ ነው ተብሎ ይገመት የነበረው የልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ልጅ ሚካኤል እምሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ተሾመ።

እንዲያ ተጠቦና ተጨንቆ የፈጠረው የፖለቲካ ሥርዓት እየሟሸሸ ሲሄድ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የአፍዝ አደንግዝ እንደያዘው ሰው ዝም ብሎ ይመለከት ነበር። የንቅናቄው የመጨረሻ ዒላማ መሆኑን ከቶም የተገነዘበው አይመስልም ነበር። ለውጡ የማታ ማታ ማን ላይ ያነጣጠረ እንደነበር ግን ሳይውል ሳያድር ገሀድ እየሆነ መጣ። ደርግ «ትልቁን ግንድ ለመቁረጥ መጀመርያ ቅርንጫፎቹን መልምል» የሚለውን ስልት በመከተል፣ በመጀመርያ የንጉሣዊ ሥልጣን አውታሮች የነበሩትን እንደ ዙፋን ችሎት፣ ፍርድ አጣሪ ጉባዔ፣ ልዩ ካቢኔ፣ የግቢ ሚኒስቴርና የዘውድ ምክር ቤት ያሉትን ተቋሞች አፈረሳቸው። ብዙም ሳይቆይ ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ በከፍተኛ ባለአክሲዮንነት ይቆጣጠረው የነበረውን የአንበሳ አውቶቡስና የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካን ወረሳቸው። በተለይ በቢራ ፋብሪካው ንጉሠ ነገሥቱ ተጠቃሚ እንደነበር የሚያውቀው በጣም ጥቂት ሰው ስለነበር እርምጃው በንጉሠ ነገሥቱ ካደረሰበት የገንዘብ ኪሣራ ይልቅ ክብሩንና ሞገሱን በብርቱ አቀለለው። መላ ዘመነ መንግሥቱን ለሕዝቡ አሳቢ መስሎ ይታይ የነበረው መሪ አሁን ትርፍ ለማግበስበስ የሚሯሯጥ ተራ ነጋዴ ሆኖ ታየ። በመጨረሻም ንጉሠ ነገሥቱ ያለ አጋዥና አዛኝ እንደቀረ ካረጋገጠ በኋላ፤ ደርግ ጳጉሜ 4 ቀን 1966 ባደረገው ስብሰባ በድምፅ ብልጫ ንጉሠ ነገሥቱን ከዙፋኑ ለማውረድ ወሰነ።

ከማውረዱ በፊት ግን፣ አሁንም አስተማማኝ የሆነ የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት ሲል፣ የመጨረሻውን ድራማ ቀምሞ አቀረበ። አዲሱን ዓመት ለማክበር ለተዘጋጀው የአዲስ አበባና የአካባቢዋ ሕዝብም ጳጉሜ 5 ቀን ምሽት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የ1965ቱን የወሎ ሕዝብ የረሀብ እልቂት የሚያሳይ ፊልም አቀረበ። ፊልሙ መሠረት ያደረገው በእንግሊዛዊው ሪፖርተር ጆናታን ዲምቢልቢ ተዘጋጅቶ እንግሊዝ አገር በቴሌቪዥን የታየውን ቢሆንም፤ ከንጉሠ ነገሥቱ የምቾትና የቅንጦት ኑሮ ጋር ተቀነባብሮ የቀረበ በመሆኑ፤ ተመልካቹ ሕዝባዊ ስቀቃን ከንጉሣዊ ፈንጠዚያ ጋር እያነፃፀረ ቁጣው ገንፍሎ እንዲወጣ

ነገር ግን ይህ የአገር ቤቱ መኢሶን አመለካከት ከአገር ውጭ ካለው የመኢሶን አመራር ጋር የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም:: ምክንያቱም የ«ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» መፈክር ግራው ክንፍ ሰፊውን ሕዝብ ለማደራጀት ካለበት ዋነኛ ተግባር የሚያዘናጋ ነው የሚል ጠንካራ አቋም አመራሩ ስለነበረው ነው:: የመኢሶን የውጭ ክንፍ አገር ቤት ከገባ በኋላም የሱ አቋም አይሎ ድርጅቱ መፈክሩን ለመተውና ኋላም አምርሮ ሊታገለው በቃ:: በመፈክሩ ዙርያ በኢሕአፓና በመኢሶን መካከል የነበረው የጦፈ ክርክር በማርክሳዊ ቃላት ተሸልሞ ሲቀርብ መሠረታዊ የርዕዮተ ዓለም ክርክር ይምሰል እንጂ ዞሮ ዞሮ የሥልጣን ሽኩቻ ነበር ማለት ይቻላል:: ይኸውም ባንድ ወገን ኢሕአፓ በብዙኃን ድርጅቶች (የመምህራን፣ ተማሪዎችና ሠራተኞች) ውስጥ በስፋት ሰርጎ የገባ በመሆኑ የሚቋቋመውን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እቆጣጠራለሁ የሚል እምነት ነበረው:: ባንፃሩ ደግሞ መኢሶን በዚህ ረገድ ገና ብዙ የሚቀረው ስለነበር እሱ ድርጅቱን አፈርጥሞ እስከሚረከበው ድረስ ሥልጣን በደርግ እጅ መቆየቱን እምብዛም አልጠላውም ነበር:: ስለዚህም ነው ወደ 1967 አጋማሽ ገደማ መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ በማድረግ ደርግን ሙሉ በሙሉ ከመቃወም ወደ ሂሳዊ ድጋፍ የተሸጋገረው::

ያም ሆነ ይህ ግን፣ ደርግ ሥልጣን አስረክቦ ወደ ካምፕ የመመለስ አንዳችም ፍንጭ አላሳየም:: ወራት በዓመታት እየተተኩ በሄዱ ቁጥር እራሱን የአብዮቱ ዋና ጠባቂና አለኝታ ማድረግ ያዘ:: ወደ ካምፕ መመለስ ማለት አብዮቱን መክዳት ሆኖ ታየው:: «ያለምንም ደም» ብሎ የተነሳው ደርግ ደም ማፍሰስ ከጀመረ በኋላ ከሥልጣን መውረድ ማለት ራስን ለፍርድ ወይ ለበቀል አሳልፎ መስጠት ሆኖ አገኘው:: ስለሆነም ከሕዝብ የሚመጣውን የሥልጣን ጥያቄ ሲሆን በዘዴ ማለዘብ፣ ካልሆነም በኃይል መቅጨት ነበረበት:: እራሱን ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ያሰኘውም ከሕዝብ የቀረበውን የሽግግር ስልት ለራሱ በሚስማማ መንገድ ለመተርጎም ነው:: የሕዝባዊ ውክልና ጥያቄንም ለማስተንገስ መንግሥታዊና ሃይማኖታዊ ተቋሞችን፣ አሥራ አራቱን ክፍላተ ሀገርና ሕዝባዊና የሙያ ድርጅቶችን የሚወክሉ አባላት ያሉበት ብሔራዊ የመማክርት ሸንጎ ሰየመ::

ይህ የመሸንገያው ስልት ሲሆን፣ በዚህ በማይመለሱት ላይ ደግሞ ጠንካራ በትሩን አሳረፈባቸው:: በመጀመርያ የተቃዋሚ ሕዝባዊና የሙያ ድርጅቶች መሪዎችን አሰረ:: ወዝአደሩ የመሪዎቹን መታሰር ተቃውሞ ሲነሳ ደግሞ ያለ ርኅራኄ መታቸው:: ፍጥጫው ወደ ሠራዊቱም ጎራ ተዛምቶ የሕይወት መጥፋትን አስከተለ:: የደርግ በሥልጣን ላይ መደላደልን ከተቃወሙት ወገን ክቡር ዘበኛና የአርሚ አቪየሽን መሪዎቻቸውን አሳልፈው ለመስጠት ሲገደዱ፣ የመሐንዲስ ክፍል ግን አሻፈረኝ በማለቱ መስከረም 27 ቀን ለደርጉ (በተለይም ለአንደኛው ምክትል ሊቀ መንበር ለሻለቃ መንግሥቱ) ታማኝ የሆኑ ወታደሮች ካምፑን ሰብረው በመግባት በተከፈተው ተኩስ አምስት የመሐንዲስ ጦር አባላት ሲገደሉ አያሌዎች ለመቁሰልና ለመታሰር በቁ:: በዚህ ክስተትም አብዮቱ ያለምንም ደም ይጠናቀቃል የሚለው እምነት እንደ ጉም በነነ::





6.3 ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም በአሥመራ ስታዲዮም ከሕዝቡ ለተደረገለት የጋለ አቀባበል አፀፋውን ሲመልስ

የመስከረሙ ደም መፋሰስ የንትናቱውን የደም አልባ ምዕራፍ የዘጋውን ያህል መጭውን ፅልመትም የሚያረዳ ደወል ነበር:: ኅዳር 15፣ 1968 እሑድ ጠዋት በኢትዮጵያ ሬዲዮ የተላለፈውና የኢትዮጵያ ሕዝብን ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም ያስደነገጠው ዜና በአብዮቱ የደም ጎዳና ጉልህ ሥፍራ ይዞ የቆየ ክስተት ነው:: እንደተለመደው በወታደራዊ ማርሽ የታጀበው የደርግ መግለጫ የደርጉ ሊቀ መንበር ሌተና ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን ጨምሮ በስድሳ የቀድሞ ባለሥልጣናትና የደርግ ተቃዋሚዎች ላይ ኅዳር 14 ቀን «የፖለቲካ ውሳኔ» እንደተወሰደባቸው ለፈፈ:: በዚህም፣ ጄኔራሉ እጅ አልሰጥም ብሎ ቤቱ ተከቦ በተፈጠረው የተኩስ ልውውጥ ሲሞት የተቀሩት ሃምሳ ዘጠኙ ደግሞ ከእስር ተወስደው እንደተረሸኑ ለፍፏል:: ደርግ ባወጣው መግለጫ፣ በጄኔራሉ ላይ ያን ዓይነት የመጨረሻ እርምጃ ሊወስድ የተገደደው፣ አምባገነን ባሕሪ በማሳየቱ፣ ደርግንና ጦሩን የመከፋፈል ተግባራት በመፈፀሙና አኩርፎ ከሥራ ገበታ ራሱን በማግለሉ ነው ብሏል::

በመሠረቱ ግን መጥፊያው የሆነው ከተቀዳሚ ምክትል ሊቀ መንበሩ ከሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ጋር የነበራቸው ግንኙነት እየሻከረ መሄዱ ይመስላል:: በተለይም የኤርትራን ችግር እንዴት እንፍታው በሚለው ጥያቄ ዙርያ ጄኔራሉ ሰላማዊ አማራጭን ሲከተሉ፣ ኮሎኔሉ በኃይል የመተማመን ዝንባሌው የጎላ ነበር:: ሁለቱም ባላንጣዎች ቀደም ባሉት ሳምንታት ለተፃራሪ አቋማቸው ተቀባይነት ለማስገኘትና ደጋፊዎቻቸውን ለማብራከት በጦር ኃይሉች የተለያዩ ክፍሎች መግለጫዎች ሲሰጡ ቆይተዋል:: ከነዚህ ልዩነቶችም ባሻገር ለጄኔራሉ ሕይወት መጥፋት ዋናው ምክንያት ታሪካዊ ተልዕኮውን መፈፀሙ

ግን ይህ የአገር ቤቱ መኢሶን አመለካከት ከአገር ውጭ ካለው ... ጋር የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም:: ምክንያቱም የ«ጊዜያዊ ... መፈክር ግራው ክንፍ ሰፊውን ሕዝብ ለማደራጀት ካለበት የሚያዘናጋ ነው የሚል ጠንካራ አቋም አመራሩ ስለነበረው ነው:: ... ክንፍ አገር ቤት ከገባ በኋላም የሱ አቋም አይሎ ድርጅቱ ... ኋላም እምርሮ ሊታገለው በቃ:: በመፈክሩ ዙርያ ... መካከል የነበረው የጦፈ ክርክር በማርክሳዊ ቃላት ... መሠረታዊ የርዕዮተ ዓለም ክርክር ይምሰል እንጂ ዞሮ ዞሮ ... ማለት ይቻላል:: ይኸውም ባንድ ወገን ኢሕአፓ በብዙኃን ... ተማሪዎችና ሠራተኞች) ውስጥ በስፋት ሰርጎ የገባ ... ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እቆጣጠራለሁ የሚል ... ደግሞ መኢሶን በዚህ ረገድ ገና ብዙ የሚቀረው ስለነበር ... እስከሚረከበው ድረስ ሥልጣን በደርግ እጅ መቆየቱን ... ነበር:: ስለዚህም ነው ወደ 1967 አጋማሽ ገደማ መኢሶን ... በማድረግ ደርግን ሙሉ በሙሉ ከመቃወም ወደ ሂሳዊ ... ገረው::

... ይህ ግን፣ ደርግ ሥልጣን አስረክቦ ወደ ካምፕ የመመለስ ... አላሳየም:: ወራት በዓመታት እየተተኩ በሄዱ ቁጥር እራሱን ... አለኝታ ማድረግ ያዘ:: ወደ ካምፕ መመለስ ማለት ... ሆኖ ታየው:: «ያለምንም ደም» ብሎ የተነሳው ደርግ ደም ... ከሥልጣን መውረድ ማለት ራስን ለፍርድ ወይ ለበቀል ... ሆኖ አገኘው:: ስለሆነም ከሕዝብ የሚመጣውን የሥልጣን ... ማለዘብ፣ ካልሆነም በኃይል መቀጨት ነበረበት:: እራሱን ... አስተዳደር ደርግ ያሰኘውም ከሕዝብ የቀረበውን የሽግግር ... መንገድ ለመተርጎም ነው:: የሕዝባዊ ውክልና ... መንግሥታዊና ሃይማኖታዊ ተቋሞችን፣ አሥራ አራቱን ... የሙያ ድርጅቶችን የሚወክሉ አባላት ያሉበት ብሔራዊ ... ሰየመ::

... መሸጋገያው ስልት ሲሆን፣ በዚህ በማይመለሱት ላይ ደግሞ ... አላፈለባቸው:: በመጀመርያ የተቃዋሚ ሕዝባዊና የሙያ ... አሰረ:: ወዝአደሩ የመሪዎቹን መታሰር ተቃውሞ ሲነሳ ... መታቸው:: ፍጥጫው ወደ ሠራዊቱም ጎራ ተዛምቶ ... አስከተለ:: የደርግ በሥልጣን ላይ መደላደልን ... ክቡር ዘበኛና የአርሚ አቪየሽን መሪዎቻቸውን አሳልፈው ... የመሐንዲስ ክፍል ግን አሻፈረኝ በማለቱ መስከረም 27 ቀን ... (ሁለተኛው ምክትል ሊቀ መንበር ለሻለቃ መንግሥቱ) ታማኝ ... ካምፑን ሰብረው በመግባት በተከፈተው ተኩስ አምስት ... አባላት ሲገደሉ አያሌዎች ለመቁሰልና ለመታሰር በቁ:: በዚህ ... ያለምንም ደም ይጠናቀቃል የሚለው እምነት እንደ ጉም





6.3 ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም በአሥመራ ስታዲዮም ከሕዝቡ ለተደረገለት የጋለ አቀባበል አፀፋውን ሲመልስ

የመስከረሙ ደም መፋሰስ የንቅናቄውን የደም አልባ ምዕራፍ የዘጋውን ያህል መጭውን ፅልመትም የሚያረዳ ደወል ነበር:: ኅዳር 15፣ 1968 እሑድ ጠዋት በኢትዮጵያ ሬዲዮ የተላለፈውና የኢትዮጵያ ሕዝብን ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም ያስደነገጠው ዜና በአብዮቱ የደም ጎዳና ጉልህ ሥፍራ ይዞ የቆየ ክስተት ነው:: እንደተለመደው በወታደራዊ ማርሽ የታጀበው የደርግ መግለጫ የደርጉ ሊቀ መንበር ሌተና ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን ጨምሮ በስድሳ የቀድሞ ባለሥልጣኖችና የደርግ ተቃዋሚዎች ላይ ኅዳር 14 ቀን «የፖለቲካ ውሳኔ» እንደተወሰደባቸው ለፈፈ:: በዚህም፣ ጄኔራሉ እጅ አልሰጥም ብሎ ቤቱ ተከቦ በተፈጠረው የተኩስ ልውውጥ ሲሞት የተቀሩት ሃምሳ ዘጠኙ ደግሞ ከእስር ተወስደው እንደተረሸኑ ለፍፏል:: ደርግ ባወጣው መግለጫ፣ በጄኔራሉ ላይ ያን ዓይነት የመጨረሻ እርምጃ ሊወስድ የተገደደው፣ አምባገነን ባሕሪ በማሳየቱ፣ ደርግንና ጦሩን የመከፋፈል ተግባራት በመፈፀሙና አኩርፎ ከሥራ ገበታ ራሱን በማግለሉ ነው ብሏል::

በመሠረቱ ግን መጥፊያው የሆነው ከተቀዳሚ ምክትል ሊቀ መንበሩ ከሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ጋር የነበራቸው ግንኙነት እየሻከረ መሄዱ ይመስላል:: በተለይም የኤርትራን ችግር እንዴት እንፍታው በሚለው ጥያቄ ዙርያ ጄኔራሉ ሰላማዊ አማራጭን ሲከተል፣ ኮሎኔሉ በኃይል የመተማመን ዝንባሌው የጎላ ነበር:: ሁለቱም ባላንጣዎች ቀደም ባሉት ሳምንታት ለተፃራሪ አቋማቸው ተቀባይነት ለማስገኘትና ደጋፊዎቻቸውን ለማበራከት በጦር ኃይሎች የተለያዩ ክፍሎች መግለጫዎች ሲሰጡ ቆይተዋል:: ከነዚህ ልዩነቶችም ባሻገር ለጄኔራሉ ሕይወት መጥፋት ዋናው ምክንያት ታሪካዊ ተልዕኮውን መፈፀሙ

ነው ማለቱ የተሻለ ተአማኒነት ይኖረዋል። እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ፣ በሕዝብ ዘንድ በውል ያልታወቁት የደርግ አባላት የጄኔራሉን ስም ጋሻና ከለላ አድርገው መንቀሳቀሳቸው አያሌ ጠቀሜታ ነበረው። እያደር ግን፣ ጄኔራሉም የራሱን የሥልጣን ፍላጎት ማሳየቱ ስላልቀረና፣ ከደርግ አባላት መካከልም በተለይ እንደ ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ያሉት የራሳቸው የሥልጣን አጀንዳ ስለነበራቸው፤ ጄኔራሉ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እያመዘነ መጣ። ስለዚህ በግብፅ በ1940ዎቹ እንደታየው እነ ኮሎኔል ናስር ጄኔራል ነጊብን መጀመርያ ለሽፋን ተጠቅመው ገለል እንዳደረጉት ሁሉ፣ እነ ኮሎኔል መንግሥቱም ጄኔራል አማንን አስወገዱት። ትልቁ ልዩነት የግብፁ ጄኔራል ሕይወቱ ሲተርፍ ኢትዮጵያዊው ሕይወቱ ማለፉ ነው።

የጄኔራሉን ሞት አስከትሎ የተረሸኑት እስረኞች ባብዛኛው መሣፍንት፣ የቤተ መንግሥት ባለሟሎች፣ ሚኒስትሮች፣ የጦር አዛዦችና የጠቅላይ ግዛት እንደራሴዎች ነበሩ። ስለሆነም በተለምዶ «ስድሳ የቀድሞው መንግሥት ባለሥልጣኖች» እንደተገደሉ ተደርጎ ሲወሳ ቆይቷል። የደርግን መግለጫ በቅጡ ለተከታተለው ከስድሳዎቹ መኻል በቀድሞው ሥርዓት ምንም ሚና ያልነበራቸው፣ ግን የደርግን የፖለቲካ ሥልጣን መያዝ በመቃወማቸው ብቻ በዚሁ አጋጣሚ አብረው የተረሸኑ መኰንኖችና ወታደሮች እንደነበሩ ግልፅ ነው። በሚቀጥሉት ዓመታትም ደርግ ይህን «ሁለት ወፍ ባንድ ድንጋይ» በመምታት በሚወስዳቸው እርምጃዎች ምክንያት ሊነሳ የሚችለውን ተቃውሞ የማደናገር ስልት ካንዴም ሁለቴ ሲጠቀምበት ታይቷል።

የጄኔራሉ ሞትና የሃምሳ ዘጠኙ እስረኞች መረሸን ያለው ትስስር በውል አይታወቅም። ያም ሆነ ይህ ግን እስረኞቹ አደረሱት የተባለውን በደል የሚያጣራ መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሞ የማጣራት ሥራውን በጀመረበት ወቅት እንዲህ ያለው ፍርደ ገምድል እርምጃ መወሰዱ፤ ኮሚሽኑን ትርጉም አልባ ከማድረጉም በላይ የወደፊቱም የደርግ አካሄድ ምን ያህል ፍትሓዊ እንደሚሆን በእጅጉ የሚያጠራጥር ነበር። ይህ ያለፍርድ መግደል አባዜም ማሳረጊያው እስካሁንም ጠባሳው ያልጠፋው «ቀይ ሽብር» ሆነ። ደም በማፍሰስ የተሳሰሩት የደርግ አባላትም ከእንግዲህ ወደኋላ መመለስ እንደማይችሉ ስለተረዱ የፖለቲካ አቋማቸውን ይበልጥ እያከረሩ መጡ። ምናልባት እስከዚያን ጊዜ ድረስ በፈጠራቸው የቀድሞው ሥርዓትና በአብዮታዊው ንቅናቄ መካከል ሲናውዙ ነበር ቢባልም፣ ከዚያን ጊዜ በኋላ ግን ከቀድሞው ሥርዓት ጋር የሚያገናኛቸውን እትብት ቆርጠው ዕድላቸውን ከአብዮታዊው ንቅናቄ ጋር ሙሉ በሙሉ አስተሳሰሩ። ስለሆነም በተከታታይ ለረጅም ጊዜ መለያቸው የሆኑትን አብዮታዊ እርምጃዎች ወሰዱ።

ከነዚህም እርምጃዎች ቀዳሚ የሆነው የገጠሩን ሕይወት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቀየር የነደፉትን ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀሳቸው ነው። ይህ ከጊዜ በኋላ «ብሔራዊ የእድገት በኅብረት ዘመቻ» የተባለው ፕሮግራም መጀመርያ የተሰነዘረው ደርግ ሥልጣን ከመያዙ ወደ አንድ ሳምንት ግድም ነው። ዓላማውም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችንና መምህራንን ወደ ገጠር በማዝመት





6.4 ከዘማች ተማሪዎች የዕለት ተዕለት ተግባር አንዱ ውሃ መቅዳት ነበር

የ«ኢትዮጵያ ትቅደም»ን መርህ መሠረት ያደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎችን እንዲመሩ ለማድረግ ነበር። ፕሮግራሙ በቅን ልቦና አገሪቱን ከኋላ ቀርነት ለማውጣት ታልሞ የተነደፈ ሊሆን ቢችልም፤ ደርግ የሥልጣን ተፋላሚዎቹን በልማት ስም ወደ ገጠር በማግለል በሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመደላደል የቀመመው ስልት ነው በማለት በተለይ በኋላ በኢሕአፓ ስር የተሰለፉት ግራ ክንፍ ኃይሎች ተቃወሙት።

ይህንኑ ተቃውሞ ለማለዘብም ደርግ አንዳንድ እርምጃዎች መውሰድ ነበረበት። በተለይም በምሁራኑ ዘንድ ሰፍኖ ወደነበረው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ቀረብ ለማለት ይመስላል እምብዛም ተቀባይነት ያላገኘውን የ«ኢትዮጵያ ትቅደም» መፈክር በመከለስ መመሪያዬ «ኅብረተሰባዊነት» ነው አለ። የምሁራኑን ማርክሳዊ ርዕዮት ባዕድነት ለማመላከትም «ኅብረተሰባዊነት» ሙሉ በሙሉ አገር-በቀል መሆኑን አበክሮ ገለፀ። የሂደቱ አቅጣጫ በሌሎች አፍሪቃ አገሮች እንደታየው ኢትዮጵያዊ ሶሻሊዝም ለመከተል ነው። ይሁን እንጂ አዲሱ መርህም ቢሆን ከመጀመርያው መፈክር እምብዛም ግልፅ ያልሆነና የተለያዩ እምነቶችና መርሀ-ግብሮች የተጨናነቁበት ሁኔታ ከመሆን አልዳነም።

ዘማቾቹ ወደየምድብ ሥፍራዎቻቸው ከመሰማራታቸው በፊት ታኅሣሥ 12 ቀን 1967 ጃንሜዳ ላይ ትልቅ የሰልፍ ትርኢት አደረጉ። በዚህም ጊዜ የደርግ አባላት ለመጀመርያ ጊዜ ገሀድ ወጥተው ለሕዝብ ታዩ። በተለይም መንግሥቱን ዘማቾቹ «መንጌ! መንጌ!» እያሉ በጋለ ስሜት ያደረጉለት አቀባበል በመሪነት ሥፍራው ላይ ተደላድሎ እንዲቆይ የልብ ልብ ሳይሰጠው አልቀረም። ምንም እንኳ መጀመርያ በዘመቻው ዙርያ ብዙ ክርክርና አታካራ የነበረ ቢሆንም፤ አንዴ



6.4 ከዘማች ተማሪዎች የዕለት ተዕለት ተግባር አንዱ ውሃ መቅዳት ነበር

የ«ኢትዮጵያ ትቅደም»ን መርህ መሠረት ያደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎችን እንዲመሩ ለማድረግ ነበር:: ፕሮግራሙ በቅን ልቦና አገሪቱን ከኋላ ቀርነት ለማውጣት ታልሞ የተነደፈ ሊሆን ቢችልም፣ ደርግ የሥልጣን ተፋላሚዎቹን በልማት ስም ወደ ገጠር በማግለል በሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመደላደል የቀመመው ስልት ነው በማለት በተለይ በኋላ በኢሕአፓ ስር የተሰለፉት ግራ ክንፍ ኃይሎች ተቃወሙት::

ይህንኑ ተቃውሞ ለማለዘብም ደርግ አንዳንድ እርምጃዎች መውሰድ ነበረበት:: በተለይም በምሁራኑ ዘንድ ሰፍና ወደነበረው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ቀረብ ለማለት ይመስላል እምብዛም ተቀባይነት ያላገኘውን የ«ኢትዮጵያ ትቅደም» መፈክር በመከለስ መመሪያዩ «ኅብረተሰባዊነት» ነው አለ:: የምሁራኑን ማርክሳዊ ርዕዮት ባዕድነት ለማመላከትም «ኅብረተሰባዊነት» ሙሉ በሙሉ አገር-በቀል መሆኑን አበክሮ ገለፀ:: የሂደቱ አቅጣጫ በሌሎች አፍሪቃ አገሮች እንደታየው ኢትዮጵያዊ ሶሻሊዝም ለመከተል ነው:: ይሁን እንጂ አዲሱ መርህም ቢሆን ከመጀመርያው መፈክር እምብዛም ግልፅ ያልሆነና የተለያዩ እምነቶችና መርሀ-ግብሮች የተጨናነቁበት ሁኔታ ከመሆን አልዳነም::

ዘማቾቹ ወደየምድብ ሥፍራዎቻቸው ከመሰማራታቸው በፊት ታኅሣሥ 12 ቀን 1967 ጃንሜዳ ላይ ትልቅ የሰልፍ ትርኢት አደረጉ:: በዚህም ጊዜ የደርግ አባላት ለመጀመርያ ጊዜ ገሀድ ወጥተው ለሕዝብ ታዩ:: በተለይም መንግሥቱን ዘማቾቹ «መንጌ! መንጌ!» እያሉ በጋለ ስሜት ያደረጉለት አቀባበል በመሪነት ሥፍራው ላይ ተደላድሎ እንዲቀይ የልብ ልብ ሳይሰጠው አልቀረም:: ምንም እንኳ መጀመርያ በዘመቻው ዙርያ ብዙ ክርክርና አታካራ የነበረ ቢሆንም፣ አንዱ

ከዘመቱ በኋላ ዘማቾቹ በሙሉ ስሜት የገጠሩን ሕይወት የመለወጡን ተግባር ተያያዙት። በተለይም በናፍቆት ይጠብቁት የነበረው የመሬት ስሪት አዋጅ የካቲት 25 ቀን ከወጣ በኋላ፣ አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ በሙሉ ኃይላቸውና በጋለ ስሜት ተንቀሳቀሱ። ይሁን እንጂ ይህ እንቅስቃሴያቸው ሳይውል ሳያድር ከደርግ አባላትና ከሌሎች የመንግሥት ሹማምንት ጋር አጋጫቸው። ተማሪዎቹ አዋጁን በመተግበሩ ላይ ጭቁኑን አርሶ አደር ያሳተፈ ስልት ሲከተሉ፣ የደርግ ባለሥልጣኖች የመረጡት ስልት ደግሞ ቢሮክራሲያዊ ነበር። እያደርም የዘመቻ ጣቢያዎች ደርግና ደጋፊዎቹ ባንድ ወገን፣ ደርግን አምርሮ የሚቃወመው የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎቹ በሌላ ወገን የሚፋለሙበት መድረክ ሆነ። ዘመቻው እየተራዘመ በሄደ ቁጥር ተቃዋሚዎቹ ምድብ ጣቢያዎቻቸውን እየተዉ ወሳኙ የፖለቲካ ፍልሚያ ወደሚካሄድበት ወደሀገሪቱ ርዕሰ ከተማ መመለስ ጀመሩ።

ደርግ መሬትን የ«ሕዝብ» (እንደ እውነቱ ከሆነ የመንግሥት) ያደረገውን አዋጅ የካቲት 25፣ 1967 ከማውጣቱ ቀደም ብሎ የንግድ፣ የኢንዱስትሪና የገንዘብ ተቋማትን ወርሶ ነበር። በሐምሌ 19 ደግሞ የከተማ መሬትንና ትርፍ ቤቶችን የመንግሥት ያደረገው አዋጅ ታወጀ። እነዚህ ተከታታይ እርምጃዎች ደርግ እስከ ፍፃሜ መንግሥቱ ድረስ ሲመካባቸውና ሲኩራራባቸው የነበሩ እርምጃዎች ሆኑ። በተለይ እንደ አብዮት በዓል (መስከረም 2) ባሉ በዓላት እነዚህን «ድሎች» የማይዘረዝር ንግግር ከቶም አይታሰብም ነበር። ይሁን እንጂ እያደር የነዚህ እርምጃዎች ሕዝባዊ ፋይዳ በእጅጉ አጠያያቂ እየሆነ መጣ። በመሠረቱ፣ ውጤታቸው የሀገር ሀብትን ከግል ወደ መንግሥት እጅ ማዘዋወር ነበር። ስለሆነም፣ ወትሮም ገደብየለሽ ሥልጣን የነበረው መንግሥት አሁን ፈላጭ ቆራጭ ሆነ። መንግሥት ቀጭም ሽላሚም ሆኖ ኅብረተሰቡን ሙሉ በሙሉ ከመዳፉ ሥር አደረገው። በሌላ አነጋገር መንግሥት በቁጥጥሩ ሥር ያደረጋቸው የኢኮኖሚ አውታሮች ፍፁማዊ የሥልጣን መረብ ለመዘርጋት የተደላደለ መሠረት ሰጡት። የሀገር ኢኮኖሚ በቢሮክራሲው ቁጥጥር ስር እየሆነ በሄደ ቁጥርም የግሉ ዘርፍ እየሟሸሸና እየቀጨጨ ሄደ።

ይህ ማለት ግን የመሬት አዋጁ የነበረውን ታሪካዊ ፋይዳ ለማንኳሰስ አይደለም። እያሌ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን በፅኑ የታገሉትን የዘመናት ብሶት ለማስወገድ የታለመ በመሆኑ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው። በሃያኛው መቶ ዓመት መጀመርያዎቹ ዐሥርተ ዓመታት ተራማጅ ምሁራን የገባሩ ዕዳና እሳር እንዲቀልለት በአፅንዖትና በስሜት ታግለዋል። በተድበሰበሰ መልክም ቢሆን የ1953 መፈንቅለ መንግሥት መሪዎችም የእርሻ ምርትን ለማስፋፋት ቃል ገብተዋል። በ1957 ደግሞ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች «መሬት ለአራሹ» ብለው ሰልፍ በመውጣት አብዮታዊ ፈር ቀደዋል። ያ መፈክርም ለዓመታት ሲያስተጋባ ቆይቶ የቀድሞውን ሥርዓት ግብአተ ሞት አፋጥኗል። የ1967ቱ የመሬት አዋጅም ከሁሉም በላይ የዚያ መፈክር ውጤት ነው ማለት ይቻላል። የእንዳልካቸው ካቢኔም ቢሆን የጥያቄውን መሠረታዊነት በመገንዘብ መጋቢት 27 ባወጣው የፖሊሲ መግለጫ በመሬት ይዞታዎች ላይ የአንድ ሺ ሄክታር ጣራ በመደንገግና ወደፊት የሚሰጡ ማሳዎች መሬት ለሌላቸው ብቻ እንደሚሆን ቃል በመግባት አንገብጋቢ ለነበረው የሕዝብ ጥያቄ የበኩሉን መልስ ለመስጠት ተገዷል።





6.5 የገጠርን መሬት ለሕዝብ ያደረገውን አዋጅ በመደገፍ የወጣው ሕዝባዊ ሰልፍ ከከፊሉ።

በየካቲት 1966 አብዮቱ ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮም፣ የመሬት ጥያቄና መፍትሔው በአገሪቱ ጋዜጦች ዋና የመወያያ ርእስ ሆነው ቆይተዋል። ክርክሩና ውይይቱ በመንግሥት ጋዜጦች፣ በኅቡዕ ጋዜጦችና በተለይም ጉዳዩ በቀጥታ በሚመለከታቸው እንደ መሬት ይዞታ ሚኒስቴርና የጭላሉ እርሻ ልማት ድርጅት ባሉ መሥሪያ ቤቶች ይካሄድ ነበር። ክርክሩ ያተኮረባቸው ዋና ዋና ነጥቦችም መፍትሔው መሠረት የሚያደርገው ምርታማነትን ነው ወይስ ፍትሕን፣ የሚመጣውስ ከላይ ነው ወይስ ከታች፣ መሬት የግል ይሆናል ወይስ የጋራ ነበሩ።

ከዚህ ሁሉ ክርክርና ውጣ ውረድ በኋላ ነበር ደርግ በየካቲት 25 ቀን 1967 በስር ነቀልነቱ ወደር ያልተገኘለትንና እከራሪ የግራ ተቃዋሚዎቹን እንኳ ያስገረመውን የመሬት አዋጅ ይፋ ያደረገው። አዋጁ የግል የመሬት ይዞታን የሚያስወግድና የገጠር መሬት የማይሸጥ፣ በሊዝ የማይተላለፍና በዋስትናም የማይያዝ መሆኑን ደነገገ። ጭሰኝነትን ያስቀረው አዋጅ የመሬት ይዞታን በአሥር ሄክታር ሲወስን፣ አርሶ አደሩም በመሬቱ ላይ የሚኖረው መብት በጥቅም ላይ ከማዋል ያለፈ እንደማይሆን አወጀ። አዋጁን ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድና ወደፊትም እንደ አስፈላጊነቱ የመሬት ድልድል የማድረግ ሥልጣን ያላቸውን የገበሬዎች ማኅበር አቋቋመ። ከአዋጁ ቀጥተኛ ውጤቶች አንዱ የቅድመ-አብዮት ኢትዮጵያ ዓይነተኛ ባሕሪ የነበረውን የመሬት ሙግት ማስቀረቱ ነው።

በሙሉ ስሜት የገጠሩን ሕይወት የመለወጡን ተግባር በናፍቆት ይጠብቁት የነበረው የመሬት ስሪት አዋጅ በኋላ፤ አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ በሙሉ ኃይላቸውና ተንቀሳቀሱ:: ይሁን እንጂ ይህ እንቅስቃሴያቸው ሳይውል ሳያድር ከሌሎች የመንግሥት ሹማምንት ጋር አጋጫቸው:: ተማሪዎቹ ጭቁኑን አርሶ አደር ያሳተፈ ስልት ሲከተሉ፤ የደርግ የመረጠው ስልት ደግሞ ቢሮክራሲያዊ ነበር:: እያደርም የዘመቻ ገበሬዎቹ ባንድ ወገን፤ ደርግን አምርሮ የሚቃወመው ገበሬዎቹ በሌላ ወገን የሚፋለሙበት መድረክ ሆነ:: በሄደ ቁጥር ተቃዋሚዎቹ ምድብ ጣቢያዎቻቸውን የፓለቲካ ፍልሚያ ወደሚካሄድበት ወደሀገሪቱ ርዕሰ ከተማ ...

ደርግ የካቲት መሬትን የ«ሕዝብ» (እንደ እውነቱ ከሆነ የመንግሥት) ያደረገውን 25፤ 1967 ከማውጣቱ ቀደም ብሎ የንግድ፤ የኢንዱስትሪና ወርሶ ነበር:: በሐምሌ 19 ደግሞ የከተማ መሬትንና ትርፍ ያደረገው አዋጅ ታወጀ:: እነዚህ ተከታታይ እርምጃዎች መንግሥቱ ድረስ ሲመካባቸውና ሲኩራራባቸው የነበሩ በ... ላይ እንደ አብዮት በዓል (መስከረም 2) ባሉ በዓላት የሚ ይዘረዝር ንግግር ከቶም አይታሰብም ነበር:: ይሁን እንጂ እርምጃዎች ሕዝባዊ ፋይዳ በእጅጉ አጠያያቂ እየሆነ መጣ:: ውጤታቸው የሀገር ሀብትን ከግል ወደ መንግሥት እጅ ማዘዋወር ወ...ርም ገደብየለሽ ሥልጣን የነበረው መንግሥት አሁን መንግሥት ቀጭም ሸላሚም ሆኖ ኅብረተሰቡን ሙሉ አደረገው:: በሌላ አነጋገር መንግሥት በቁጥጥሩ ሥር አውታሮች ፍፁማዊ የሥልጣን መረብ ለመዘርጋት ሰጡት:: የሀገር ኤኮኖሚ በቢሮክራሲው ቁጥጥር ስር እየሆነ የግሉ ዘርፍ እየሟሸሸና እየቀጨጨ ሄደ::

ይህ ማለት ግን የመሬት አዋጁ የነበረውን ታሪካዊ ፋይዳ ለማንኳሰስ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን በፅኑ የታገሉትን የዘመናት ብሶት በመሆኑ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው:: በሃያኛው መቶ ... ዓመታት ተራማጅ ምሁራን የገባሩ ዕዳና አሳር በስሜት ታግለዋል:: በተድበሰበሰ መልክም ቢሆን መንግሥት መሪዎችም የእርሻ ምርትን ለማስፋፋት ቃል በ1957 ደግሞ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች «መሬት ለአራሹ» ብለው አብዮታዊ ፈር ቀደዋል:: ያ መፈክርም ለዓመታት ሲያስተጋባ ሥርዓት ግብአተ ሞት አፋጥኗል:: የ1967ቱ የመሬት በላይ የዚያ መፈክር ውጤት ነው ማለት ይቻላል:: ቢሆን የጥያቄውን መሠረታዊነት በመገንዘብ መጋቢት 27 መግለጫ በመሬት ይዞታዎች ላይ የአንድ ሺ ሄክታር ጣራ የሚሰጡ ማሳዎች መሬት ለሌላቸው ብቻ እንደሚሆን ቃል ለነበረው የሕዝብ ጥያቄ የበኩሉን መልስ ለመስጠት




6.5 የገጠርን መሬት ለሕዝብ ያደረገውን አዋጅ በመደገፍ የወጣው ሕዝባዊ ሰልፍ በከፊል::

በየካቲት 1966 አብዮቱ ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮም፣ የመሬት ጥያቄና መፍትኄው በአገሪቱ ጋዜጦች ዋና የመወያያ ርእስ ሆነው ቆይተዋል:: ክርክሩና ውይይቱ በመንግሥት ጋዜጦች፣ በኅቡዕ ጋዜጦችና በተለይም ጉዳዩ በቀጥታ በሚመለከታቸው እንደ መሬት ይዞታ ሚኒስቴርና የጭላሎ እርሻ ልማት ድርጅት ባሉ መሥሪያ ቤቶች ይካሄድ ነበር:: ክርክሩ ያተኮረባቸው ዋና ዋና ነጥቦችም መፍትኄው መሠረት የሚያደርገው ምርታማነትን ነው ወይስ ፍትሕን፣ የሚመጣውስ ከላይ ነው ወይስ ከታች፣ መሬት የግል ይሆናል ወይስ የጋራ ነበሩ::

ከዚህ ሁሉ ክርክርና ውጣ ውረድ በኋላ ነበር ደርግ በየካቲት 25 ቀን 1967 በስር ነቀልነቱ ወደር ያልተገኘለትንና አክራሪ የግራ ተቃዋሚዎቹን እንኳ ያስገረመውን የመሬት አዋጅ ይፋ ያደረገው:: አዋጁ የግል የመሬት ይዞታን የሚያስወግድና የገጠር መሬት የማይሸጥ፣ በሊዝ የማይተላለፍና በዋስትናም የማይያዝ መሆኑን ደነገገ:: ጭሰኝነትን ያስቀረው አዋጅ የመሬት ይዞታን በአሥር ሄክታር ሲወስን፣ አርሶ አደሩም በመሬቱ ላይ የሚኖረው መብት በጥቅም ላይ ከማዋል ያለፈ እንደማይሆን አወጀ:: አዋጁን ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድና ወደፊትም እንደ አስፈላጊነቱ የመሬት ድልድል የማድረግ ሥልጣን ያላቸውን የገበሬዎች ማኅበር አቋቋመ:: ከአዋጁ ቀጥተኛ ውጤቶች አንዱ የቅድመ-አብዮት ኢትዮጵያ ዓይነተኛ ባሕሪ የነበረውን የመሬት ሙግት ማስቀረቱ ነው::

የአዋጁ ታሪካዊ ፋይዳ የመሬት ከበርቴውን መደብ ማስወገድ ሲሆን፣ ዋነኛ ተጠቃሚዎቹም ጭሰኞችና መሬት አልባ አርሶ አደሮች ነበሩ። አዋጁ በተጠቃሚነት ደረጃም ብቻ ቢሆን ባለመሬት ያደረጋቸው ባብዛኛው በደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍል ይገኙ የነበሩ እነዚህ ጭቁን ዜጎች ለሚቀጥሉት ሁለት አሥርተ ዓመታት ያህል ለደርግ የሥልጣን መደላድል ፅኑ መሠረት ሊሆኑ በቅተዋል። ይሁን እንጂ ለዚያኑ ዓመታት ያህል ሳያባራ በተካሄደው ጦርነት ተማገዱ እንጂ ኑሯቸውን በማሻሻል ረገድ ይህ ነው የሚባል ያገኙት ጠቀሜታ አልነበረም። የችግሩ ምንጭ አርሶ አደሩ በተመደበለት መሬት ከመጠቀም አልፎ ባለቤት መሆን አለመቻሉ ነው። ይህም አልበቃ ብሎ መንግሥት የአርሶ አደሩን ኑሮ ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ የሚቆጣጠሩና ነፃነቱን በብርቱ የሚሸብቡ እርምጃዎች ወሰደ። ከነዚህም መካከል አርሶ አደሩ ምርቱን መንግሥት በደነገገው (ዝቅተኛ) ዋጋ ለመንግሥት ብቻ እንዲያቀርብ ተብሎ የተቋቋመው የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት፣ በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሠረተ የሰፈራ ፕሮግራምና የጋራ እርሻ፣ እንዲሁም አርሶ አደሩ ያልመከረበትና ያልዘከረበት የመንደር ምሥረታ ፕሮግራምን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ እምብዛም ተወዳጅነት ያልነበራቸው የደርግ እርምጃዎች በተለይ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል አርሶ አደሩ ከፍተኛ ብሶት እንዲሰማውና ብሎም ከኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ጎን በመሰለፍ ደርግን ለመጣል እንዲዘምት አስተዋፅኦ አድርገዋል።

የከተማ መሬትንና ትርፍ ቤቶችን የመንግሥት ያደረገውም አዋጅ ቢሆን፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፍትሕን ለማምጣት እንደተወሰደ ቅን እርምጃ ብቻ አድርጎ ማየት ያዳግታል። እርግጥ ነው የቀድሞው ገዢ መደብ የኢኮኖሚ መሠረት ከገጠር መሬት በተጨማሪ በከተማ ቦታ ሽያጭና ቤት ኪራይ ላይም የነበረ በመሆኑ ያን መደብ በማዳከም ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይሁን እንጂ አዋጁ ለመንግሥት ውርስ የዳረገው የከበርቴውን ቪላና ፎቅ ብቻ ሳይሆን የጭቁኑንም ደሳሳ ጎጆ ነው። ስለሆነም የነገሩ ኢፍትሐዊነት እንዳለ ሆኖ፣ እነዚህን ጎጆዎች እንዲያስተዳድሩ ሥልጣን የተሰጣቸው የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት (በተለምዶ አነጋገር ቀበሌዎች) በተለይ ጎጆዎቹን እንጠግናለን ካሉ የሚጠብቃቸው ከትርፍ ይልቅ ኪሳራ ነው። እያደር ግልፅ እየሆነ እንደመጣው ግን የቀበሌዎች ሚና ካስተዳደር ይልቅ ቁጥጥር ላይ ያተኮረ ነበር። የገበሬዎች ማኅበራት አርሶ አደሩን ከደርግ መዳፍ ስር እንዳደረጉት ሁሉ፣ አዲስ አድራሽ የተሰጠው እያንዳንዱ የከተማ ነዋሪም በቀበሌዎች አማካይነት ሕይወቱና እንቅስቃሴው በመንግሥት ቁጥጥር ስር ዋለ። በሚቀጥሉት ዓመታትም ቀበሌዎች የደርግና የኢሕአፓ መፋለሚያ መድረኮች ሆኑ። የኢሕአፓ ታጣቂዎች የቀበሌ መሪዎችን እያደኑ ሲገድሉ፣ ቀበሌዎች በተለይም የአብዮት ጥበቃ ጓዶች፣ የኢሕአፓ አባላትንና ደጋፊዎች እስከ «ቀይ ሽብር» በዘለቀ የአፀፋ ምት በየአደባባዩና በየእስር ቤቱ ገደሉ።

## ደርግ በማርክሳዊ ርዕዮት ጎዳና

ደርግ በታሪክ የሚታወቀው በ20ኛው መቶ ዓመት ብቅ ካሉት እጅግ ቀናናዊ ማርክሳዊ መንግሥታት እንዱ በመሆኑ ነው። እስከ ዕለተ ሞቱም በዚህ ማርክሳዊ ማንነቱ ራሱን ሲያሞካሽ ቆየ። ይሁን እንጂ፣ መቶ አሥር ግድም የሆኑት የደርግ አባላት በ1966 አጋማሽ ላይ አራተኛ ክፍለ ጦር መሽገው የሀገሪቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምን ይሁን ብለው ሲመክሩ፣ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን በኢትዮጵያ ውስጥ ስርጎ የማስገባቱ ጉዳይ ከአብዛኞቹ ኅሊና እጅግ የራቀ ነበር። መመሪያቸው ያደረጉት «ኢትዮጵያ ትቅደም» የሚለው መፈክር ግፋ ቢል አገር ወዳድነትን የሚጠቁም ነበር። በታኅሣሥ ወር ባብዛኛው የእድገት በኅብረት ዘማቾችን ለማስደሰት ሲባል ወደ «ኅብረተሰብዓዊነት» ሲኀለምስም ዓላማው «ኢትዮጵያዊ ሶሻሊዝም»ን እንጂ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ለማስረፅ አልነበረም።



ይሁንና ደርግ ፈራ ተባ ሲል የያዘው የሶሻሊስት ፈር ወደፊት የሚከተለውን የርዕዮተ ዓለም አቅጣጫ አመልካች ነበር። ያንን ፈር መልቀቁ እያደር አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን የማይታሰብ እየሆነ መጣ። የዚህንም ዋነኛ ምክንያት ለመረዳት ተማሪዎች በኢትዮጵያ አብዮት አመጣጥና ሂደት ላይ የነበራቸውን ወሳኝ ሚና ማጤን ያስፈልጋል። እንደ እውነቱ ከሆነ መለዮ ለባሹ በየካቲት 1966 ሕዝባዊ አመፅ ውስጥ ብቅ ያለው ባመዛኙ ከሙያው ጋር የተያያዙ ብሶቶችን ይዞ ነው (የደመወዝ ጭማሪ፣ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል፣ ወዘተ)። ጥቅማቸውን አስከብረው ወደ ካምፖቻቸው ለመመለስ ሲያስቡ፣ «ወቱ ደሞዟን አስጨምራ ወደ ካምፕ ተመለሰች» የሚለው የተማሪዎችና የሌሎች ሲቪል ወገኖች ጉንተላና ወቀሳ ነው መለዮ ለባሹን ወደ ፖለቲካው መድረክ የገፋፋው። እያደርም ደርግ ሥልጣን ለመያዝ ብቻ ሳይሆን በሥልጣን ላይ ለመቆየት ከፈለገ እየገነነ ከመጣው ማርክሳዊ ርዕዮት ውጭ አማራጭ እንደሌለው እየተገነዘበ መጣ።

ከ1966 እስከ 1968 ድረስ ባሉት ሁለት ዓመታት ደርግ ከዚህ ርዕዮት ጋር ለመተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ከማንም ያላነሰ ክህሎት አለኝ ለማለት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ነበረበት። ሁልጊዜ አንድ እርምጃ ወደፊት ቀድሞ ከሚገኘው የግራ ክንፍ ኃይል ጋር ለመስተካከልና ብሎም ለማለፍ የነበረው ትግልና ጥረት ቀላል አልነበረም። ጥረቱም ተሳክቶ በሚያዝያ 1968 ደርግ የመጨረሻውን ርዕዮተ ዓለማዊ እመርታ በማድረግ፣ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን በመመሪያነት አወጀ። በዚህ ድርጊቱም እየቀደመ ሲያስቸግረው ከነበረው የግራ ክንፍ የፖለቲካ ቡድን ጋር ተስተካከለ ማለት ይቻላል። ከዚያ የሚቀጥለው እርምጃ ራሱን የሠፊውንና የጭቁኑን ሕዝብ ትግል በግንባር ቀደምነት ለመምራት በታሪክ የታጨ ብቸኛ የፖለቲካ ኃይል አርጎ ማየቱ ነው።

ይህን አስደናቂ የደርግ የርዕዮተ ዓለም ጉዞ ያስመረለት አንዱ የግራ ክንፉ ተከፋፍሎ ወደ አብዮቱ መድረክ መውጣት ነው። በተለይም ከሀገር ውጭ የሚገኘው የተማሪው ንቅናቄ አካል አብዮቱ ሲፈነዳ በሁለት አክራሪ ጎራዎች ተሰልፎ ነበር። ኋላ ገሀድ እንደ ወጣው እነዚህ ሁለት ጎራዎች የኢሕአፓና የመኢሶን ድርጅቶች ተከታዮች ነበሩ። እነዚህ ሁለት አንጋፋ የግራ ክንፍ ኅቡዕ ድርጅቶች በተማሪ ድርጅቶች ሽፋን ደጋፊዎቻቸውን ማብዛትና ማጠናከር ተያይዘው ነበር። በአብዮቱ ዋዜማ ሁለቱ ጎራዎች በዓለም አቀፉ የተማሪዎች ድርጅት አወቃቀር ላይ ሳንጃ-ቀረሽ ክርክር እያደረጉ ነበር። የኢሕአፓ ወገኖች በአዲስ መልክ የተዋቀረውን ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን ሲደግፉ፣ የመኢሶን ተከታዮች ደግሞ በቁጥጥራቸው ስር የነበረው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር እንዲቀጥል ይሟገቱ ነበር። በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ባብዛኛው የፌዴሬሽንና የኢሕአፓ ደጋፊ ሲሆን በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ደግሞ ሁለት ተከፍሎ ነበር።

ከአብዮቱ መፈንዳት በፊት፤ እነዚህ ልዩነቶች ከሀገር ውጭ በመሆናቸውና በተማሪ ድርጅቶች የተወሰኑ በመሆናቸው ብዙም እርባና አልነበራቸውም። አብዮቱ በየካቲት 1966 ከፈነዳ በኋላ ግን ስለ አብዮቱ ባሕሪና ሂደት ቡድኖቹ ካላቸው አመለካከት ጋር ተቆራኙ። በተከታዮቹ ዓመታትም ልዩነቶቹ በሀገራዊ መድረክ እየጎሉ መጥተው ቀስ በቀስ ከርዕዮተ ዓለማዊ ክርክር ወደ እርስ በርስ መጠፋፋት ዘመቻ ተሸጋገሩ።

የውጭው ሁኔታ ይኸን ሲመስል፤ በሀገር ቤት ደግሞ በ1960ዎቹ መጀመርያ ዓመታት ማርክሳዊ-ሌኒናዊ የጥናት ቡድኖች በኅቡዕ መደራጀት ጀምረው ነበር። አብዮቱ ሲፈነዳም በኅቡዕ በሚሰራጩት ልሳኖቻቸው አማካይነት ከሕዝቡ ጋር መተዋወቅ ጀመሩ። ከነዚህም ልሳኖች ወዲያውኑ ግንባር ቀደም ሥፍራ የያዙት ዴሞክራሲያ እና የሰፊው ሕዝብ ድምፅ የተሰኙት ነበሩ። ውሎ አድሮም የኢሕአፓና የመኢሶን ልሳን መሆናቸው ይፋ ሆነ። ከነዚህ ሌላም የተለያዩ የግራ ክንፍ ድርጅቶች በየወቅቱ ብቅ ማለት ያዙ። የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች አብዮታዊ ትግል (ኢጭአት) በተለይ የደቡባዊ ኢትዮጵያን ሕዝቦች እወክላለሁ ሲል፤ ወዝሊግ የተባለውና ቀድሞ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት በነበረው በዶ/ር ሠናይ ልኬ የሚመራው ድርጅት ደግሞ ከሠራዊቱ መሐል በተለይም በአየር ኃይል አካባቢ አባላት መመልመል ችሎ ነበር። በመጨረሻም ከኢሕአፓ ያፈነገጡ አባላት ከሌላ አገር ውስጥ ከነበረ ኅቡዕ ድርጅት ጋር በመቀናጀት ማርክሲስት ሌኒኒስት ሪቮሉሽናሪ ድርጅት (ማሌሪድ) የተባለውን ቡድን አቋቋሙ።

በመጀመርያ የነዚህ የግራ ክንፍ ቡድኖች መበራከት ደርግን ግር ማሰኘቱ አልቀረም። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ወደ ርዕዮተ ዓለማዊው ፍልሚያ ውስጥ ገባ። በዚህ ረገድ ነገሩን ያሠመረለትም እንዳንዶቹ የግራ ክንፍ ቡድኖች ለደርግ የነበራቸው ቀና አመለካከት ነው። በተለይም መኢሶንና ወዝሊግ ደርግን ለመወዳጀት ፋክክር ይዘው ነበር ማለት ይቻላል። አንዳንዶቹ የደርግ መሪዎች የማርክሲዝም - ሌኒኒዝምን «ሀ» «ሁ» የቀሰሙትም ከሁለቱ ድርጅቶች መሪ አባላት ነበር ይባላል። ይሁንና እነዚህ የደርግ መሪዎች እስከ ወዲያኛው በኛ ጥላ ስር ይቆያሉ ብለው አስበው ከሆነ ተሳስተዋል። በተለይም ለፖለቲካ ሥልጣን ያለውን ቀናኢነት ከመጀመርያው የፈነጠቀው የደርጉ አንደኛ ሊቀ መንበር ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የራሱ ድርጅታዊ ትልም እንዳለው ሳይውል ሳያድር ግልፅ እየሆነ መጣ። በ1968 ክረምት ላይ በወዝሊግ አዋላጅነት የመንግሥቱና መለዮ ለባሽ ጓዶቹ ፓርቲ የሆነው «አብዮታዊ ሰደድ» የተሰኘው ድርጅት ተወለደ። በዚህ ድርጅታዊ ገድል የመንግሥቱ ቀኝ እጅ ሆኖ ያገለገለው እንደሱው ሐረር የሚገኘውን ሦስተኛ ክፍለ ጦርን ወክሎ የደርግ አባል የሆነው የሃምሳ አለቃ (ከጊዜ በኋላ ሻምበል) ለገሠ አስፋው ነበር። የወዝሊግና የሰደድ መተሳሰርና መወራረስ ሰደድን ያጎለበተውን ያህል ለወዝሊግ ግን የማታ ማታ መጥፊያው ሆነ። ጊዜው ደርሶ ወዝሊግ ሲመታና ሰደድ ብቸኛው የግራ አማራጭ ሆኖ ሲወጣ በወዝሊግ ላይ የቀረበበት ዐቢይ ክስ ሰርጎ ገብነት ሆነ።

በግራው ክንፍ ጎራ የነበረው ርዕዮተ ዓለማዊ ትንቅንቅ በ1968 ሁለተኛ አጋማሽ የመጀመርያዎቹ ወራት ላይ ከፍተኛ ደረጃ ደረሰ። ዞሮ ዞሮ የትንቅንቁ ተጠቃሚ የሆነውም የዳር ተመልካች የነበረው ደርግ ነው። ይህ ፍልሚያ የሚካሄደው በዕለታዊው የአማርኛ ጋዜጣ አዲስ ዘመን ሁለተኛ ገፅ ላይ በተለይ



«አብዮታዊ መድረክ» በተሰኘው ዓምድ ላይ ነበር። ዋና ተፋላሚዎቹም ኢሕአፓና መኢሶን ሲሆኑ ዋና ዋና ርእሶቹም እንደ «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት መፈክር» ያሉት የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ነበሩ። በእነዚህ በታላቅ ጉጉት ይጠበቁ በነበሩና የሁለቱ ድርጅቶች አውራ ደራስያን በብዕር ስማቸው በሚጽፏቸው ጽሑፎች አማካይነት የድርጅታቸውን ማርክሳዊ ሐቀኝነት ባንፃሩም የባላንጣቸውን ክስረት ለማስረገጥ ከፍተኛ ጥረት አደረጉ። የክርክሩ አዝማሚያ አንዱ ካንዱ ለመማር ሳይሆን አንዱ ሌላውን እርቃኑን ለማስቀረት በመሆኑ የሁለቱን ድርጅቶች ልዩነት ከማጥበብ ይልቅ ይበልጥ አሰፋው። በመሠረቱ የርዕዮተ ዓለሙ ፍልሚያ ታሪካዊ ፋይዳ ከጥቂት ወራት በኋላ ለተከሰተው የትጥቅ ፍልሚያ ማሟሻ መሆኑ ነበር ማለት ይቻላል።

ሚያዝያ 12 ቀን 1968 ደርግ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን መመሪያው አድርጎ ሲያውጅ፤ በግራ ክንፉ ባቡር ጋቢና ውስጥ ከመደላደልም አልፎ መሪውን ለመጨበጥ ተዘጋጀ ማለት ይቻላል። ይህ ከቻይና አብዮት የተቀሰመ ፎርሙላ በሦስተኛው ዓለም ሶሻሊስት ለውጥን ለማምጣት ፍቱን ነው ተብሎ የታመነበት ሲሆን፤ መሠረታዊ ይዘቱም በወዝአደሩ፤ በአርሶ አደሩና በተራማጅ ንዑስ ከበርቴው አብዮታዊ ጥምረት የሠፊው ሕዝብ ጠላቶች ተብለው የተለዩትን ፊውዳሊዝምን፤ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን መደምሰስ ነው። የመጨረሻ ዓላማውም ሕዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመሥረት ነው። ይህ ዓላማም ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በመስከረም 1980 እውን ሆነ። ለተመለከተውና ነገሩን ላጤነው ሁሉ እውር ድንብሩን «ኢትዮጵያ ትቅደም!» ብሎ በሰኔ 1966 የተነሳው ደርግ እዚህ ጣራ ላይ ለመድረስ ምን ያህል አስደናቂና ረጅም ጉዞ እንደተጓዘ ግልፅ ነው።

የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ከታወጀ በኋላ ቀጣዩ እርምጃ የፕሮግራሙ አስፈፃሚ አካል የሆነውን ጊዜያዊ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ማደራጀት ሆነ። የአዋጁ መታወጅና የጽሕፈት ቤቱም መቋቋም የወቅቱ ዐቢይ ተግባር ሠፊውን ሕዝብ ማንቃትና ማደራጀት ነው እያሉ ይወተውቱ ለነበሩት እንደ መኢሶን ላሉ የግራ ክንፍ ኃይሎች ትልቅ ድል ነበር። ጽሕፈት ቤቱን እንዲመራ በተሰየመው አሥራ አምስት አባላት ባሉት ኮሚሲዮን ውስጥ የሊቀ መንበርነቱን ሥፍራ ከመያዝ አንስቶ ግልፅ የሆነ የበላይነት የነበረው መኢሶን የጽሕፈት ቤቱን መዋቅር ድርጅታዊ አቅሙን ለማፈርጠም ተጠቀመበት። ጽሕፈት ቤቱ በተቋቋመ በጥቂት ወራት ውስጥ የድርጅቱ ቁሳዊም ሆነ ሰብአዊ ኃይል ቀላል የማይባል እመርታን አሳየ። በተጓዳኝም ከተሞችን ለመቆጣጠር ቁልፍ የሆነውን የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር በመቆጣጠሩና በ1968 መጨረሻ ላይ በተደረገው የቀበሌ ምርጫ ደጋፊዎቹን ለማስመረጥ በመቻሉ ትልቅ የመደላለደል ስሜት ተሰማው። ስለሆነም የመንግሥት ሥልጣን ወደሠፊው ሕዝብ ተወካዮች የሚተላለፈው እንደ ኢሕአፓ በሐሳብ ግትርነት ደርግን በመጋፈጥ ሳይሆን ደርግ የፈጠረውን መዋቅር በዘዴ በመጠቀም ነው ብሎ ቢያስብ እምብዛም አይገርምም።

ይሁን እንጂ፤ ደርግ ይሆን የመኢሶን ስሌት ሳይረዳው ይቀራል ብሎ ማሰብ የፖለቲካ የዋህነት ነበር። ደርግ ሌላው ሁሉ ነገር ቢቀር በፖለቲካ ሥልጣን ጉዳይ ቀቅ መሆኑን ካንዴም ሁለቴ አሳይቷል። በዚያ ላይ ደግሞ የሁለት ዓመት የአብዮት ትምህርት ቤት የግራ ክንፉን ማርክሳዊ ዘይቤና

ድርጅታዊ ስልት እንዲጨብጥ አስችሎታል። ስለዚህ ነገሩ «ብልጥ ለብልጥ» ሆነና የጉልበት ፍትሻውን አይቀሬ አደረገው። አይቀሬ እየሆነ የመጣው ድራማም በአብዛኛው በ1969 ዓ.ም. መጀመርያ ተጀምሮ በዓመቱ ማብቂያ ላይ ተጠናቀቀ። በመጀመርያ ደርግ ለዘብተኛ የሆነውን የግራ ክንፍ አጋር በማድረግ፣ የእድገት እመርታው ባስደነገጠውና ማዕቀብ የሌለው ተቃውሞው ባበገነው በኢሕአፓ ላይ ዘመተ። በዚህ ረገድ፣ እያሌ የሠራተኛውና የብዙኃን ድርጅቶች የኢሕአፓን መፈክር አንግበው ሰልፍ የወጡበት የ1968ቱ «ሜይ ዴይ» በዓል ወሳኝ ወቅት ነበር ማለት ይቻላል። በዚያን ወቅት ደርግና የግራ ክንፍ አጋሮቹ ኢሕአፓ እስካለ ድረስ እነሱ መኖር እንደማይችሉ በቅጡ ተረዱ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ሁለቱ ባላንጣዎች ሰይፋቸውን መሳል ጀመሩ። በክረምቱ ወራት የታየው አንፃራዊ ዝምታም ዶፍ ያዘለ ዳመና ነበር።

የተፈጥሮው ክረምት ሲያባራ፣ ሰው-ሰራሹ የሽብር ክረምት መስከረም ላይ ጀምሮ ዓመቱን ሙሉ ቀጠለ። ደርግ የኢሕአፓ ታጋዮችንና ደጋፊዎችን በመግደል፣ ኢሕአፓ በደርግ አቀንቃኞችና ባለሟሎች ላይ የሽምቅ ጦርነት በማወጅ ፉክክር ተያያዙ። ከሁለቱም ወገን ታሪኩን ለመጻፍ የሞከሩ ሰዎች ግድያውን የጀመረው ሌላኛው ወገን ነበር የማለት አዝማሚያ ያሳያሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ግድያውን ማን ጀመረው ብሎ መጠየቅ መሣሪያቸውን ስለው ከተፋጠጡ ሁለት ባላንጣ ሠራዊቶች መካከል የመጀመርያውን ተኩስ ማን ከፈተ ብሎ የመጠየቅ ያህል ነው። በዚህም ሆነ በዚያ ፍልሚያው አይቀሬ እየሆነ መጥቷል። አንዴ ከተጀመረ ወዲያም፣ እያሻቀበ እንጂ እየለዘበ አልሄደም።

የመገዳደሉ ዐበይት ምዕራፎች ከሞላ ጎደል የሚከተሉትን ይመስላሉ። በመስከረም 13 ኢሕአፓ እንደ ቀንደኛ ጠላቱ ያየው በነበረው በደርጉ አንደኛ ምክትል ሊቀ መንበር በሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ላይ የግድያ ሙከራ አድርጎ ሳይሳካለት ቀረ። እንዲያውም ከሙከራው ያመለጠው መንግሥቱ ባንድ በኩል ለራሱ ተወዳጅነትን ለማትረፍ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የኢሕአፓን ክስረት ለማሳየት ተጠቀመበት። በዚያው ወር ውስጥ፣ ኢሕአፓ የመኢሶን አመራር አባልና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ባልደረባ የነበረውን ዶ/ር ፍቅሬ መርዕድን ሠንጋ ተራ መኪና ውስጥ ቁጭ ብሎ ሚስቱን በመጠበቅ ላይ ሳለ አድፍጦ በመግደል የመጀመርያውን ዐቢይ ሰለባ አገኘ። በድርጊቱ ያረረው ደርግም (ምናልባት መንግሥቱ ማለቱ ይበልጥ ወደ እውነቱ የተጠጋ ይሆናል) «የአንድ አብዮታዊ ሕይወት በሺ ፀረ-ሕዝቦች ሕይወት ይመነዘራል» የሚል መግለጫ ካወጣ በኋላ የኢሕአፓ አባሎችንና ደጋፊዎችን በገፍ በማሰርና ከታሰሩትም መካከል መርጦ በመረሸን የበቀል እርምጃውን ወሰደ።

የመንግሥት የማጥቃት እርምጃ አፍቃሬ-ኢሕአፓ ተብለው በተፈረጁት የደርግ አባላት ላይ በጥር 26፣ 1969 «አብዮታዊ እርምጃ» ከተወሰደባቸው በኋላ ተጠናክሮ ቀጠለ። በተለይም በሚቀጥሉት ወራት አከታትሎ በወሰዳቸው ሁለት አሰሳዎች ጎቡዕ ገብተው የነበሩትን አንዳንድ የኢሕአፓ መሪዎችንና ቀንደኛ አባላት ከመግደሉና ከማሰሩ ባሻገር፤ ሲቪሉን ትጥቅ በማስፈታት ወኔውን ሰለበው። እነዚህ የ«አሰሳና ድምሰሳ» እርምጃዎች በ«ቀይ ሽብር» ስም ኋላ ለታወጀው ዘግናኝ የታሪክ ምዕራፍ መቅድም መሆናቸው ነው። «ቀይ ሽብር» በዋነኛነት ያነጣጠረው በኢሕአፓ ላይ ሲሆን፤ ቀስ በቀስ ግን የኤርትራ ሕዝባዊ



አርነት ግንባርና ሕዝባዊ ወያኔ አርነት ትግራይ፣ ብሎም ከደርግ ጎራ ያፈነገጠው መኢሶን ሳይቀር የሽብሩ ዒላማ ሆኑ።

ሌሎች የግራ ክንፍ ቡድኖች ኢሕአፓን በክፉ ዐይን እንዲመለከቱት ካደረጋቸው ምክንያቶች አንዱ ተሽቀዳድሞ እራሱን «የላብ አደሩ ፓርቲ ነኝ» ብሎ በማወጁ ነው። የሁሉም ዓላማ በወቅቱ ገኖ በነበረው ማርክሳዊ-ሌኒናዊ አስተሳሰብ የሌኒን ፅንሰ-ሐሳብ ማዕከል የነበረውን ግንባር ቀደም የሠራተኛው መደብ ፓርቲ ሆኖ ለመገኘት ነበር። በሠራተኛው ማኅበራትና በሕዝባዊያን ድርጅቶች የኢሕአፓን ያህል ሰርገው ለመግባት ያልቀናቸው እነዚህ ቡድኖች ኢሕአፓን «የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል» ብለው አጣጣሉት። በነሱ ስሌት፣ የፖለቲካ ፓርቲ ባሕል ባይተዋር በሆነባት ኢትዮጵያ የወዝ አደሩ ግንባር ቀደም ፓርቲን ተጣድፎ ማወጅ ወይ ድንቁርናን ወይ ስግብግብነትን አመልካች ነበር። ስለዚህም ይመስላል በኋላ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ኅብረትን (ኢማሌድኅ) ከፈጠሩት ከነዚህ ፀረ-ኢሕአፓ ከነበሩት የግራ ክንፍ ቡድኖች መካከል አንዳቸውም ቢሆን እራሱን ፓርቲ ብሎ ያልሰየመው። ከስማቸው እንደምንረዳው፣ የመረጡት ስያሜ «ንቅናቄ»፣ «ሊግ»፣ «ትግል»፣ «ድርጅት» ወይም «ሰደድ» ነበር። ሐቀኛው ግንባር ቀደም ፓርቲ ሊመሠረት የሚችለው፣ ሰፊው ሕዝብንና ተራማጅ ኃይሎችን ያለመታከት በማንቃትና በማደራጀት ነው ብለው በአጽንዖት ተከራከሩ። ኢማሌድኅን በየካቲት 1969 ያቋቋሙትም ወደዚሁ የመጨረሻ ግብ አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለመድረስ ነበር።

ይሁን እንጂ፣ ኢማሌድኅ እንደታሰበው የግንባር ቀደሙ ፓርቲ አዋላጅ መሆኑ ቀርቶ አባል ቡድኖቹ ለድርጅታዊ የበላይነት የሚፋለሙበት መድረክ ሆኖ አረፈው። በተለይም መኢሶን ያሳይ በነበረው የበላይነትና የመኩራራ ስሜት የሌሎቹን የተባበረ ጥላቻ አተረፈ። ሽኩቻውና ጥልፊያው በስውር እየቀጠለ እያለ፤ በ1968 ዓ.ም. በኢሕአፓና በመኢሶን መካከል የተደረገውን ዓይነት ክርክር *በአዲስ ዘመን* «አብዮታዊ መድረክ» ላይ በመኢሶንና በሌሎች የኢማሌድኅ አባላት መካከል ተካሄደ። የክርክሩ እምብርት «ዴሞክራቲክ መብቶች» በምን ሁኔታ ይፈቀዱ የሚል ነበር (በገደብ ወይስ ያለገደብ፣ ቀስ ብሎ ወይስ አሁኑኑ)። በሕዝቡ ዘንድ ሰፊ መሠረት ጥያለሁ ብሎ የተማመነው መኢሶን ያለገደብ አሁኑኑ ሲል፣ ሌሎቹ ቡድኖች ግን፣ ከአንድ ዓመት በፊት መኢሶን ኢሕአፓን ይሞግተው እንደነበረው፣ ሰፊው ሕዝብ ሳይነቃና ሳይደራጅ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን መፍቀድ አብዮቱን ለፀረ-አብዮተኞች አሳልፎ መስጠት ነው ብለው ተከራከሩ። እንደዚሁም ኢሕአፓ በጀብደኝነቱ የተወገዘውን ያህል፣ መኢሶን ደግሞ በተራው «እብጠት» ተሰምቶታል ተብሎ ተኰነነ። ሰይፍ እንደተመዘዘባቸው የተረዱት የመኢሶን መሪዎች ብዙም ወዳልተዘጋጁበት የትጥቅ ትግል ለመሰማራት በቡድን ተከፋፍለው በተለያየ አቅጣጫ ዋና ከተማውን ለቀው ለመውጣት ሲሞክሩ እኩሌታዎቹ ተገደሉ፣ የቀሩት ደግሞ ተይዘው ታሰሩ።

ይዘግይ እንጂ ከሰደድ በስተቀር የሌሎቹ ቡድኖች ዕጣ ፈንታ ከመኢሶን የተለየ አልሆነም። ከመኢሶን ብዙም ሳይዘገይ በዘመኑ አነጋገር «የተመታው» ከመኢሶን ጋር ብዙ ድርጅታዊ ትስስር የነበረው ኢጭአት ነበር። ከዚያም በ1971 መባቻ ላይ ተራው ሰደድን ለመቆጣጠር ሰርጎ ገብቷል ተብሎ የተወነጀለው የወዝሊግ ሆነ። ከዚያ በኋላ የሰደድ መሪዎች (ማለትም መንግሥቱ ኃይለ

ማርያምና ሌሎቹ) ወትሮም አቅመ ደካማ የነበረውን ማሌሪድ ለማስወገድ ብዙም አልቸገራቸውም። የማታ ማታም ቀድሞ «ኢትዮጵያ ትቅደም» ብለው የተነሱት ወታደሮች የማርክሲዝም ሌኒኒዝም አውራዎች ለመሆን በቁ። ወታደራዊ ኮሚቴ የነበረው ደርግ እራሱን ለወዝ አደሩ ግንባር ቀደም ፓርቲነት አጨ።

### «ከጓድ መንግሥቱ አብዮታዊ አመራር ጋር ወደፊት!»

የኢትዮጵያ አብዮት ታሪክ ከመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ስብዕና ጋር በአያሌው ተቆራኝቶ ቆይቷል። ሰኔ 21፣ 1966 በቃል ኪዳን ከተሳሰሩት የደርግ ባልደረቦቹ አንፃርም ሆነ ከጊዜ በኋላ አጋር ከሆኑት ሲቪል ምሁራን ጋር ሲወዳደር፣ እንደሱ አሻራውን በአብዮቱ ላይ ትቶ ያለፈ ግለሰብ የለም። በ1980 ዓ.ም. መባቻ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሲታወጅ፣ ከዚያ በፊት ማናቸውም የኢትዮጵያ ገዥ አይቶ የማያውቀው ሥልጣን ጫፍ ላይ ለመድረሱ ጉልህ ማስረጃ ሆነ። የሚደንቀው ከአብዮት በፊት ብዙም ሰው የማያውቀው የነበረው ሻለቃ እንዲህ ያለ ፍፁማዊ ሥልጣን ለማግኘት መብቃቱ ብቻ ሳይሆን እዚያ ከመድረስ የሚያቆመው አንዳችም ኃይል ያለ አለምመስሉ ነው። እንዲህ ባላጋራዎቹን አንድ ባንድ ደምስሶ ገዝፎ ለመውጣት ያስቻሉት ሁኔታዎች ነባራዊም ግላዊም ነበሩ ማለት ይቻላል። ባንድ በኩል፣ ወትሮም ከንጉሣዊ አገዛዝ ውጭ ሌላ ሥርዓት የማያውቀው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባሕል ደርግ ለማስፈን ከሞከረው የቡድን አመራር ይልቅ ለአምባገነን አገዛዝ ያመቸ ነበር። በዚያ ላይ ደግሞ በኦርቶዶክሳዊ ቀኖና ላይ የተዋቀረ ማርክሳዊ-ሌኒናዊ ቀኖና ሲታከልበት አገዛዙ ርዕዮተ ዓለማዊ ምልዓት አገኘ። በዚህ ረገድ የሩሲያና የኢትዮጵያ የታሪክ ሂደት የመመሳሰል ባሕሪ ነበረው። ሁለቱም አፄያዊ አገዛዝና የኦርቶዶክስ እምነት ሥር የሰደዱባቸው አገሮች ነበሩ። በሁለቱም ሀገሮች፣ አብዮት አምባገነን መሪን ወለደ፤ በሩሲያ ስታሊን፣ በኢትዮጵያ መንግሥቱ ኃይለማርያም።

ይህን ነባራዊ ሁኔታ ማመልከት ግን የግለሰቡን የተለየ ሥልጣን የማካበት ክህሎት ለማንኳሰስ አይደለም። በዚህ ረገድ በሱና በስመ ሞክሼው በብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መካከል የነበረው ልዩነት ለማንኛውም አነፃፃሪ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነው። ጄኔራሉ የ1953ቱን መፈንቅለ መንግሥት የመራበት ስልትና ሻለቃው (ኮሎኔሉ) ሥልጣን ላይ የተደላደለበት መንገድ የሰማይና መሬትን ያህል የተራራቁ ናቸው። የመጀመርያው ጥርጣሬና ለዘብተኝነት የተመላበት፣ የኋለኛው ፍጥነትና ጭካኔ (ወይም በ«አብዮታውያን» ቋንቋ «ቆራጥነት») መለዮው የሆነ ነበሩ። በቅርቡ ስለ ዘመነ ደርግ የተጻፉ





6.6 ትህትናን ተላብሶ የሚታየው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም (ከግራ ሦስተኛ)። ነገር ግን በፎቶው ከሚታዩት መካከል አራቱ የሱ ሰለባ የሆኑ ናቸው፡- ከግራ ወደ ቀኝ፣ ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ፣ ሻለቃ ሲሣይ ሀብቴ፣ ሌተና ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ (የቆመው)፣ ሌተና ኮሎኔል አጥናፉ አባተ (ወደ ተፈሪ ቀረብ ያለው)

መጻሕፍት የሚስማሙበት ነገር ቢኖር ኮሎኔሉ ሰዎችንና ሁኔታዎችን በፍጥነት ለመገምገምና ለመመዘን የነበረው ችሎታ ነው። ሌላው ከዙፋን ካወረደው ንጉሠ ነገሥት ጋር የሚያመሳስለው ባሕርዩ ደግሞ እውነተኛ ስሜቱንና ውጥኑን የመሸፈን ተሰጥዎው ነው። ሞት የደገሰላቸውን ሰዎች በቁጣ ሳይሆን በፈገግታ ነበር የሚያስተናግደው። ወደ ደርግ ብቅ ካለበት የመጀመርያዪቱ ቀን ጀምሮ የተደቀነበትን የሥልጣን ሽኩቻ በድል ሊወጣ የቻለው ብዙ ተመልካቾች በሚስማሙበት ብልጠቱ (ወይም አራዳነቱ) ነበር ማለት ይቻላል።

ብዙም አጠያያቂ ያልሆነው ብሔራዊ ስሜቱና እንደበተ ርቱዕነቱም በደርግ ውስጥ (በተለይ በወታደሮቹና ባለሌላ ማዕረጎች መካከል) እና በሕዝቡም አካባቢ ተከታዮች ሊያስገኙለት ችሏል። በደርግ ውስጥ ከሚገኙት መኰንኖች አብዛኛዎቹ እንደሱ ከሐረር አካዳሚ መኰንኖች ጋር የጉረጥ ይተያዩ የነበሩት የሆለታ ምሩቃን መሆናቸውም ተጨማሪ የድጋፍ መሠረት ሆኖለት ነበር። ሌሎች የደርግ አባላት በተለይ በነዚያ የመጀመርያዎቹ የቀውጢ ቀናት እውር ድንብራቸውን በአብዮት ማዕበል ሲናወጡ ወዲት አቅጣጫ መኪድ እንዳለበት አንፃራዊ በሆነ መልኩም ቢሆን መላ የነበረው እሱ ነበር። «ኢትዮጵያ ትቅደም!» የሚለውን መፈክር በመወርወር ነገሩን ፈር ያስያዘውም እሱ እንደሆነ ይነገራል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ መንግሥቱ የፖለቲካ ሥልጣን ከጠመንጃ አፈሙዝ እንደሚገኝ አሳምሮ ያውቅ ነበር። ያንን ለመጨበጥ ብቻ ሳይሆን ይዞ



6.6 ትህትናን ተላብሶ የሚታየው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም (ከግራ ሦስተኛ)። ነገር ግን በፎቶው ከሚታዩት መካከል አራቱ የሱ ሰለባ የሆኑ ናቸው።- ከግራ ወደ ቀኝ፣ ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ፣ ሻለቃ ሲሣይ ሀብቴ፣ ሌተና ጄኔራል ተፈሪ ባንቴ (የቆመው)፣ ሌተና ኮሎኔል አጥናፉ አባተ (ወደ ተፈሪ ቀረብ ያለው)

መጻሕፍት የሚስማሙበት ነገር ቢኖር ኮሎኔሉ ሰዎችንና ሁኔታዎችን በፍጥነት ለመገምገምና ለመመዘን የነበረው ችሎታ ነው። ሌላው ከዙፋን ካወረደው ንጉሠ ነገሥት ጋር የሚያመሳስለው ባሕርዩ ደግሞ እውነተኛ ስሜቱንና ውጥኑን የመሸፈን ተሰጥዎው ነው። ሞት የደገሰላቸውን ሰዎች በቁጣ ሳይሆን በፈገግታ ነበር የሚያስተናግደው። ወደ ደርግ ብቅ ካለበት የመጀመሪያዪቱ ቀን ጀምሮ የተደቀነበትን የሥልጣን ሽኩቻ በድል ሊወጣ የቻለው ብዙ ተመልካቾች በሚስማሙበት ብልጠቱ (ወይም አራዳነቱ) ነበር ማለት ይቻላል።

ብዙም አጠያያቂ ያልሆነው ብሔራዊ ስሜቱና አንደበተ ርቱዕነቱም በደርግ ውስጥ (በተለይ በወታደሮቹና ባለሌላ ማዕረጎች መካከል) እና በሕዝቡም አካባቢ ተከታዮች ሊያስገኙለት ችሏል። በደርግ ውስጥ ከሚገኙት መኰንኖች አብዛኞዎቹ እንደሱ ከሐረር አካዳሚ መኰንኖች ጋር የኵሪጥ ይተያዩ የነበሩት የሆለታ ምሩቃን መሆናቸውም ተጨማሪ የድጋፍ መሠረት ሆኖለት ነበር። ሌሎች የደርግ አባላት በተለይ በነዚያ የመጀመሪያዎቹ የቀውጢ ቀናት እውር ድንብራቸውን በአብዮት ማዕበል ሲናወጡ ወዴት አቅጣጫ መኬድ እንዳለበት አንፃራዊ በሆነ መልኩም ቢሆን መላ የነበረው እሱ ነበር። «ኢትዮጵያ ትቅደም!» የሚለውን መፈክር በመወርወር ነገሩን ፈር ያስያዘውም እሱ እንደሆነ ይነገራል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ መንግሥቱ የፖለቲካ ሥልጣን ከጠመንጃ አፈሙዝ እንደሚገኝ አሳምሮ ያውቅ ነበር። ያንን ለመጨበጥ ብቻ ሳይሆን ይዞ

ለመቆየት ወታደራዊ ኃይልን ከማፈርጠም ሌላ አማራጭ እንደሌለ ያውቅ ነበር። ለዚህም በመጀመርያ አለኝታው የነበረው ደርግ ውስጥ ራሱ የሚወክለው የ3ኛ ክፍለ ጦር ነው። በመስከረም 1967 በመሐንዲስ ክፍል የተነሳውን ተቃውሞ የደመሰሰለትም ይኸው ጦር ነው። ከዚያ በማስከተልም በተለይ ሽምቅ ተዋጊዎችን የመቋቋም ጣምራ ተልእኮ የነበረውንና «ነበልባል» የተሰኘውን ክፍለ ጦር አቋቋመ። ሥልጣኑ እያደገ፣ ተቃዋሚውም እየበዛ ሲሄድ ደግሞ እንደ ተናካሽ ውሻ ነቅቶ የሚጠብቀውን ልዩ የቤተ መንግሥት ጦር አደራጀ። በግንቦት 1981 የተሞከረውን መፈንቅለ መንግሥት በማምከኑ ረገድ ቁልፍ ሚና የተጫወተውም ይኸው «ቀልብ» ጦር ነው። መንግሥቱ ጦሩን ከማደራጀት ጎን ለጎን የፀጥታ ጥበቃውንም አጠናክሮ ነበር። በዚህ ረገድ መንግሥቱን አምባገነናዊ ሥልጣን ለማጎናፀፍ ዐቢይ ሥፍራ የነበራቸው ሁለት ግለሰቦች መጥቀስ ቢያስፈልግ በጥር 26፣ 1969 በተደረገው መፈንቅለ መንግሥት ወቅት ሕይወቱ ያለፈችው ኮሎኔል ዳንኤል አስፋውና ኋላ የብሔራዊ ደህንነት ሚኒስትር ለመሆን የበቃው ኮሎኔል ተስፋዬ ወልደ ሥላሴ ነበሩ።

ይህ ስለተባለ ግን መንግሥቱ እንደ ዑጋንዳው ኢዲ አሚን ዳዳ ወይም እንደ ማዕከላዊ አፍሪቃ ሬፐብሊኩ ቦካሳ ያፈጠጠና ያገጠጠ ወታደራዊ አምባገነን መሪ ብቻ ነበር ማለት አይደለም። የሥልጣኑ አለኝታ ለነበረው ወታደራዊ ጡንቻ ከግራ ክንፉ ቡድን የቀሰመውን ርዕዮተ ዓለማዊ ሽፋን ሰጥቶት ነበር። በተለምዶ ከላይ ወደታች ከሚፈሰው ወታደራዊ እዝ ጎን ለጎን (እንዲያውም ከዚያ በላይ ማለት ይቻላል) ካድሬዎችና ኮሚሳሮች የሚገኙበት የእዝ ሰንሰለት አዋቅሮ ነበር። ይህ አሰራር በሙያው በሰለጠኑት የጦር አዛዦች ውሳኔዎች ላይ የፖለቲካ ኮሚሳሮች ለሚያደርጉት ጣልቃ ገብነት በር በመክፈቱ በወታደራዊ ዘመቻዎች ላይ የነበረው አሉታዊ ተፅዕኖ ግልፅ ነበር። በዚያው መጠን ግን መንግሥቱ በወታደራዊው መዋቅር ላይ የነበረውን የበላይነት እንዳጠናከረለት እሙን ነው።

እንግዲህ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ክህሎቶችና ሁኔታዎች - ልማድ፣ ተክለ ሰውነትና ለፖለቲካ ሥልጣን ቁልፍ የሆኑት ቅድመ ሁኔታዎች መመቻቸት - ናቸው መንግሥቱን የበላይነት ሰጥተውት ተፎካካሪዎቹን፣ ተቃዋሚዎቹን ተራ በተራ በሚያስገርምና በሚያስለች ድግግሞሽ ለማስወገድ ያስቻሉት። በዚህ ረገድ በንቃትና በትጋት ለሚያሳድደው ፍፁማዊ ሥልጣን የመጀመሪያውን መሰናክል በኅዳር 1967 የደርጉን ሊቀ መንበር ሌተና ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን በማስወገድ ተወጣው። የጄኔራሉ መወገድ ግልፅ ያደረገው አንድ ነገር ቢኖር በሠራዊቱ ዘንድ የነበረው ተወዳጅነት ሁለት ስለት ያለው ቢላዎ እንደሆነ ነው። የደርግ አባላት እነዚያን የመጀመሪያዎቹን የቀውጢ ወራት ጄኔራሉን ከለላ አድርገው ለመግዛት ያበቡትን ያህል፣ ጄኔራሉም የራሱ የሥልጣን ፍላጎትና ቀመር ነበረው። የሁለቱ ስሌቶች ተቃርኖ ነው ያንን የደም ጎርፍ ምዕራፍ መክፈቻ ሊሆን የበቃውን ክስተት አይቀሬ ያደረገው።

የጄኔራሉ ሞት አዲስ ምዕራፍ ከፈተ የሚባለውም ያለምክንያት አይደለም። ያቺ ቀን ደርግ ካለፈው ሥርዓት ጋር የሚያገናኘውን እትብቱን የቆረጠባት ቀን ነበረች ማለት ይቻላል። ለዚህም ጉልህ ማስረጃው በዚያት ምሽት እስር ላይ የነበሩትን የቀድሞ መኳንንትና ሹማምንት በቅጽበታዊ ውሳኔ አውጥቶ መረሸኑ ነው። በሌላ መልኩም ከጄኔራል አማን ተሞክሮ





6.7 ሦስቱ ከፍተኛ የደርግ ሹማምንት፦ (ከግራ ወደ ቀኝ) መንግሥቱ፣ አጥናፉና ሲሣይ

በመማር ደርግ በምትኩ የሚያስቀምጠውን ሰው ለመምረጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ከማድረጉም በላይ በመጨረሻም ለሊቀ መንበርነት የመረጠውን የሌተና ጄኔራል ተፈሪ ባንቲን ሥልጣን የተገደበ አደረገው። የጄኔራል አማን መወገድ በኤርትራ ጉዳይም ላይ አሉታዊ እንድምታ ነበረው። በጥያቄው ላይ የነበረው ለዘብተኛና ሰላማዊ አቀራረብ ከጄኔራሉ ጋር ተወግዶ በምትኩ በኤርትራውያን ሽማቂዎቹ በኩል «ነፃነት ወይም ሞት»፣ በደርግ በኩል ደግሞ «አንድነት ወይም ሞት» የሚሉ ተፃራሪ አቋሞች ነግሠው ኤርትራን የጦርነት አውድማ አደረጓት።

ከጄኔራል አማን መገደል በኋላ ለሁለት ዓመት ያህል ይህ ነው የሚባል የፖለቲካ ግድያ አልነበረም። ምናልባትም በነዚህ ዓመታት ደርግ ሙሉ ትኩረቱን እንደ መሬት አዋጅ ያሉትን ሥር-ነቀል እርምጃዎች በመውሰድ ላይ አድርጎ ስለነበር ይሆናል። በነዚህ እርምጃዎች ዙርያ ደርግ ውስጥ ሙሉ ስምምነት ነበረ ባይባልም አደባባይ የወጣ ግልፅ የሆነ መከፋፈል አልነበረም። በ1968 መጨረሻ ላይ ግን የደርግ የግድያ አባዜ እንደገና አገረሸ። የዚህም ዋነኛ ሰለባ የደርጉ የፖለቲካና የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበረው የአየር ኃይሉ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ ነበር። በምሕንድስና የማስትሬት ዲግሪ የነበረውንና እንደበተ ርቱዑን ሻለቃ መንግሥቱ የፖለቲካ ተቀናቃኙ አርጎ ይገምተው ስለነበር በጥርጣሬ ዐይን ነበር የሚመለከተው። ስለሆነም በአብዮቱ ላይ አሲሯል በሚል ክስ የጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲረሸን አደረገው።

የሚቀጥለው ዘመቻ የሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ ግብረ አበሮች ናቸው በተባሉት ኤርትራ የሚገኘው የሁለተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ብረጋዴር ጄኔራል



6.7 ሦስቱ ከፍተኛ የደርግ ሹማምንት፦ (ከግራ ወደ ቀኝ) መንግሥቱ፣ አጥናፉና ሲሣይ

በመማር ደርግ በምትኩ የሚያስቀምጠውን ሰው ለመምረጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ከማድረጉም በላይ በመጨረሻም ለሊቀ መንበርነት የመረጠውን የሌተና ጄኔራል ተፈሪ ባንቴን ሥልጣን የተገደበ አደረገው። የጄኔራል አማን መወገድ በኤርትራ ጉዳይም ላይ አሉታዊ እንድምታ ነበረው። በጥያቄው ላይ የነበረው ለዘብተኛና ሰላማዊ አቀራረብ ከጄኔራሉ ጋር ተወግዶ በምትኩ በኤርትራውያን ሽማቂዎቹ በኩል «ነፃነት ወይም ሞት»፣ በደርግ በኩል ደግሞ «አንድነት ወይም ሞት» የሚሉ ተፃራሪ አቋሞች ነግሠው ኤርትራን የጦርነት አውድማ አደረጓት።

ከጄኔራል አማን መገደል በኋላ ለሁለት ዓመት ያህል ይህ ነው የሚባል የፖለቲካ ግድያ አልነበረም። ምናልባትም በነዚህ ዓመታት ደርግ ሙሉ ትኩረቱን እንደ መሬት አዋጅ ያሉትን ሥር-ነቀል እርምጃዎች በመውሰድ ላይ አድርጎ ስለነበር ይሆናል። በነዚህ እርምጃዎች ዙርያ ደርግ ውስጥ ሙሉ ስምምነት ነበረ ባይባልም አደባባይ የወጣ ግልፅ የሆነ መከፋፈል አልነበረም። በ1968 መጨረሻ ላይ ግን የደርግ የግድያ አባዜ እንደገና አገረሸ። የዚህም ዋነኛ ሰለባ የደርጉ የፖለቲካና የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበረው የአየር ኃይሉ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ ነበር። በምሕንድስና የማስትሬት ዲግሪ የነበረውንና እንደበተ ርቱዑን ሻለቃ መንግሥቱ የፖለቲካ ተቀናቃኝ አርጎ ይገምተው ስለነበር በጥርጣሬ ዐይን ነበር የሚመለከተው። ስለሆነም በአብዮቱ ላይ አሲሯል በሚል ክስ የጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲረሸን አደረገው።

የሚቀጥለው ዘመቻ የሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ ግብረ አበሮች ናቸው በተባሉት ኤርትራ የሚገኘው የሁለተኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ብሪጋዴር ጄኔራል

ጌታቸው ናደውና የመቶ አለቃ በውቀቱ ካሣና የመቶ አለቃ ስለሺ በየነ በተባሉ ሁለት የደርግ አባሎች ላይ አነጣጠረ:: ጄኔራሉ ልክ እንደ አማን ቤቱ ተከቦ ተታኩሶ ሲሞት ሁለቱ የደርግ አባሎች ወደ ትውልድ አገራቸው ጎጃም ሸሽተው እነሱን የሚያሳድድ ጦር ተልኮ ተይዘው ተገደሉ:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ የእድገት በኅብረት ዘመቻ አስተባባሪ የነበረው ሻለቃ ኪሮስ ዓለማየሁም ተይዞ በእስር ላይ እንዳለ ሕይወቱን እንዳጠፋ ይነገራል:: በተለመደው የማደናገር ባሕሪው ደርግ ከነዚህ ላይ ከተጠቀሱት ከፍተኛ የፖለቲካ ባላንጣዎች ጋር ደብለቅ በማድረግ ስድስት የሚሆኑ ነጋዴዎችንም በርበሬ ደብቀው ዋጋ በማስወደድ የኤኮኖሚ አሻጥር ፈፅመዋል ብሎ የረሸነውም በዚህ ወቅት ነበር::

የሲሳይ መረሸን የመንግሥቱን ሥልጣን ካልገቱት የነሱም ተራ ሩቅ እንዳልሆነ ለተቀሩት የደርግ አባላት የሚያመለክት ቀይ መብራት ነበር:: ይህንንም በማጤን ይመስላል በ1969 ዓ.ም. መጀመርያ ወራት ከብዙ ምክክር በኋላ በደርግ አወቃቀር ላይ መሠረታዊ ለውጦች የሚያመጣ እርምጃ የተወሰደው:: በአዲሱ አወቃቀር መሠረት የደርግ አባላት በሙሉ የሚሳተፉበት ሸንጎ ዋናው የሥልጣን አካል ሲሆን በተዋረድ ደግሞ የማዕከላዊ ኮሚቴና ቋሚ ኮሚቴ ተቋቋሙ:: በተለይም የደርጉ ሊቀ መንበርና ሁለቱ ምክትል ሊቃነ መናብርት ኃላፊነትና ሥልጣን ከመቼውም በበለጠ በግልፅ ተደንግጎ ነበር:: እስከዚያን ጊዜ ድረስ ለወግ ብቻ ተቀምጦ የነበረው የደርጉ ሊቀ መንበር ጠንከር ያለ ሥልጣን ሲሰጠው፣ ባንፃሩ የተቀዳሚ ምክትል ሊቀ መንበሩ (ማለትም የመንግሥቱ) ሥልጣን በመሠረቱ ብዙም ፋይዳ ያልነበረውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሊቀ መንበርነት በመምራት ተገድቦ ነበር:: በሌላ በኩል የደርጉ ዋና ጸሐፊ ሥልጣን ተጠናክሮ የደርግ ጽሕፈት ቤቱን ሥራ ከመምራትም ባሻገር እስከዚያን ጊዜ ድረስ ከተቀዳሚ ሊቀ መንበሩ ጋር ተቆራኝቶ የነበረውን የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽሕፈት ቤትንም እንዲቆጣጠር ተደረገ::

ለመንግሥቱና አጋሮቹ ይህ አዲስ የደርግ አወቃቀር በብዙ መልኩ የማይዋጥላቸው ሲሆን፣ በተለይም ያንገሸገሻቸው እርምጃው የተወገዘውን ኢሕአፓን የሚያጠናክር መስሎ ስለታያቸው ነው:: ለዚህ ጥርጣሬያቸው ምክንያት የሆነው በዚህ የማዋቀር ተግባር ግንባር ቀደም ተዋንያን የነበሩት በኢሕአፓ አባልነትና ደጋፊነት የሚጠረጠሩት የደርጉ የኤኮኖሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበረው ሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤልና በአዲሱ መዋቅር የደርጉ ዋና ጸሐፊ የሆነው ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ መሆናቸው ነው::

አስጊ እየሆነ የመጣውን መንግሥቱን እጅና እግሩን አስረነዋል፣ ከእንግዲህ አልቆለታል፣ ብለው በማመን ባላንጣዎቹ ሥራቸውን ተዝናንተው ማካሄድ ቀጠሉ:: አድብቶ የመልስ ምት ሊሰጣቸው እንደሚችል ከቶም ከግምት አላስገቡም:: በተለይም ትልቁ ስሕተታቸው፣ የፀጥታውን ክፍል የመንግሥቱ የሆለታ ጓደኛና ደርግ ከተመሠረተ ጀምሮም ቀኝ እጁ በሆነው በኮሎኔል ዳንኤል አስፋው እጅ እንዳለ መተዋቸው ነው:: የተፈራውም አልቀረ፣ ጥር 26፣ ቀን 1969 መንግሥቱና ዳንኤል ቅፅበታዊ የመልሶ ማጥቃት እርምጃቸውን ወሰዱ:: በስብሰባ ሰበብ የሚፈልጓቸውን ባላንጣዎቻቸውን ባንድ ክፍል ውስጥ እንዲገኙ ካደረጉ በኋላ የመፈንቅለ መንግሥት ድራማቸውን አከናወኑ:: መንግሥቱ በሐሰት የስልክ ጥሪ ከስብሰባው አዳራሽ እንዲወጣ ሲደረግ፤ የታጠቁ ወታደሮች ገብተው ተቀናቃኞቹን በስም እየጠሩ ወደሌላ ክፍል ወስደው ገደሏቸው:: በዚህ



ፈጣን እርምጃ አማካይነት ከተረሸኑት ሰባት የደርግ አባላት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፤ ሌተና ጄኔራል ተፈሪ ባንቴ፣ የደርጉ ሊቀ መንበር፤ ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ፣ የደርጉ ዋና ጸሐፊ፤ ሻምበል ሞገስ ወልደ ሚካኤል፣ የደርጉ የኤኮኖሚ ኮሚቴ ሊቀ መንበርና ሌተና ኮሎኔል አሥራት ደስታ፣ የደርጉ የማስታወቂያ ኮሚቴ ሊቀ መንበር::

በዚህ ቅፅበታዊ እርምጃ አማካይነት መንግሥቱና አጋሮቹ የማያሻማ ድልን ተጎናፀፉ:: አብዮቱም «ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል» ተባለ:: የነመንግሥቱን የድል ጽዋ በመጠኑም ቢሆን ያደፈረሰባቸው፣ የዳንኤል ምክትልና በስውር ግን የነ ዓለማየሁ ደጋፊ የነበረው ሻምበል ዮሐንስ ምስክር ሁኔታውን በመጠርጠር ሳይቀድሙኝ ልቅደም በማለት ዳንኤልንና የነመንግሥቱ አለኝታ የነበረውን ዶ/ር ሰናይ ልኬን በመግደሉ ነው:: ይሁን እንጂ ደርጉ ውስጥ ለጊዜው የበላይነት አግኝተው የነበሩትን ኃይሎች ካስወገዱ በኋላ፣ መንግሥቱና አጋሮቹ በኢሕአፓ ላይ «ነፃ እርምጃ» ከመውሰድ የሚገታቸው ምንም ማዕቀብ አልነበረም:: በተንዳኝም የመንግሥቱ አምባገነንነት አግጦ መውጣት ጀመረ:: ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ መንበር በሚል ሽፋን ከጄኔራል ጀርባ ማሴሩ ቀረና ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ አደባባይ ወጣ:: የደርጉ ሊቀ መንበርነትን ብቻ ሳይሆን፣ወደ ሞት ዓለም የሸኛቸው ባላንጣዎቹ ሳያውቁ ያመቻቹለትን የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥነትንም ደርቦ ያዘ:: የደርጉ ሥራ አስፈፃሚ አካል ይሆናል ተብሎ የታቀደውን ቋሚ ኮሚቴም በራሱ ታማኞች ገጠገጠው::

በመንግሥቱና በፍፁማዊ ሥልጣን መካከል ጋሬጣ ሆኖ ያስቸገረው አንድ ሰው ብቻ ነበር፤ ምክትል ሊቀ መንበሩ ሌተና ኮሎኔል አጥናፉ አባተ:: በመሠረቱ ለመንግሥቱ፣ ምክትል ሊቀ መንበሩ ከአደገኛነት ይልቅ የአዋኪነት ባሕሪ ነበር የነበረው:: ይሁን እንጂ በተለይ ጥር 26 በተወሰደው እርምጃ ላይ የገለፀውን ቅሬታ መንግሥቱ አልወደደለትም:: እንዴት እንደሚያስወግደው ሲያደባ፣ ዓመት ሳይሞላ የአጥናፉ የፖለቲካ የዋህነት መንግሥቱ እግር ሥር ጣለው:: በኅዳር ወር ውስጥ እንደገና ሆን ተብሎ የተጠራ በሚመስል የደርጉ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ አጥናፉ በተቃዋሚዎች ላይ የሚወሰደውን እርምጃ ከመቃወሙም በላይ፣ ደርግ ቀኖና እያደረገ የመጣውን የሶሻሊዝምን መሠረታዊ መርሆዎች የሚፃረሩ አስተያየቶች ሰነዘረ:: የመንግሥቱ አሽቃባጮች ይህን እድል በመጠቀም እየተቀባበሉ ካብጠለጠሉት በኋላ እሱም እንዲረሸን ተፈረደበት:: ከማንኛውም የደርግ አባል በላይ ሕይወቱ ከደርግ አፈጣጠር ጋር የተሳሰረው የአጥናፉ መወገድ የደርግን መክሰም የሚያረጋግጥ ታሪካዊ እርምጃ ነበር::

ከዚያ በኋላ የነገሠው የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ነው:: መንግሥቱ በእሺ ባዮችና አጫፋሪዎች ታጀበ:: ይህን ስዕል ትንሽ የሚቀይረው ሁኔታ ቢኖር አልፎ አልፎ የነፃነት ባሕሪ ለማሳየት የሚጥረው የሻምበል ፍቅረ ሥላሴ ወግ ደረስ ሁኔታ ነው:: ከጥር 26 በፊት በደርግ ውስጥ ጉልህ የሥራ ድርሻ ያልነበረው ፍቅረ ሥላሴ፣ እንደሚወራው በስሕተት ከመረሸን ከዳነ በኋላ የደርጉ ዋና ጸሐፊና ቆይቶም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን በቃ::

የጥር 26ቱን ክስተት ተከትሎ የደርግ መንግሥት ከኮሙኒስቱ ጎራ ጋር ይበልጥ እየተቆራኘ ሲሄድ፤ ከምዕራቡ ዓለም፣ በተለይም ከአሜሪካ፣ ጋር ያለው

ትስስር እየላላ ሄደ። የመንግሥቱን ድል እንደ ተራማጅ ኃይሎች ድል ያዩት የኮሙኒስት አገሮች በሥልጣን ትግሉ ውጤት ደስታቸውን ለመግለፅ የመጀመርያዎቹ ነበሩ። የኩባው መሪ ፊደል ካስትሮ ከዚያም አልፎ በሚያዝያ ወር ኢትዮጵያን ከመጎብኘቱም በላይ፣ ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያና ደቡብ የመን በኮንፌዴሬሽን የማስተሳሰር ሐሳብም ሰንዝሮ ነበር። በአንፃሩ፣ አገሪቱ ከአሜሪካ ጋር የነበራት ቅርብ ግንኙነት ፈፅሞ ተቋረጠ፤ በ1945 ተፈርሞ የነበረው የጋራ ትብብር ስምምነትም ተሰረዘ። የአሜሪካ ወታደራዊና ባሕላዊ ተቋማትም ተዘጉ። በግንቦት 1969 መንግሥቱ ሶቪየት ኅብረትን በኦፊሲዬል ለመጎብኘት ወደ ሞስኮ ተጉዞ ከአዲስ አጋሩ ጋር የኢኮኖሚ፣ የባሕልና የወታደራዊ ትብብር ስምምነቶች ሲፈራረም፣ አዲሱ አሰላለፍ ሕጋዊ መሠረቱን አገኘ።

እነዚህ ክስተቶች በአካባቢው ይታይ ከነበረው የአሰላለፍ ለውጥ ጋር የተቆራኙ ነበሩ። አሜሪካ ከኢትዮጵያ እየተራራቀች በሄደች መጠን፣ በዚያድ ባሬ ከሚመራው የሶማሌ መንግሥት ጋር እየተቀራረበች መጣች። በሌላ ወገን ደግሞ ሶቪየቶች ወደኢትዮጵያ ግዛት የመስፋፋት ዓላማውን አላጥፍ ያላቸውን ዚያድ ባሬን ገሸሽ አድርገው ዕድላቸውን ከኢትዮጵያ ጋር ማስተሳሰሩን መረጡ። ወደ 1969 ማብቂያ ላይ፣ ካስትሮ አናፍሶት የነበረው የአካባቢው መንግሥታት ኮንፌዴሬሽንም በኢትዮጵያና ሶማሊያ መካከል በተቀሰቀሰው ጦርነት የመድፍ ግባት እንደ ጉም ተኖ ጠፋ።

ጦርነቱ ራሱ መጀመርያ የምዕራብ ሶማሊያ አርነት ግንባር ተብሎ የሚታወቀው ድርጅት ታጣቂዎች ወደ ኦጋዴን ሰርገው በመግባት በሚያደርጉት ጥቃት ተከፈተ። የነሱን ዱካ ተከትሎ የመጣው መደበኛ የሶማሌ መንግሥት ጦር ባጭር ጊዜ ውስጥ ቆልፍ ቦታዎችንና ከተማዎችን ለመቆጣጠር በቃ። ይሁንና ይህ የሶማሌ ጦር ድል ከጥቂት ወራት በኋላ ሙሉ በሙሉ ተቀለበሰ። ለዚህ መቀልበስም ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረጉት ሁለት ዐቢይ ነገሮች ናቸው፣ ባንድ ወገን በኢትዮጵያ በኩል ባጭር ጊዜ ውስጥ ወደ 300000 የሚገመት የሚሊሺያ ጦር አሠልጥኖ ለማዝመት መቻሉና በሌላ በኩል ደግሞ በሶቪየት የጦር አዛዦች የሚመራ ከኩባና ከደቡብ የመን የተውጣጣ ጦር ያደረገው ፈጣንና ወሳኝ የጦር እርዳታ። የሶማሌ ጦር ድል ተመትቶ ሲበተን፣ የሶማሌ የመስፋፋት ፖሊሲ መቼም አይቶ የማያውቀውንና አሻራው እስካሁን ያልጠፋውን ከባድ ሽንፈት ተከናነበ። ባንፃሩ፣ ሁለት ወታደራዊ ሥፍራዎች በኢትዮጵያ ወታደራዊ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሥፍራ ለማግኘት በቁ። እነሱም፣ ሚሊሺያ ጦሩ የሰለጠነበት ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ የሚገኘው ታጠቅ የተሰኘው የጦር ማሠልጠኛ ጣቢያና በኦጋዴን ጦርነት ወሳኝ ፍልሚያ የተካሄደባት ካራ ማራ ናቸው።

የኢትዮጵያ ጦር በኦጋዴን ጦር ግንባር ያገኘው ድል፣ በአገር ውስጥ በነበረው የሥልጣን ትግልም ላይ ትልቅ እንደምታ ነበረው። ወራሪውን ጦር ተረባርቦ ለማስወጣት ደርግ «የእናት አገር ጥሪ» ባወጀበት ወቅት፣ ዘመቻውን የተቃወመው ኢሕአፓ በዚህ አቋሙ ውድቀቱን አፋጠነ። በተቃራኒው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የወታደራዊ ድሉ አንደኛ ተጠቃሚ ሆኖ በመውጣት የሥልጣን ኮርቻውን አደላደለ። «ቪቫ መንግሥቱ!» «ከጎድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እብዮታዊ አመራር ጋር ወደፊት!» የሚሉት የአምባገነንነት ማጋፈሪያ መፈክሮችም መሰማት የጀመሩት በዚህ ድል ማግስት ነው።



እንግዲህ፣ 1970 ዓ.ም. ሲጋመስ፣ መንግሥቱ ደርግ ውስጥ ያሉትን ተቀናቃኞች በሙሉ (የተጋፉትንም ሆነ የጠረጠራቸውን) አስወግዷል። ከሲቪሉ ወገን የተነሱበትን ተቃዋሚዎችንም ፀጥ አስደርጓል። የውጭ ወረራም ከፋኛ ተመቷል። አሁንም መፈታተናቸውን የቀጠሉት በሰሜን ግንባር የነበሩት የኤርትራ ተዋጊዎች ብቻ ናቸው። እነሱም ቢሆኑ፣ በምሥራቁ ግንባር ድልን የተጎናፀፈው የደርግ ጦር «የምሥራቁ ድል በሰሜን ኢትዮጵያም ይደገማል!» ብሎ ፊቱን ወደ ሰሜን ግንባር ሲያዞር፣ ዕድሚያቸው አጭር መስሎ ታየ።

አሁን መንግሥቱ የቀረው፣ በብልጠቱና በዕድል ያገኘውን ኃይል ተቋማዊ መሠረት መስጠቱ ነው። ይህም ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ አልነበረም። ፍፁማዊ ሥልጣኑን ያረጋገጠለት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በ1980 እስከሚታወጅና የተደላደለ የሥልጣን መዋቅሩ እስከሚዘረጋ ድረስ አሥር ዓመት ያህል ፈጅቷል። ከዚያ በፊት የሚጠብቀው ዐቢይ ተግባር «እንከን የለሹ»ን ግንባር ቀደም ፓርቲ ማቋቋም ነበር። ከላይ እንዳየነው፣ ለዚሁ ፓርቲ አስኳል ይሆናል ተብሎ የታሰበው ኢማሌድን የአባላቱ እርስ በርስ አለመተማመን ሰለባ ሆኖ ፈርሷል። ከዚህም ሂደት የተገኘው ትምህርት የተለያዩ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅቶችን በማዋሐድ የሠርቶ አደሩን ፓርቲ ለማቋቋም የተነደፈው ስልት እንደማያዋጣ ነው። ይልቁንስ ሁነኛው መንገድ ወደር የለሹን አብዮተኛ መንግሥቱን ማዕከል በማድረግ ሐቀኛና የተፈተኑ አብዮታውያንን ማሰባሰቡ ነው ተባለ። በዚህም መሠረት፣ የሠርቶ አደሩ ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) በታኅሣሥ 1972 ተቋቋመ። ከመንግሥት ደጎስ ያለ የገንዘብ ድጋፍ የተቸረው ይህ ኮሚሽን ድርጅታዊ መዋቅሩ ከሞላ ጎደል ኋላ የተቋቋመው ፓርቲ አስኳል ሆነ። መንግሥቱ ራሱ በሊቀ መንበርነት የሚመራው ይህ ኮሚሽን፣ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ የክፍላተ ሀገር ኮሚቴ እና በየቀበሌው ማኅበራትና መሥሪያ ቤቶች የተዋቀሩ መሠረታዊ ድርጅቶች ነበሩት።

ከሁለት ዓመት ድርጅታዊ ሥራ በኋላም፣ ኢሠፓአኮ ኢሠፓን (የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ፓርቲን) ወለደ። በመስከረም 1977 ደርግ ሥልጣን የያዘበትን አሥረኛ ዓመት በታላቅ ፈንጠዚያ ሲያከብር፣ እንዲያ የተደከመበት ፓርቲም በታላቅ ሥነ ሥርዓት ታወጀ። ድግሱን ያበላሸው በወቅቱ መላ ሀገሪቱን ቀስፎ የያዘውና እስከዚያን ጊዜ ድረስ ወደር የሌለው ድርቅና ረሀብ ነው። የታሪክ ምጸት ሆነና፣ አፄያዊውን ሥርዓት የ1965ቱን ረሀብ በመሸፋፈኑ ወንጅሎ ከሥልጣን ያስወገደው መንግሥት የድሉን ፍፃሜ ያከበረው በተራቡ ኢትዮጵያውያን ስቃይና ዋይታ ታጅቦ ሆነ። ከ1965ቱ ረሀብ በኋላ እንዲያ ያለ እልቂት እንዳይደገም ታስቦ የተቋቋመው የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ስለአንዣበበው አደጋ ማስጠንቀቂያ ከጀመረ ወራቶች ተቆጥረዋል። ነገር ግን ደርግ የደከመበት ድግሱ እንዲበላሽበት ስላልፈለገ ማስጠንቀቂያዎቹን ጆሮ ዳባ ልበስ አላቸው። ስለሆነም፣ በዓሉ እያሌ ዓለም አቀፍ ደጋፊዎቹ በተገኙበት በትልቅ ፈንጠዚያ ተከበረ። ለይስሙላ በተደረገው ምርጫም፣ መንግሥቱ ቁልፍ የሆነውን የፓርቲ ዋና ጸሐፊነት ከመያዙም በላይ፣ ሁለት መቶ አባላት ያሉት ማዕከላዊ ኮሚቴና ዐሥራ ስምንት አባላት ያሉት የፖሊት ቢሮ ሊቀ መንበር ሆነ። የፖሊት ቢሮው አባላት ለመንግሥቱ ታማኝነታቸውን ያረጋገጡ የደርግ አባላት፣ ቴክኖክራቶችና የማርክሲዝም ሌኒኒዝም አቀንቃኞች ነበሩ። ከእንግዲህ

ወዲያ መሪው መፈክር አንድና አንድ ብቻ ሆነ፦ «ከጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አብዮታዊ አመራር ጋር ወደፊት!»

አምባገነናዊ ሥልጣንን ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት የቀሩት ሁለት ነገሮች ብቻ ነበሩ፤ አዲሱን ሕገ መንግሥት መደንገግና ሪፐብሊኩን ማወጅ። ሕገ መንግሥቱን የማርቀቁ ተግባር ቀደም ሲል በተቋቋመው በብሔረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት ሥር ለተሰባሰቡት ኤክስፐርቶች ተሰጠ። የነሱ ረቂቅ መንግሥቱ ራሱ በሊቀ መንበርነት ለሚመራው 347 አባላት ላሉበት የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ቢቀርብም፣ ረቂቁን የመጨረሻ መልኩን እንዲይዝ ያደረጉት መንግሥቱና የቅርብ አማካሪዎቹ ናቸው። ከዚያም ረቂቁን በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ሕዝብ እንዲወያይበትና ማሻሻያ ሐሳቦቹን እንዲያቀርብ ከተጋበዘ በኋላ ጥር 24 ቀን 1979 በሪፈረንደም ፀደቀ።

ሕገ መንግሥቱ በሚደነግገው መሠረትም የመንግሥት ከፍተኛው አካል ነው ለተባለው ብሔራዊ ሸንጎ አባልነት ብሔራዊ ምርጫ ተደረገ። ብዙም ፉክክር ባልተደረገበት በዚህ ምርጫ በፓርቲው የተደገፉ እጩዎች አሸናፊነትን አገኙ። የአሸናፊዎቹ የምርጫ ምልክት አይበገሬው ዝሆን የሆነው ያለምክንያት አልነበረም! እንደገና ታሪካዊው መስከረም ሲመጣ፣ ብሔራዊ ሸንጎው አዲሲቷን የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕዲሪ) አወጀ። ከልደት እስከ ሞቱ በድራማ የታጀበው ደርግም ሥልጣን በአደራ ከተረከበው ደርግ ወደ ሕዝባዊ መንግሥት መሸጋገሩን በባንዲራ ርክክብ ቲያትር ይፋ አደረገ። የድራማው ዳር ግን የመንግሥቱ የኢሕዲሪ ፕሬዚዳንት ሆኖ «መመረጥ» ነው። እንዲህ እንዲህ እያለ፣ አብዮት ሲፈነዳ ማንም የማያውቀው የነበረው ሻለቃ ኢትዮጵያ በታሪኳ ካየቻቸው ሁሉ ፍፁም የሠመረለት አምባገነን ለመሆን በቃ።

## ፍፃሜ

የኢሕዲሪ ምስረታን ያጀበው ሸብርቅና ሽርጉድ የደርግ ሥርዓት የተጠናወተውን መሠረታዊ ችግር ደብቆት ነበር። አራት ዓመትም ሳያስቆጥር፣ እንዲያ በረቀቀ ጥበብና በአያሌ ደምና ዕንባ የተገነባው ሥርዓት እንደ አሸዋ ክምር ተናደ። ደርግ ውስጥ የነበሩትን ባላንጣዎቹንና የከተሜውን ግራ ክንፍ ኃይል የሸወደው አምባገነን፣ የገጠር ሽምቅ ተዋጊዎቹን ምሕረት-የለሽ የጥይት ውርጅብኝ መቋቋም አቅቶት ወደቀ። ደርግ በሰሜን ኢትዮጵያ እየተስፋፋ የመጣውን ብሔርተኛ አመፅ ለማግታት ከዐሥር ዓመት በላይ ተከታታይ ዘመቻዎች አድርጎ ነበር። በዚህ ከቶም ሳይበገሩ፣ አማፅያኑ በድል ጎዳና ግሥጋሤያቸውን ቀጠሉ። መንግሥቱም ራሱን ለማዳን ለመሸሽ ተገደደ። የሻዕቢያና የኢሕአዴግ ጦርም በግንቦት ወር 1983 በየፊናው አሥመራንና አዲስ አበባን ለመቆጣጠር በቃ። በዚያውም የአካባቢው የኃይል ሚዛን ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ቅኝቱም ወሳኝ በሆነ መልኩ ተቀየረ። ኅብረ-ብሔራዊውን ተቃዋሚ ኃይል ቀደም ሲል ያስወገደው ደርግ፣ አሐዳዊ የሆነውን የፖለቲካ ባሕል ሳንጄም ለሁሌም ለመቀየር ቆርጦ በተነሣ የብሔርተኛ ኃይል ከታሪክ መድረክ ተባረረ።



## ብሔርተኛ አመፅ

የ1966 አብዮት በተቀጣጠለበት የመጀመርያ ወራት፣ ባንዳንድ የደርግ አባላት አካባቢ በአስከፊነቱ የተስማሙበት አፄያዊ ሥርዓት እንዴ ከተወገደ በኋላ፣ የኤርትራ አማፅያን የጦር መሣሪያቸውን ያስቀምጣሉ የሚል የተስፋ ጭላንጭል ነበር። በትውልድ ኤርትራዊ የሆነውና የደርጉ ሊቀ መንበር የነበረው ጄኔራል አማን ጠቅላይ ግዛቱን ከጎበኘ በኋላም፣ አስተዳደራዊ መሻሻል፣ ኤኮኖሚያዊ እድገትና የፖለቲካ እርቅ ያመጣል ብሎ ያመነበትን ሁለገብ ዕቅድ ለደርግ አቅርቦ ነበር። በመፍረሱ ምክንያት መጀመርያ ለአመፁ መነሻ የሆነውን የፌዴራል አደረጃጀትንም የመመለስ ሐሳብ መብላላት ጀምሮ ነበር። ይሁን እንጂ በዚያች ጣጠኛ የኅዳር ምሽት የጄኔራሉ ሕይወት ሲቀጠፍ፣ ለችግሩ ሰላማዊ መፍትሔ ለማስገኘት የነበረው ጥረትም ባጭር ተቀጨ።

ያም ሆኖ የኤርትራ ግንባሮች የጄኔራሉን እንቅስቃሴ በበጎ ዐይን የተመለከቱት አልነበረም። እንዲያውም የመጨረሻ ግባቸው ለሆነው ነፃነት እንደ እንቅፋት ነበር ያዩት። የጄኔራል አማን ሞትን ተከትሎም በደርግ ውስጥ የነበሩት በኮሎኔል መንግሥቱ የሚመሩት አክራሪ ኃይሎች የበላይነትን ስለተቀዳጁ ጦርነቱ እየተፋፋመ መጣ። ግንባሮቹ አሥመራን ዒላማ ያደረገ ጥቃት ከፈቱ። ደርግ በበኩሉ ባንድ ወገን ፀረ-ኤርትራውያን ቅስቀሳ እያካሄደ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በጥር 1967 የግንባሮቹ ደጋፊዎችና ሠርጎ ገቦች ናቸው ባላቸው ሰዎች ላይ አሥመራ ውስጥ ሰፊ የግድያ ዘመቻ አካሄደ። በዚህም የተነሳ፣ ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ኤርትራውያን የመንግሥት ሹማምንትና የጦር መኰንኖች ግንባሮቹን በተለይ ሻዕቢያን ተቀላቀሉ። ስለሆነም የሻዕቢያ የሰው ኃይል በአሥር እጅ እንዳደገ ይነገራል።

ከዚያ በኋላ፣ ሁለቱም ወገኖች በአቋማቸው ፀንተው በጦርነቱ ገፉበት። ነገር ትንሽ ጋብ ያለ የመሰለው፣ ደርግ በ1968 መጨረሻ ላይ ለኤርትራ ክልላዊ የውስጥ አስተዳደር የሚሰጥ ባለ ዘጠኝ ነጥብ ፖሊሲ ይፋ ባደረገበት ወቅት ነው። ይህንን ተከትሎም፣ የደርጉ የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበረው የአየር ኃይሉ ሻለቃ ሲሳይ ሀብቴ ከግንባሮቹ ጋር ድርድር ጀምሮ ነበር። ይሁንና ሻለቃው በሐምሌ ወር ላይ በመንግሥት ላይ አሲረሃል ተብሎ ሲረሸን የሰላም ተስፋውም አብሮ ተዳፈነ።

ለነገሩ ግንባሮቹ ክልላዊ የአስተዳደር ነፃነትን እንደ አማራጭ ማየት ካቆሙ ሰንበት ብሏል። ምንም እንኳን የኤርትራ አርነት ንቅናቄ መጀመርያ ሲንቀሳቀስ ዓላማው የፈረሰውን ፌዴሬሽን ለማስመለስ የነበረ ቢሆንም፤ የጦርነቱ መባባስ ነፃነትን ብቸኛው አጀንዳ አድርጎታል። የኤርትራ ጉዳይም የሕግና ሥርዓት መጣስ መሆኑ ቀርቶ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ሆኗል። ኢትዮጵያም ፌዴሬሽኑን በማፍረሷ ከመወንጀል አልፋ እንዲያውም ሲሆን ሲሆን በ1933፣ የፋሽስት ኢጣሊያ ጦር ተሸንፎ ካካባቢው ሲባረር፣ ግፋ ቢል ግን በ1943 የተባበሩት መንግሥታት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል ከመወሰኑ ይልቅ ማክተም የነበረበት የቅኝ አገዛዝ አልጋ ወራሽ ሆኖ መታየት ጀምራለች። የአካባቢው ታሪክም በግንባሮቹ መሪዎችና አቀንቃኞች ተከልሶ ኢትዮጵያና ኤርትራ አንድም የሚያስተሳስራቸው ነገር የሌላቸው ሁለት የተለያዩ አገሮች ሆነው ቀረቡ። በዚህ አዲስ የታሪክ አቀራረብ፣ ሁለቱም አገሮች በ19ኛው

መቶ ዓመት መጨረሻ ዓመታት ቅኝ ገዥዎች አፍሪቃን ሲቀራመቱ የተፈጠሩ ሆነው ተሳሉ:: በ1930ዎቹ ዓመታት፣ እልፍ አእላፍ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ ጋር ለመዋሐድ ያደረጉት ትግል ተድበሰበሶ ቀረ:: ፌዴሬሽኑን በማፍረስ ረገድ የኤርትራ የአንድነት ኃይሎች የተጫወቱት ወሳኝ ሚና ተዘንግቶ፣ ነገሩ ሁሉ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ተላከከ:: የሚገርመው ነገር አብዛኛው የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ክፍል፣ ከ«ጉልበተኛው» ይልቅ «ተጨቋኙን» ማመን በመምረጥ፣ ይህን የፈጠራ ታሪክ አሜን ብሎ ተቀበለው::

ይህም ሆኖ፣ የነፃነት ጎዳና አጭርና ቀላል አልነበረም:: ግንባሮቹ ለኢትዮጵያ መንግሥት ባላቸው ጥላቻ አንድ ዓይነት አቋም ይኑራቸው እንጂ፣ እርስ በርሳቸው አጥፊና ጠፊ ነበሩ:: በተለይም በ1960ዎቹ ዓመታት አንጋፋው ጀብሐና ከዚያ አፈንግጦ የተመሠረተው ሻዕቢያ እያንዳንዱ የበላይነቱን ለማረጋገጥ በነበረው ፍላጎት ብዙ ደም ያፋሰሰና አያሌ ሕይወት የፈጀ የእርስ በርስ ጦርነት አካሄዱ:: ይህ ሁኔታ ትንሽ ጋብ ያለው፣ የጄኔራል አማን አንዶምን የሰላም ጥሪ ለማስፈፀም እንዲረዱ በተጋበዙት ያገር ሽማግሌዎች አማካይነት ግንባሮቹ ልዩነታቸውን እንዲያስወግዱ የሕዝብ ግፊት ሲፈጠር ነው:: ነገር ግን ሁለቱ ግንባሮች፣ የተፈለገውን ኅብረት በተመለከተ የተለያየና የማይጣጣም ስልት ነበራቸው:: ጀብሐ ሁለቱ ግንባሮች በድርጅትም በአመራርም እንዲዋሐዱ ሲሻ፣ የሻዕቢያ ምርጫ ደግሞ ሁለቱ ግንባሮች ነፃነታቸውን ጠብቀው ትግሉን የሚያስተባብር የጋራ ግንባር እንዲፈጥሩ ነበር::

ሁለቱን ግንባሮች ለማቀራረብ የተደረገው ጥረት ይባስ ብሎ ሻዕቢያን ከሁለት ሰነጠቀው:: የግንባሩ የውጭ ግንኙነት ኃላፊ የነበረው ኦስማን ሳለህ ሳቤ ተገንጥሎ በመውጣት፣ የኤርትራ አርነት ግንባር/ሕዝባዊ አርነት ኃይሎች የተባለ ድርጅት አቋቋመ:: ይህን እርምጃ የወሰደው ሳያማክር ከጀብሐ አመራር ጋር በነሐሴ 1967 ስምምነት በማድረጉ በሻዕቢያ የጦር አዛዦች ከተወገዘ በኋላ ነው:: ምንም እንኳን ሁለቱንም ግንባሮች የሚደግፉት የዐረብ መንግሥታት በተለያየ ጊዜ የይስሙላ ስምምነት እንዲያደርጉ ቢጫኗቸውም፣ ግንኙነታቸው በመሠረቱ በጥርጣሬና ቶክከር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ዘላቂነት ሊያገኝ አልቻለም:: ከምሥራቁ ድል በኋላ ደርግ የከፈተባቸው ግዙፍ ዘመቻ እንኳን ልዩነታቸውን አስወግደው የጋራ ግንባር እንዲፈጥሩ አላደረጋቸውም:: ነገሩ እልባት ያገኘው በ1973 መጨረሻ ላይ ሻዕቢያ ጉልበቱን አፈርጥሞ ጀብሐን ሙሉ በሙሉ በመደምሰስ ከትግል ሜዳ ሲያስወጣው ነው::

ሻዕቢያ ገና የበላይነቱን አጣጥሞ ሳይጨርስ፣ ደርግ ከዚህ በፊት ካደረጋቸው የላቀውን ዘመቻ ከፈተበት:: ከዚያ በፊት መጀመርያ በግንቦት ወር 1968፣ ደርግ ሽማቂዎቹን በእርሶ አደር ሠራዊት ማዕበል አጥለቅልቆ ለማጥፋት በማሰብ፣ ራዛ ዘመቻ የተባለ ጥቃት ሰንዝሮ ነበር:: ሆኖም ዘመቻው ተዝረክርኮ ግቡን ሊመታ ቀርቶ ወደዚያ ሊቃረብም አልቻለም:: የመላ ሰሜን ኢትዮጵያን አርሶ አደር ለማዝመት የታቀደው ጥቃት፣ በመጨረሻ ሊያንቀሳቅስ የቻለው 10000 የሚሆኑ የወሎ ገበሬዎችን ብቻ ነው:: እነሱም ቢሆኑ የሕወሓትና የኢሕአፓ የታጠቀ ሠራዊት የነበረው ኢሕአሠ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት) በሰነዘሩባቸው ወታደራዊና ፕሮፓጋንዳዊ ጥቃት ተዋክበው፣ እንኳን ኤርትራ ሊዘልቁ የትግራይንም ግዛት ማለፍ ተስኗቸው ተበታተኑ::



ደርግ በኤርትራ ሽምቅ ተዋጊዎች ላይ የከፈተው ሁለተኛው ዘመቻ ደግሞ በ1970 ክረምት ላይ ሲሆን፣ ዓላማውም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ በምሥራቅ ጦር የተገኘውን ድል በሰሜንም ለመድገም ነበር:: በርግጥም መጀመርያ ላይ፣ በስምንት ግብረ ኃይሎች ተዋቅሮ የዘመተው የደርግ ጦር፣ ጀብሐና ሻዕቢያ ቀደም ሲል የተቆጣጠሯቸውን የኤርትራ ዋና ዋና ከተሞች ለቀው እንዲሸሹ አስገደዳቸው:: ሻዕቢያም አስተማማኝ ደጀኑ ወደሆነው የተፈጥሮ ምሽጉ ወደናቅፋ አፈገፈገ:: ከአንድ አራት ዓመታት በኋላ፣ ደርግ ሦስተኛውንና ምናልባትም ከሁሉም ዘመቻዎች በላይ ትልቅ ተስፋ የጣለበትን የ«ቀይ ኮከብ» ዘመቻ ነጋሪት ጎስሞ፣ እምቢልታ መለከት ነፍቶ ከፈተ:: በጦርነት የተጎዳውን ክፍለ ሀገር መልሶ ለማቋቋምና ተገንጣይ ኃይሎችን እንዳያንሰራሩ አርጎ ለመምታት የሚል ጣምራ ዓላማ ይዞ የተነሳው ይህ ዘመቻ ያነጣጠረው ሻዕቢያ በመሸገበት ናቅፋ ተራራ ላይ ነበር:: በርግጥም የደርግ ጦር ያን የተፈጥሮ ምሽግ ለመቆጣጠር ትንሽ ሲቀረው፣ እስካሁንም በውል ባልታወቀ ምክንያት ወደ ኋላ በማፈግፈጉ፣ ሻዕቢያ አዲስ ነፍስ እንዲዘራ አደረገው:: የዚህ ዘመቻ መክሸፍም የጦርነቱ ወሳኝ ነቁጥ ሆነ:: ከዚያ በኋላ፣ ስሉስ ዞሮ ሻዕቢያ አሳዳጅ ደርግ ተሳዳጅ ለመሆን በቁ::

በዚህ ሁሉ መኻል፣ ከመረብ ወንዝ በስተደቡብ ደርግን በብርቱ የሚፈታተን ሌላ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄ እንደ ዋዛ ተጀምሮ በማደግ ላይ ነበር:: ትግሉን የሚመራው የሕዝባዊ ወያኔ አርነት ግንባር በምዕራብ ትግራይ፣ ሽሬ አውራጃ፣ ደደቢት በምትባል በረሃማ ቀበሌ በየካቲት 1967 በጥቂት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና የአካባቢው መሪዎች ተመሠረተ:: የንቅናቄው ታሪካዊ ምንጭ፣ ከአፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ የትግራይ ግዛት ባጠቃላይ፣ መኳንንቷ በተለይ፣ የፖለቲካ ማዕከላዊነት በማጣታቸው ምክንያት የተሰማቸው ቁጭት ሲሆን፣ በሃያኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ላይ በክፍለ ሀገሩ በተከሰተው ተደጋጋሚ ድርቅ ምክንያት የደረሰው የኤኮኖሚ ችግርም የበደል ስሜቱን አባብሶታል::

እንዲህ ዓይነቱ ቁጭትና ብሶትም ነው በ1935 ዓ.ም. ቀደም ሲል በምዕራፍ 5 ላይ የተዘገበውንና ምሥራቃዊ ትግራይን ያጥለቀለቀውን የወያኔ አመፅ የቀሰቀሰው:: ከሦስት ዐሥርት ዓመታት በኋላ ሕወሓትን የመሠረቱት ተማሪዎች «ወያኔ» የሚለውን ቀስቃሽ ገላጭ ስማቸው ውስጥ የጨመሩት ያለምክንያት አልነበረም:: ነገር ግን፣ ዳግማዊው ወያኔ ከቀዳማዊው ወያኔ በድርጅታዊ ጥንካሬና በርዕዮተ ዓለም ትጥቅም የላቀ ነበር:: የመጀመሪያው ወያኔ ሃይማኖታዊ ርዕዮት አንግቦ የተነሳ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በወረሰውና «የራስን ዕድል በራስ የመወሰን፣ እስከ መገንጠል» በሚለው ሌኒናዊ መርሕ የሚመራ ነበር:: እንዴ ይህን መርሕ ከጨበጡ በኋላም፣ ከማንኛቸውም መሰል የግራ ድርጅት ይበልጥ እስካሁንም ገፍተውበታል:: ይህም ለመርሁ የተለየ ታማኒነት ኖሯቸው ሳይሆን፣ በተለይ በዳር አገሮች ፀረ-መንግሥት ተቃውሞን ለመቀስቀስ ፍቱን መሣሪያ ሆኖ ስላገኙት ይመስላል::

ልክ በኤርትራ እንደታየው ሁሉ፣ በመጀመርያዎቹ ዓመታት ሕወሓት ዋና ሥራው አድርጎ የያዘው በክፍለ ሀገሩ ውስጥ የበላይነቱን ማስፈን ነው::



6.8 የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ታጋዮች

ለዚህም ከሦስት ተቃናቃኝ ድርጅቶች ጋር መፋለም ነበረበት። ከነዚህ ሁሉ ቀላል ሆኖ ያገኘው ከሱ ቀድሞ የተደራጀውንና ከጀብሐ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበረውን የትግራይ አርነት ግንባርን ማስወገዱ ነው። በምዕራብ ትግራይ ተደላድሎ የነበረውን የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረትን (በእንግሊዝኛ ምሕፃረ-ቃሉ «ኢዲዩ»ን) ለመፈንቀል ግን እንደዚያ ቀላል ሆኖ አላገኘውም። ብዙ ደም ካፋሰሰ የሁለት ዓመት ጦርነት በኋላ ነው ሕወሓት ኢዲዩን ከምዕራብ ትግራይ ጨርሶ ለማስወጣት የቻለው።

ከዚያ በኋላ የቀጠለው ፍልሚያ በሰሜን ምሥራቅ ትግራይ አሲምባ በሚባለው ተራራማ ሥፍራ ከመሸገው የኢሕአፓ ሠራዊት ጋር ነበር። ሕወሓትም ኢሕአፓም ግራ-ዘመም ከሆነው ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አብራክ የወጡ ድርጅቶች ይሁኑ እንጂ፣ የትግሉን አቅጣጫና ይዘት በተመለከተ እጅግ የተራራቀ አመለካከት ነበራቸው። ኢሕአፓ እንደሱ ባለ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅት የሚመራውን የመደብ ትግል ቀዳሚነት በአጽንኦት ሲያስቀምጥ፣ እንደ ሕወሓት አመለካከት ግን፣ ትግሉ ሊሰምር የሚችለው የተለያዩ ጭቁን ብሔርና ብሔረሰቦች በራሳቸው ድርጅት አማካይነት ትግላቸውን ጀምረው ከዚያ በኋላ የኅብረት ግንባር ሲፈጥሩ ነው። በተጨማሪም፣ ሕወሓት ሙሉ እምነቱን በገጠር ትጥቅ ትግል ላይ ሲጥል፣ ኢሕአፓ ግን፣ ምናልባትም በከተሞች ውስጥ ማግኘት ከቻለው ተቀባይነትም ይመስላል፣ ለከተማው የትጥቅ ትግል ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ነበር። በመሠረቱ፣ አሲምባ የከተማው የትጥቅ ትግል ሳይሰምር ሲቀር ከመንግሥት የጥቃት እርምጃ ላመለጡት ታጋዮቹ መጠለያ ከመሆን አልፎ ይህ ነው ለሚባል የገጠር ትጥቅ ትግል መነሻ ሆኖ ነበር ለማለትም ያስቸግራል። ስለሆነም ኢሕአፓ በገጠር ትጥቅ ትግል ከነበረው እናሳ ልምድ



ባሻገር፣ ላካባቢው የነበረው እንግዳ-ዊ ባዳነት በሕወሓት ለመሸነፍ ዳርጎት ኃዙን ጠቅሎ ወደ ጎንደርና ወሎ እንዲያፈገፍግ ተገደደ።

መጀመርያ ላይ ደርግ ሕወሓትን ከቁም ነገር አልቆጠረውም ነበር። ለድርጅቱ መፈጠር ምክንያት የሆኑትን የትግራይ ነባራዊ ሁኔታዎች ባለማጤን፣ ድርጅቱን እንደ ሻዕቢያ ተቀፅላ አድርጎ ወሰደው። ሙሉ ኃይሉን ያዘመተበት ሻዕቢያ ከተመታ ሕወሓትም አብሮ ይከስማል ብሎ ገመተ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሕወሓትና ሻዕቢያ ከሚያቀራርባቸው ሁኔታ የሚያራርቃቸው ይበዛ ነበር። እንዲያውም መጀመርያ ላይ፣ ሻዕቢያ ከሕወሓት ይልቅ የኃይል ሚዛን አጋድሎበት ከትግራይ እስከወጣ ድረስ ወደ ኢሕአፓ ያጋድል ነበር። ሕወሓት በመላ ትግራይ የበላይነቱን ካሰፈነ በኋላም ቢሆን፣ የሁለቱ ድርጅቶች ትስስር የፍቅር ሳይሆን የጥቅም ነበር። ለዚህም አያሌ ምክንያቶች ነበሩ። በአንደኛ ደረጃ፣ በተለይም የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ በተወው አሻራ ምክንያት፣ በሁለቱ የመረብ ወንዝ ተዋሳኝ ወንድማማች ሕዝቦች መካከል የመናናቅና የመቃቃር ባሕል ነበር። ከዚያም በላይ ሁለቱ የአርነት ንቅናቄዎች የትግል ስልቱን በተመለከተ መሠረታዊ ልዩነቶች ነበሯቸው። ሕወሓት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መርሕ በኤርትራ ውስጥ ለሚገኙት የተለያዩ ብሔረሰቦችም መሥራት አለበት ሲል፣ ሻዕቢያ ግን የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ በኤርትራ ትግል ውስጥ ከቶም እንዲነሳ አይሻም ነበር። የሶቪየት ኅብረትንም በተመለከተ፣ ሕወሓት ሶቪየቶች ለደርግ በሚሰጡት ያልተቆጠበ ድጋፍ የተነሳ የማያወላዳ ፀረ-ሶቪየት አቋም ሲወስድ፣ ሻዕቢያ ግን ለስለስ ያለ አቋም ነበረው። ከዚያም አልፎ ሁለቱ ድርጅቶች በጦር ታክቲካቸውም የተለያየ አመለካከት ነበራቸው። የሕወሓት የጦር ስልት በደፈጣ ውጊያ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ሻዕቢያንም ተቻኩሎ ወደ መደበኛ ጦርነት በመግባቱ ይተቸው ነበር። ሁለቱ ድርጅቶች እነዚህን ሁሉ ያስተሳሰሩብና የቅኝት ልዩነቶች አቻችለው የጋራ ጠላታቸውን ውድቀት ለማፋጠን የተረባረቡት በ1970ዎቹ መጨረሻና በ1980ዎቹ መጀመርያ ላይ ነው።

በመጨረሻዎቹ ዓመታት ደርግ ላይ ካመፁት ብሔርተኛ ድርጅቶች መካከል ሌላ ሊጠቀስ የሚገባው የኦሮሞ አርነት ግንባር (ኦነግ) ነው። የኦሮሞ ሕዝብ የብሔራዊ ማንነት ጥያቄ መጀመርያ በተደራጀ መንገድ የተቀሰቀሰው የቱለማና ሜጫ ራስ-አገዝ ማኅበር በጥር 1955 ሲመሠረት ነው ማለት ይቻላል። ይህም ሆኖ፣ ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መረዳት እንደሚቻለው፣ የማኅበሩ መነሻ ዓላማ ለብሔራዊ አርነት መታገል ሳይሆን፣ የኦሮሞ ግዛቶች በትምህርት፣ መንገድና ጤና ረገድ የነበረባቸውን ችግር ለመቅረፍ ነበር። በኦሮሞዎች ስም ይቋቋም እንጂ አባላቱን የመለመለውም ከኦሮሞ ብሔር ብቻ አልነበረም። እንዲያውም በአመራሩ ውስጥ አንዳንድ ታዋቂ የሆኑ የደቡብ ኢትዮጵያ የኅብረተሰብ መሪዎችም ነበሩበት። ይህም ሆኖ፣ ከአሓዳዊ አስተዳደሩ ዝንፍ ለማለትም የማይፈልገው መንግሥት ማኅበሩን በአደገኛነት የሚፈረጅ ሆኖ አገኘው። በተለይም የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ የነበረው ብርጋዴር ጀኔራል ታደሰ ብሩ የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ሆኖ መመረጥ ሥርዓቱን አስበረገገው።

በዘውዳዊው አገዛዝና በማኅበሩ መካከል የሰፈነው ውጥረት የተመላበት ፍጥጫ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው በጥቅምት 1959 ዓ.ም. አንዳንድ የማኅበሩ አባላት በዘውድ በዓል ወቅት በንጉሡ ነገሥቱ ላይ የግድያ ሙከራ ለማድረግ ሲያሴሩ ተደረሰባቸው ተብለው ሲወነጀሉ ነው። ከዚያም በመቀጠል ሲኒማ



6.8 የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ታጋዮች

ለዚህም ከሦስት ተቃናቃኝ ድርጅቶች ጋር መፋለም ነበረበት። ከነዚህ ሁሉ ቀላል ሆኖ ያገኘው ከሱ ቀድሞ የተደራጀውንና ከጀብሐ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበረውን የትግራይ አርነት ግንባርን ማስወገዱ ነው። በምዕራብ ትግራይ ተደላድሎ የነበረውን የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረትን (በእንግሊዝኛ ምሕፃረ-ቃሉ «ኢዲዩ»ን) ለመፈንቀል ግን እንደዚያ ቀላል ሆኖ አላገኘውም። ብዙ ደም ካፋሰስ የሁለት ዓመት ጦርነት በኋላ ነው ሕወሓት ኢዲዩን ከምዕራብ ትግራይ ጨርሶ ለማስወጣት የቻለው።

ከዚያ በኋላ የቀጠለው ፍልሚያ በሰሜን ምሥራቅ ትግራይ አሲምባ በሚባለው ተራራማ ሥፍራ ከመሸገው የኢሕአፓ ሠራዊት ጋር ነበር። ሕወሓትም ኢሕአፓም ግራ-ዘመም ከሆነው ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አብራክ የወጡ ድርጅቶች ይሁኑ እንጂ፣ የትግሉን አቅጣጫና ይዘት በተመለከተ እጅግ የተራራቀ አመለካከት ነበራቸው። ኢሕአፓ እንደሱ ባለ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅት የሚመራውን የመደብ ትግል ቀዳሚነት በአጽንኦት ሲያስቀምጥ፣ እንደ ሕወሓት አመለካከት ግን፣ ትግሉ ሊሰምር የሚችለው የተለያዩ ጭቁን ብሔርና ብሔረሰቦች በራሳቸው ድርጅት አማካይነት ትግላቸውን ጀምረው ከዚያ በኋላ የኅብረት ግንባር ሲፈጥሩ ነው። በተጨማሪም፣ ሕወሓት ሙሉ እምነቱን በገጠር ትጥቅ ትግል ላይ ሲጥል፣ ኢሕአፓ ግን፣ ምናልባትም በከተሞች ውስጥ ማግኘት ከቻለው ተቀባይነትም ይመስላል፣ ለከተማው የትጥቅ ትግል ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ነበር። በመሠረቱ፣ አሲምባ የከተማው የትጥቅ ትግል ሳይሰምር ሲቀር ከመንግሥት የጥቃት እርምጃ ላመለጡት ታጋዮቹ መጠለያ ከመሆን አልፎ ይህ ነው ለሚባል የገጠር ትጥቅ ትግል መነሻ ሆኖ ነበር ለማለትም ያስቸግራል። ስለሆነም ኢሕአፓ በገጠር ትጥቅ ትግል ከነበረው እናሳ ልምድ



ባሻገር፣ ላካባቢው የነበረው እንግዳዊ ባዳነት በሕወሓት ለመሸነፍ ዳርጎት ጓዙን ጠቅሎ ወደ ጎንደርና ወሎ እንዲያፈገፍግ ተገደደ።

መጀመርያ ላይ ደርግ ሕወሓትን ከቁም ነገር አልቆጠረውም ነበር። ለድርጅቱ መፈጠር ምክንያት የሆኑትን የትግራይ ነባራዊ ሁኔታዎች ባለማጤን፣ ድርጅቱን እንደ ሻዕቢያ ተቀፅላ አድርጎ ወሰደው። ሙሉ ኃይሉን ያዘመተበት ሻዕቢያ ከተመታ ሕወሓትም አብሮ ይከስማል ብሎ ገመተ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሕወሓትና ሻዕቢያ ከሚያቀራርባቸው ሁኔታ የሚያራርቃቸው ይበዛ ነበር። እንዲያውም መጀመርያ ላይ፣ ሻዕቢያ ከሕወሓት ይልቅ የኃይል ሚዛን አጋድሎበት ከትግራይ እስከወጣ ድረስ ወደ ኢሕአፓ ያጋድል ነበር። ሕወሓት በመላ ትግራይ የበላይነቱን ካሰፈነ በኋላም ቢሆን፣ የሁለቱ ድርጅቶች ትስስር የፍቅር ሳይሆን የጥቅም ነበር። ለዚህም አያሌ ምክንያቶች ነበሩ። በአንደኛ ደረጃ፣ በተለይም የኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ በተወው አሻራ ምክንያት፣ በሁለቱ የመረብ ወንዝ ተዋሳኝ ወንድማማች ሕዝቦች መካከል የመናናቅና የመቃቃር ባሕል ነበር። ከዚያም በላይ ሁለቱ የአርነት ንቅናቄዎች የትግል ስልቱን በተመለከተ መሠረታዊ ልዩነቶች ነበሯቸው። ሕወሓት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መርሕ በኤርትራ ውስጥ ለሚገኙት የተለያዩ ብሔረሰቦችም መሥራት አለበት ሲል፣ ሻዕቢያ ግን የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ በኤርትራ ትግል ውስጥ ከቶም እንዲነሳ አይሻም ነበር። የሶቪየት ኅብረትንም በተመለከተ፣ ሕወሓት ሶቪየቶች ለደርግ በሚሰጡት ያልተቆጠበ ድጋፍ የተነሳ የማያወላዳ ፀረ-ሶቪየት አቋም ሲወስድ፣ ሻዕቢያ ግን ለስለስ ያለ አቋም ነበረው። ከዚያም አልፎ ሁለቱ ድርጅቶች በጦር ታክቲካቸውም የተለያየ አመለካከት ነበራቸው። የሕወሓት የጦር ስልት በደፈጣ ውጊያ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ሻዕቢያንም ተቻኩሎ ወደ መደበኛ ጦርነት በመግባቱ ይተቸው ነበር። ሁለቱ ድርጅቶች እነዚህን ሁሉ ያስተሳሰብና የቅኝት ልዩነቶች አቻችለው የጋራ ጠላታቸውን ውድቀት ለማፋጠን የተረባረቡት በ1970ዎቹ መጨረሻና በ1980ዎቹ መጀመርያ ላይ ነው።

በመጨረሻዎቹ ዓመታት ደርግ ላይ ካመፁት ብሔርተኛ ድርጅቶች መካከል ሌላ ሊጠቀስ የሚገባው የኦሮሞ አርነት ግንባር (ኦነግ) ነው። የኦሮሞ ሕዝብ የብሔራዊ ማንነት ጥያቄ መጀመርያ በተደራጀ መንገድ የተቀሰቀሰው የቱለማና ሜጫ ራስ-አገዝ ማኅበር በጥር 1955 ሲመሠረት ነው ማለት ይቻላል። ይህም ሆኖ፣ ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መረዳት እንደሚቻለው፣ የማኅበሩ መነሻ ዓላማ ለብሔራዊ አርነት መታገል ሳይሆን፣ የኦሮሞ ግዛቶች በትምህርት፣ መገናኛና ጤና ረገድ የነበረባቸውን ችግር ለመቅረፍ ነበር። በኦሮሞዎች ስም ይቋቋም እንጂ አባላቱን የመለመለውም ከኦሮሞ ብሔር ብቻ አልነበረም። እንዲያውም በአመራሩ ውስጥ አንዳንድ ታዋቂ የሆኑ የደቡብ ኢትዮጵያ የኅብረተሰብ መሪዎችም ነበሩበት። ይህም ሆኖ፣ ከአሓዳዊ አስተዳደሩ ዝንፍ ለማለትም የማይፈልገው መንግሥት ማኅበሩን በአደገኛነት የሚፈረጅ ሆኖ አገኘው። በተለይም የፖሊስ ሠራዊት ዋና አዛዥ የነበረው ብርጋዴር ጄኔራል ታደሰ ብሩ የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ሆኖ መመረጥ ሥርዓቱን አስበረገገው።

በዘውዳዊው አገዛዝና በማኅበሩ መካከል የሰፈነው ውጥረት የተመላበት ፍጥጫ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰው በጥቅምት 1959 ዓ.ም. አንዳንድ የማኅበሩ አባላት በዘውድ በዓል ወቅት በንጉሠ ነገሥቱ ላይ የግድያ ሙከራ ለማድረግ ሲያሴሩ ተደረሰባቸው ተብለው ሲወነጀሉ ነው። ከዚያም በመቀጠል ሲኒማ

አምፒር በተባለው ሲኒማ ቤት ውስጥ በምብ ሲፈነዳ የማኅበሩ አባላት አሁንም ተጠያቂ ሆኑ። በተለይም ዋና አቀነባባሪ ተብለው የተወነጀሉት ጄኔራል ታደሰና የመቶ አለቃ ማሞ መዘምር የተባለ መኰንን ነበሩ። መንግሥት በዚህ የተነሳ የሜጫና ቱለማ ማኅበርን ሲያፈርስ፣ ከድርጊቱ በኋላ የተሰወረውን ጄኔራል አድኖ ያዘ። ከዚያ በኋላ ፍርድ ቤት ቀርቦ የሞት ፍርድ ቢፈረድበትም፣ ይህ ወደ እድሜ ልክ እስራት ተቀይሯል። አብዮት ሲፈነዳ ጄኔራሉ ከሌሎች የፖለቲካ እስረኞች ጋር በምሕረት ቢለቀቅም፣ ከኀቡዕ የኦሮሞ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠሩ ያልጣመው ደርግ የመሬት አዋጁን ተቃውሟል በሚል ውንጀላ በ1967 አጋማሽ ላይ ረሽነው።

ኦነግ ይፋ ከመውጣቱ ከአንድ አምስት ዓመት በፊት፣ አንድ የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅት ብቅ ብሎ ነበር። የቀድሞ የሜጫና ቱለማ ማኅበር አባል በነበረ ግለሰብ የተቋቋመው ይህ ድርጅት «የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርነት ግንባር» በሚል ስያሜ የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህ ነው የሚባል ቁም ነገር ሳያከናውን ከታሪክ መድረክ ወጣ። የኢትዮጵያ አብዮት በፈነዳበት የመጀመርያ ሁለት ዓመታት የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በአብዛኛው ኅብረ-ብሔራዊ ባሕሪ ስለነበራቸው የጎላ የኦሮሞ ብሔራዊ እንቅስቃሴ አይታይም ነበር። በወቅቱ የነበሩት የኦሮሞ ምሁራንም ከኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች ባንዱ ወይም በሌላው የታቀፉ ነበሩ። ይህም ሆኖ ግን፣ በአንዳንዶቹ ተመልካቾች አካባቢ፣ መኢሶንንና በተለይም ኢጭአትን የአንዳንድ መሪዎቻቸውን ብሔረሰብ በማጤን ከኦሮሞዎች ጋር የማገናኘት ዝንባሌ ነበር። በማያሻማ መንገድ በኦሮሞ ሕዝብ ስም የሚንቀሳቀስ ድርጅት ብቅ ያለው ግን በ1968 ኦነግ ሲቋቋም ነው። ከሻዕቢያ የቴክኒክ ድጋፍ ያገኝ የነበረው ኦነግ በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ (ሐረርጌና ባሌ) እና በምዕራብ ኢትዮጵያ (ወለጋ) የሽምቅ ውጊያ ማካሔድ ቢጀምርም፣ በነበረበት ውስጣዊ ክፍፍልና አብዛኛውን የኦሮሞ ሕዝብ ለመቀስቀስ ባለመቻሉ፣ የደርግን ሥርዓት እምብዛም ሊፈታተነው አልበቃም።

## የኤኮኖሚ ቀውስ

የደርጋዊውን ሥርዓት ውድቀት ያፋጠነው በስተሰሜን የተፋፋመው አመፅ ብቻ አልነበረም። ደርግ በኤኮኖሚው መስክ ያሳየው ድክመትና ይህንኑ ሁኔታ ያባባሰው አመፁ የወለደው የጦርነት ኤኮኖሚም የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል። ስለሆነም ሠፊውን ሕዝብ ከ«ሰው በላው» አፄያዊ ሥርዓት ነፃ አወጣለሁ ያለው መንግሥት አገሪቱን በከፋ ሁኔታ ትቶ ለማለፍ በቃ። ወታደርና ዘመቻ ስለማይለያዩ ይመስላል፣ የደርግ መንግሥት ሕይወት በ«ዘመቻ» የተሞላ ነበር ስለማለት ይቻላል። ከነዚህም ውስጥ ከዐበይቱ ጎራ የሚደመረው፣ ደርግ በውስጥና የውጭ ጠላቶቹ ላይ ጊዜያዊ ድልን ከተጎናፀፈ በኋላ በመስከረም 2፣ 1971 ያወጀው የብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ (ወይም በተለምዶ አጠራሩ «አረንጓዴው ዘመቻ») ነው። ዓላማውም በማዕከላዊ ፕላን ከፍተኛ ምክር ቤት አስተናባሪነት ያገሪቱን ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች በማንቀሳቀስ የሀገሪቱን ኤኮኖሚ ወሳኝ በሆነ መንገድ መቀየር ነበር። የዚህ ሁለገብ እንቅስቃሴ ውጤትም እርሻን በማሳደግና ኢንዱስትሪን በማስፋፋት ፈጣን የኤኮኖሚ እድገት ለማምጣት የተነደፈው የአሥር ዓመት (1977-1986) ጠቋሚ ዕቅድ ነው። የዕቅዱ ዓላማ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርትን (ጂ.ዲ.ፒ.) በ6.5 በመቶ፣ የነፍስ ወከፍ ገቢን በ3.6 በመቶ ለማሳደግ ነበር። ይሁን እንጂ የታለመው ቀረና እንዲያውም የነፍስ ወከፍ ገቢ በ0.8 በመቶ ዝቅ አለ።



የደርግ ኤኮኖሚ ፖሊሲ የመጨረሻው ውድቀት ገሓድ የወጣው ለስምንት ሚሊዮን ሕዝብ መሰቃየትና ለአንድ ሚሊዮን ያህል ሕዝብ ሕይወት መቀጠፍ ምክንያት በሆነው በ1977 ረሀብ ወቅት ነው። የችግሩ ምንጭ የደርግ መላውን የኤኮኖሚ ሕይወት ካልተቆጣጠርኩ የማለት አባዜ ነው። ይህ አዝማሚያ የመንግሥትን አቅም በብርቱ ከመፈተኑም ባሻገር የግል ጥረትን የሚያፍን ነበር። ለታቀደው የኤኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ የሆነው ካፒታል ከአገር ቤትም ሆነ ከውጭ ሊገኝ አልቻለም። ከዚያም በላይ፣ መንግሥት የረሀቡ አደጋ እንዳንዣበበ የመከላከያ እርምጃዎች ከመውሰድ ይልቅ በፓርቲ ምሥረታ ፈንጠዝያ ተውጦ ነበር። የምሥረታው ሽርጉድ ካለቀ በኋላ ነው የመባነን ያህል ደርግ ፊቱን ወደ ረሀቡ ያዞረው። ደግነቱ፣ የዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ባደረገው አስደናቂ ርብርቦሽና አገር ውስጥም በተሰበሰበው እርዳታ አማካይነት የረሀቡ መቅሰፍት ሊገታ ቻለ።

መጀመርያ ያሳየውን ዳተኝነት ለማካካስ ይመስላል፣ ደርግ በድርቁ የተጠቁትን የሰሜንና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ገበሬዎችና ቤተሰቦቻቸውን ለምለም ወደሆኑት የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ቀዬዎች የማስፈር ሰፊ ዘመቻ ጀመረ። የዘመቻው ውጤትም ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ አርሶ አደሮችንና ቤተሰቦቻቸውን ረጅምና ሥቃይ በበዛበት ጉዞ ወደ አዲስ ሠፈራ ጣቢያ ማጓጓዝ ሆነ። ላይ ላዩን ሲያዩት ይህ ፕሮጀክት ምንም አማራጭ የሌለው ይመስላል። ነገር ግን፣ ባንድ ወገን ሰፋሪዎቹ ወደ አዲሱ መንደራቸው ወደው ሳይሆን ተገደው የሚሄዱ በመሆኑ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ደርግ በዚሁ አጋጣሚ የሠፈራውን ፕሮግራም የእርሻ ፖሊሲው እምብርት የሆነውን የጋራ እርሻ ለማስፋፋት መሣሪያ በማድረጉ፣ ፕሮግራሙ ባገር ቤትም ሆነ በውጭ የተጠላ ሆነ።

አገሪቱ ኅብረተሰቡን ካመሰው ከዚህ ግዙፍ የሕዝብ ሠፈራ ፕሮግራም ሳታገግም፣ ደርግ ሌላ አወዛጋቢ የሆነ የማኅበራዊ ለውጥ ዕቅድ ይዞ ብቅ አለ። ይኸውም የመንደር ምሥረታ ፕሮግራም በሚል ስያሜ የሚታወቀውና የገጠር ነዋሪዎችን ባዲስ ሠፈር የሚያደራጀው ዕቅድ ነው። የፕሮግራሙ ዓላማ፣ በይፋ እንደተገለፀው ከሆነ፣ የተበታተኑትን የሰፈር አባወራዎች በማሰባሰብ የመሠረታዊ አገልግሎት (ትምህርት፣ ሕክምና፣ ወዘተ...) አቅርቦትን በተቀላጠፈና በተማከለ መንገድ ለማዳረስ ነው። ይህ የሠፈራ ፕሮግራም ባሌ፣ ሐረርጌና አርሲ ተጀምሮ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሌሎች ክፍላተ ሀገርንም አዳረሰ። ሠፈራው የገጠሬውን ሕዝብ ከለመደው፣ ከሚንከባከበውና እትብቱ ከተቀበረበት አፈናቅሎ የሚወስድ በመሆኑ በእጅጉ የተጠላ ነበር። ስለሆነም በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች የአያሌ አርሶ አደሮች ልብ እንዲሸፍትና ከደርግ ጠላቶች ጋር እንዲያብር በማድረግ የደርግን ውድቀት ለማፋጠን በቃ።

## ግላስኖስትና ፔሬስትሮይካ

ያገር ውስጥ ሁኔታ እንደዚህ ለደርግ እየጨለመበት ሲሄድ፣ የዓለም አቀፉ የፖለቲካ ገፅታም ፈፅሞ ለሱ በማያመች መልክ በፍጥነት እየተቀየረ ነበር። የሶቪየቱ መሪ ሚካኤል ጎርባቾቭ ያራምደው የነበረው የፔሬስትሮይካና

ግላስኖስት ጥምራ ፖሊሲ የሶቪየት ኅብረትን ብቻ ሳይሆን የዓለምን የኃይል ሚዛን እንደማይመለስ አርጎ ለወጠው። የጎርባቾቭ ዓላማ እየተጠላ የመጣውን የኮሙኒስት ሥርዓት ሰብዓዊ ገፅታ ለመስጠት ነበር። የዚህ አደገኛ ሙከራ መጨረሻ ውጤት ግን የሶቪየት ኅብረት ኃያልነት ማክተምና ለምዕራቡ ዓለም መንበርከክ ሆነ። የሶሻሊስት ሥርዓትን ገንብቶ ገና አጣጥሞ ላልጨረሰው የኢትዮጵያ ገዢ መደብ ደግሞ መራራ ጽዋ ነበር።

ግን እያቅማማም ቢሆን፣ ጽዋውን ከመጎንጨት ሌላ አማራጭ አልነበረውም። መጀመርያ ከጥቅምት 29 እስከ ኅዳር 2 1981 በተደረገው የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 9ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ ድርጅቱ የመጨረሻ ግቡ የሶሻሊስት ሥርዓቱን መገንባት እንደሆነ ቢያረጋግጥም፣ የግል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት አንዳንድ እርምጃዎች ለመውሰድ ተገዶ ነበር። ከመንግሥት ጋር በጋርዮሽ የሚሠሩ የግል ኢንቨስተሮችን፣ የአነስተኛ ኢንዱስትሪዎችንና የሆቴል አገልግሎቶችን የካፒታል ጣራ ከፍ አደረገ። ይሁን እንጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ካለው መሠረታዊ ለውጥ ጋር ለመጣጣም እነዚህ እርምጃዎች ከቶም በቂ ሆነው አልተገኙም። ስለሆነም፣ በየካቲት 28፣ 1982 ዓ.ም. የተካሄደው የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ 11ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ የሶሻሊስት ግንባታ መርህን በመሠረዝ፣ የቅይጥ ኢኮኖሚ መርሐ ግብርን አፀደቀ። በፖለቲካው መስክም፣ ኢሠፓን የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችን ሊያቅፍ በሚችልና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ በተሰኘ አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ እንደሚተካ አረጋገጠ። ይሁን እንጂ፣ ይህ የፖሊሲ ለውጥ በቂ ካለመሆኑም ሌላ ጊዜው ያለፈበት ሆኖ ተገኘ። በሰሜን ግንባር እንደሁ ወታደራዊ የኃይል ሚዛኑ ወደ አማፅያኑ ካጋደለ ሰንብቷል።

### የመጨረሻው ሰዓት

በጦርነቱ ግንባር፣ ለደርግ የቁርጡ ቀን በመጋቢት 1980 መጣ። ሻዕቢያ «ናደው» በሚል መጠሪያ የሚታወቀውን የደርግ ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር ደምስሶ አፍአቤት የተባለውን ቁልፍ ወታደራዊ ቦታ ያዘ። ከዚያ ቀደም ሲል የናደው ጦር አዛዥ የነበረው ጀኔራል ታሪኩ ዐይኔ በጦርነቱ አመራር ላይ ከመንግሥቱ ጋር ኃይለ ቃል የተመላለሰበት ልውውጥ ካደረገ በኋላ ተረሽኗል። ይህም የጦሩን ሞራል ክፉኛ ጎድቶት እንደነበር ይነገራል። በአፍአቤት ጦርነት 20000 የሚሆን የደርግ ጦር ከጥቅም ውጭ ከመሆኑም በላይ፣ ቁጥሩ የበዛ መሣሪያ ሻዕቢያ እጅ በመውደቁ፣ በጦርነቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ባጭሩ፣ አፍአቤት ለሻዕቢያ መጀመርያ ወደ ምፅዋ፣ ብሎም ወደ አሥመራ መረማመጃ ሆነ።

ከአንድ ዓመት ግድም በኋላ፣ በየካቲት 1981፣ የመንግሥት ጦር በትግራይ ውስጥ ተመሳሳይ ሽንፈት ደረሰበት። ሕወሓት የአካባቢውን ሕዝብ ተንተርሶና በሻዕቢያ ሜካናይዝድ አጋዥ ጦር ታግዞ፣ በምዕራብ ትግራይ የምትገኘውን ሽሬ እንዳሥላሴን ተቆጣጠረ። 40000 ወታደር ያሠለፈው የሦስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት 604ኛ ኮር ሙሉ በሙሉ ተደመሰሰ። ልክ ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ቀደም ሲል ለኤርትራ እንደተቋቋመው፣



ሦስተኛው አብዮታዊ ሠራዊት የትግራይን አመፅ ለመግታት ተብሎ በልዩ ሁኔታ የተደራጀ ጦር ነበር። የሽሬ ሽንፈትን ተከትሎ፣ ተመሳሳይ ኪሣራ እንዳይደርስበት ይመስላል፣ ደርግ ሠራዊቱን በሙሉ ከትግራይ ክፍለ ሀገር አስወጣ። የሚገርመው ይህ ክፍለ ሀገሩን ያላንዳች ውጊያ ለሕወሓት ያስረከበበት እርምጃ «ዘመቻ ቅጣው» የሚል ስም ተሰጥቶት ነበር። ከቅጣት ይልቅ ሽሽት መሰየው የሆነው ይህ ትእዛዝ በመንግሥት ሠራዊት ስነልቡና ላይ ያሳደረው ተፅእኖ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም። ከዚያ በኋላ «የወያኔ ጦር መጣ!» እያሉ የጦር ካምፕንና ከተማ እየተዉ መፈርጠጥ የተለመደ ነገር ሆኖ የደርግን ሠራዊት የመጨረሻ ውድቀት አፋጠነው።

ሕወሓትም ትግራይን ደጀን አድርጎ ዘመቻውን ወደ መሐል አገር አስፋፋ። ትግራይን ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተነሣው ድርጅት ሀገር-አቀፍ የሆነ አጀንዳ ማውጣት ግድ ሆነበት። የነዚህ ሁለት አጀንዳዎች - አንዱ ጠባብ፣ ሌላኛው ሰፊ - ቅራኔም በ1983 ወታደራዊ ድልን ካገኘም በኋላ ለዓመታት ሲቆይ ነው። የሠፊው አጀንዳ አስፈፃሚ ይሆናል ተብሎ የታለመው ድርጅት የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) ተብሎ የተዋቀረው የተለያዩ ድርጅቶች «ጥምረት» ሲሆን፣ አባላቱም ሕወሓት፣ ከተበታተነው የኢሕአፓ ሠራዊት ተርፈው በሰሜን ወሎ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ታጋዮችን ያቀፈው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢሕዴን)፣ የኦሮሞን ሕዝብ ይወክላል ተብሎ የተቋቋመው የኦሮሞ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) እና የተማሩ የደርግ ሠራዊት መኰንኖች የተሰባሰቡበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መኰንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ (ኢዴመአን) ነበሩ።

ኢሕአዴግ የአቻ ድርጅቶች የኅብረት ግንባር ይባል እንጂ ሕወሓት መሪውን ሚና ይጫወት እንደነበር ብዙም ምርምር የሚያሻው አይደለም። ከዚህም ሌላ፣ የድርጅቶቹ የድጋፍ ምንጭና ጥንካሬም የተለያየ ነበር። ሕወሓትና ኦሕዴድ በብሔረ ሰብ ላይ የተዋቀሩ ሲሆኑ (የመጀመርያው በትግራይ፣ ሁለተኛው በኦሮሞ)፣ ኢሕዴንና ኢዴመአን ኅብረ-ብሔራዊ መሠረት ነበራቸው። በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ከኦሕዴድ ይልቅ ኦነግ ተቀባይነት እንዳላው ሕወሓት ሳያውቅ ቀርቶ አይደለም። ነገር ግን ከኦነግ ጋር ግንባር ለመፍጠር የተደረገው ጥረት ስኬታማ ባለመሆኑ፣ ከኦሮሞ የጦር ምርኮኞችና በኦነግ ካልታቀፉ ምሁራን የተውጣጣ የኦሮሞ ድርጅት ለማቋቋም ተገደደ። ኢሕዴን የሚንቀሳቀሰው በአማርኛ ተናጋሪ ክፍላተ ሀገር ይሁን እንጂ ራሱን እንደ አማራ ድርጅት ይፋ ያደረገው ከድል በኋላ አዲስ ስም (ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ ብአዴን) ይዞ ብቅ ካለ በኋላ ነው። በመኰንኖቹ ስም የተቋቋመው ድርጅት በጦርነቱ ወቅት የጦር ምርኮኞችን በፖለቲካ መድረክ ዙሪያ ከማሳባሰብ ባሻገር ከድል በኋላ ስለከሰመ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ፋይዳ አልነበረውም።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ አፍአቤትና ሽሬ እንዳ ሥላሴ የደርግ መንግሥት ፍፃሜ መጀመርያ ነበሩ። እነዚህ ግዙፍ ወታደራዊ ሽንፈቶች በዋና ከተማዪቱ አዲስ አበባ መጠነኛ የፖለቲካ ቀውስ አስከተሉ። በሥርዓቱ ላይ ያንገፈገፈው አደጋ ያሳሰባቸው ከመላው የጦር ኃይሎች የተውጣጡ ጀኔራሎች በአዛዦቻቸው በመንግሥቱ ላይ ተነሱበት። ግንቦት 8፣ 1981 መንግሥቱ የልብ ወዳጅ ወደሆነችው ወደ ጀርመን ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ (ምሥራቅ ጀርመን) ጉብኝት ለማድረግ አውሮፕላኑ የቦሌ አየር ማረፊያን ለቆ በተነሣ በጥቂት

ሰዓታት ውስጥ፣ በመከላከያ ሚኒስቴር የተሰባሰቡት ጀኔራሎች መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ከሥልጣን መውረዱን ለራሳቸውና እዚያው ግቢ ውስጥ ለተሰበሰቡት የሲቪል ሠራተኞች አወጁ:: ኀብረታቸው የሚያስደንቅ ቢሆንም፣ ዝግጅታቸውና ስልታቸው መፈንቅለ መንግሥቱን ገና ከመጀመርያው ለክሽፈት ዳረገው::

ምሥጢር ለመጠበቅ ይመስላል፣ እዚያ መሃል አዲስ አበባ ተሰባስበው እስከሚነገራቸው ድረስ፣ ጉዳዩን የሚያውቁት አራት ጀኔራሎች ብቻ ነበሩ:: ከነሱም መሓል መሪዎቹ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹሙ ጀኔራል መርዕድ ንጉሤና የቀድሞ የአየር ኃይል አዛዥና በወቅቱ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር የነበረው ጀኔራል ፋንታ በላይ ነበሩ:: ቢያንስ ባንድ ታማኝ ጦር የሬዲዮ ጣቢያውን ይዘው ድርጊታቸውንና ዓላማቸውን ለሕዝብ ማስታወቅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የተገነዘቡት አይመስልም:: ከሁሉም በላይ ለሴራው መክሸፍ ዐቢይ ምክንያት የሆነው ቤተ መንግሥት ውስጥ የመሸገውን ቅልብ ጦር አስቀድመው ከጥቅም ውጭ ማድረግ ሳይችሉ መቅረታቸው ነበር:: ስለሆነም ያው ጦር የተሰበሰቡበትን መከላከያ ሚኒስቴር ከቦ በቁጥጥር ሥር አዋላቸው:: አማፅያኑን ለማገዝ ከአሥመራ ተልኮ የነበረው በጀኔራል ቁምላቸው የሚመራው ጦርም ከነሱ ጋር ግንኙነት ለማድረግ ሳይችል ተበትኖ፣ አዛዡም ሸሽቶ ራሱን ለማዳን ተገደደ:: የሆነ ውጥረት እንዳለ ከመገንዘቡ በስተቀር መፈንቅለ መንግሥት መሞከሩን ያላወቀው የአዲስ አበባ ሕዝብም መክሸፉን ማታውኑ በሬዲዮ ሰማ::

የአዲስ አበባው ሁኔታ እንደዚህ ሰው ብዙም ሳይሰማ ሲያከትም፣ በተመሳሳይ ሁኔታ አሥመራ የተካሄደው አመፅ በአስከፊ ጭፍጨፋ የታጀበ ነበር:: በአየር ወለድ ክፍለ ጦር የሚመሩ ለመንግሥቱ ታማኝ የሆኑ መኰንኖች አማፅያኑን እጅግ ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ደምስሰው አመፁን አከሸፉት:: በአመፁ የተሳተፉት ጀኔራሎች ከፊሉ ቢሮቻቸው ውስጥ እንዳሉ ሲገደሉ፣ የቀሩት ከተሰወሩበት ቦታ እየታደኑ ተይዘው ተረሸኑ:: የዚህ የብቀላ እርምጃ ሰለባ ከሆኑት መካከል የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት ዋና አዛዥ የነበረው ጀኔራል ደምሴ ቡልቶ ሲገኝበት፤ መቀጣጫ እንዲሆን ተብሎ በድኑ በአሥመራ ጎዳናዎች ተጎተተ::

መንግሥቱም ለጉብኝት ከሄደበት አገር በድል አድራጊነት ተመልሶ የራሱን የብቀላ ድግስ አዘጋጀ:: መጀመርያ በቁጥጥር ሥር የዋሉት ጀኔራሎች የጦር ፍርድ ቤት ቀርበው በአገር ክህደት ወንጀል ተከሰሱ:: ነገር ግን የፍርዱ ሂደት እየተጓተተ ሲያስቸግረው፣ መንግሥቱ ሌላ ቀልጠፍ ያለ መንገድ ፈለገ:: ከተከሳሾቹ መሃል 12ቱ ጀኔራሎች ላይ የሞት ፍርድ አስፈርዶባቸው ወዲያውኑ በመረሸን የአመፁን አንደኛ ዓመት አከበረ:: የዚህ ሁሉ የበቀል እርምጃ ድምር ውጤት ፊቱንም ያላማረበትን የደርግ ሠራዊት መሪ-አልባ አድርጎ ለሽምቅ ተዋጊዎቹ ሲሳይ ማድረግ ሆነ:: የተረሸኑትንና የታሠሩትን የጦር መሪዎች ለመተካት ብሎ መንግሥቱ የሾማቸው መኰንኖች የተደቀነውን ፈተና ለመቋቋም ብቃቱም ልምዱም የሌላቸው ነበሩ::

ከዚህ በኋላ፣ የደርግ ሥርዓት ውድቀት እጅግ በተፋጠነ መንገድ ቀጠለ:: በየካቲት 1982 ሻዕቢያ ከአስከፊና ጭፍጨፋ ከበዛበት ጦርነት በኋላ የደርግን የባሕር ኃይል ደምስሶ ምፅዋን ተቆጣጠረ:: በዚህም ሁኔታ ደርግ ቁልፍ



የሆነችውን የባሕር ወደብ ከማጣቱም ሌላ፣ ትግራይ ሙሉ በሙሉ በሕወሓት ቁጥጥር ስር በመውደቁ ኤርትራ ውስጥ ላለው ጦሩ ብቸኛ የሆነውን የስንቅ ማቅረቢያ መስመር አስረከበ:: በመሃል አገር ደግሞ፣ ኢሕአዴግ ወደ አዲስ አበባ የሚያረማምዱትን ተከታታይ ዘመቻዎች ከፈተ:: በ1982 መጀመርያ ላይ የጎንደር ክፍለ ሀገርን ለመቆጣጠር የከፈተው ዘመቻ ለጊዜው ቢከሽፍበትም፣ ጉና በተባለው ተራራ ላይ በተደረገ ጦርነት ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሎ ደብረ ታቦርን ተቆጣጠረ:: ከዚያም፣ ደቡብ ወሎ ውስጥ መራኛ በተባለው ሥፍራ ባገኘው ድል ወደ ሰሜን ሸዋ ለመረማመድ ቻለ::

እነዚህን ድሎች ተቀናጦ፣ ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ለመቆጣጠር ስሜትን በሚኮረኩሩ ታሪካዊ ስሞች የሸለማቸውን የጦር ዘመቻዎች አወጀ:: በዘመቻ ቴዎድሮስ አማካይነት ጎጃምን ተቆጣጠረ:: በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና በተጫወተውና የወሎ ተወላጅ በሆነው በዋለልኝ መኰንን ስም የተሰየመው «ዘመቻ ዋለልኝ» የደርግን ሠራዊት ከዚያ ክፍለ ሀገር ጠራርጎ አስወጣ:: የ«ዘመቻ ቢሉሱማ ወልቂጡማ» (በኦሮምኛ ቋንቋ «ነፃነትና እኩልነት») ዓላማም ኢሕአዴግን ከጎጃም ወደ ወለጋ ማሸጋገር ነበር:: ከነዚህ ተከታታይ ወታደራዊ ድሎች በኋላ አዲስ አበባን በሦስት አቅጣጫ (ሰሜን፣ ምሥራቅ እና ምዕራብ) አጥቅቶ ለመያዝ አስተማማኝ ሥፍራዎችን ያዘ::

ነገር ሁሉ ካለቀለት በኋላ፣ ደርግ የሰላም አማራጮችን መቃኘት ጀመረ:: ደርግ ወታደራዊ የበላይነት ባሳየበት በ1970ዎቹ በቅጡ ያልተፈለገ ሰላማዊ መፍትሔ የኃይል ሚዛን ብቻ ሳይሆን ዲፕሎማሲያዊ ድጋፉም ወደ ሽምቅ ተዋጊዎቹ በዞረበት በ1980ዎቹ ይገኛል ማለት ዘበት ነበር:: ደርግ ሙዝዝ ብሎ የያዘውን የማርክሲስት ሌኒኒስት ካባ ብሔርተኛ ግንባሮች በሚያስደንቅ ፍጥነት አውልቀው በመጣል በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት (ስቴት ዲፓርትሜንት) ውስጥ ሞገስ ለማግኘት በቅተዋል:: ካሳዩት ወታደራዊ ጥንካሬ የተነሣም በአፍሪካ ቀንድ የሚደረግ ማናቸውም አዲስ የፖለቲካ አደረጃጀት እነሱን ማሳተፍ የግድ እንደሆነ የአሜሪካ ባለሥልጣናት ከተገነዘቡት ውሎ አድሯል::

ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ምክንያት የማታ ማታ ፍሬ አልባ የሆነው የሰላም ድርድር የመጀመርያው ምዕራፍ የተመራው በቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ነው:: በካርተር አማካይነት የሻዕቢያና የደርግ ልዑካን በ1982 ዓ.ም. መጀመርያ በአትላንታ፣ ቀጥሎ በናይሮቢ የሰላም ድርድሮች አካሄዱ:: በነዚህ ስብሰባዎች ሁለቱ ወገኖች ወደ ፍሬ ነገሩ ሳይገቡ በሥነ ሥርዓት ነጥቦች ላይ መስማማት አቅቷቸው ያለ ውጤት ተለያዩ:: በደርግና በሕወሓት መካከል ሮም ላይ በቀድሞ የኢጣሊያ አምባሳደር ሸምግልና በመጋቢት 1982 የተደረገው የሰላም ድርድርም፣ ሕወሓት ሌሎችም የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች መሳተፍ አለባቸው ብሎ ሲያመርር እንዲሁ ውጤት-አልባ ሆኖ ቀረ:: እነዚህ ድርድሮች የፈረሱት ሥነ ሥርዓታዊ ወይም ቴክኒካዊ በሆኑ ምክንያቶች ይምሰል እንጂ መሠረታዊ ችግሩ ወታደራዊ ሁኔታው ነበር:: ይኸውም ድርድሩ የሚካሄደው ግንባሮቹ አሸናፊነታቸው እየተረጋገጠ ባለበት ሁኔታ፣ ደርግ ደግሞ ተሸናፊነቱ ግልፅ እየሆነ በመጣበት ወቅት መሆኑ ነው::

በግንቦት 1983 ለንደን ላይ በደርግና በግንባሮቹ መካከል (አሜሪካ ጨምሮ) የተደረገው ስብሰባ - በተለምዶ የለንደን ጉባዔ እየተባለ የሚታወቀው - ገሓድ ያወጣውም ይኸንኑ እውነታ ነው። የጉባዔው ሰብሳቢ በአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ጉዳዮች ኃላፊ የነበረው ሄርማን ኮኸን ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑካን የተመሩት ነገር ዓለሙ ሁሉ ጨልሞበት ብቻውን የቀረው መንግሥቱ ባለቀ ሰዓት ባደረገው ሹም ሽር ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ በተሾመው በተስፋዬ ዲንቃ ነበር። ደጀን የሌለው ጦር ይመስል የነበረው የመንግሥት ልዑካን ቡድን ይህ ነው የሚባል መደራደሪያ አቅም አልነበረውም። ይባስ ብሎ ደግሞ፣ ድርድሩ በመካሄድ ላይ እያለ፣ በግንቦት 14 ቀን መንግሥቱ ማንም ያደርገዋል ብሎ ያላሰበውን አደረገ። ለመንግሥት ሥራ የሚጓዝ አስመስሎ አውሮፕላን ይዞ መጀመርያ ወደ ናይሮቢ፣ ከዚያም ወደ ሐራሬ (ዚምባብዌ) ሸሸ። ዳግማዊ ቴዎድሮስ ይሆናል የተባለው መሪ አገር ጥሎ በመጥፋት ራሱን ማዳኑን መረጠ። ከሽሽቱ ጀርባ የሥልጣን ዝውውሩ ያለ ብዙ ደም መፋሰስ እንዲጠናቀቅ የፈለገችው የአሜሪካ ግፊት አለበት የሚል ግምትም አለ።

ያም ሆነ ይህ የመንግሥቱ ካገር መውጣት ቀድሞውኑም ወዳንድ ወገን ባጋደለው ወታደራዊ ሁኔታ ላይ ቅፅበታዊ እንደምታ ነበረው። ሁለተኛው አብዮታዊ ጦር ፍርክርኩ ወጥቶ ሻዕቢያም ለዐሥርት ዓመታት ዒላማው ወደነበረችው አሥመራ በግንቦት 16 ሰተት ብሎ ለመግባት ቻለ። የለንደኑ ጉባዔም በቅጡ ሳይጀመር ተጠናቀቀ። ግንቦት 20፣ 1983 ማለዳ ላይ የኢሕአዴግ ሠራዊት አዲስ አበባን ተቆጣጠረ። መንግሥት ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ሥርዓት ከውሉ ሲለወጥ፣ የተሰማው ተኩስ ጥቂት ያንገራገሩ የመንግሥቱ ጠባቂዎች ከድል አድራጊው ጦር ጋር ያደረጉት የተኩስ ልውውጥ ብቻ ነበር።

# መደምደሚያ

